ልዩ ዕትም

ነገረ ኢትዮጵያ

ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እንናገራለን!

ቅፅ 1 ቁጥር 14 | አርብ ግንቦት 15 2006 ዓ.ም | ዋጋ 8.00

የግንቦት 20 ፍሬዎች

ሐኪም አጥቶ የሞተው ሐኪም ! 16

ግንቦት 20 የበላቸው ቀሺ ገብሩዎች 3

❖ ግ ን ቦ ት ና ግንቦታውያን 5

ግንቦት 20ና የእምነት ነፃነት 4

ታዴዎስ ታንቱ የ ግ ን ቦ ት 20ን እንክር ዳድ ለመመ ንገል! 8

‹‹ግንቦት 20 ህዝቦቻችን የታፈኑበት እንጂ ነጻ የወጡበት አይደለም››

አቶ አበባው መሐሪ፣ የመኢአድ ፕሬዚዳንት

‹‹‹ሥርዓቱ በከፋ ሁኔታ ወደኋላ ተመልሷል››

አቶ ስለሺ ፈይሳ፣ የሰማያዊ ፓርቲ ም/ሊቀመንበር

‹‹የትግራይ ህዝብ ከግንቦት 20 ተጠቃሚ አይደለም››

አቶ አብርሃ ደስታ፣ የአረና ትግራይ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

‹‹ግንቦት 20 ኢትዮጵያዊነትን በእጅጉ አደብዝዟል››

አቶ ሰለሞን ስዩም፣ የአንድነት ፓርቲ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ

ሰማያዊ በቅርቡ የተገደሉትን ንጹሃን ዜጎች በሻማ ማብራት አሰበ

ፓርቲው ግንቦት 23 የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም አዘጋጅቷል

ግንቦት 20...ከአንድ አምባገነን ወደ ሌላ አምባገነን!

ርዕሰ አንቀፅ

ግንቦት 20...ከአንድ አምባገነን ወደ ሌላ አምባገነን!

ባለፉት ሁለት አስርት አመታት ዓለም በቴክኖሎጅና በኢ ኮኖሚው በእጅጉ የተለወጠበት፣ ለሰብአዊ መብትና ዴሞ ክራሲ መከበር በር የተከፈተበት፣ በሉላዊነት ምክንያት የዓለም ህዝቦች ከመቼውም ጊዜ በላይ የተሳሰሩበትና ለመ ተሳሰርም እድል የተገኘበት ጊዜ ነው። ይህን ነጻነታቸውን ካገኙ 20 አመት ያልበለጣቸው አገራትም ነጻነታቸውን በአ ግባቡ ተጠቅመውበት ህዝባቸውን ለመቀየር ችለዋል። ለአ ብነት ያህልም ደቡብ አፍሪካን መጥቀስ ይቻላል። ከደቡብ አፍሪካ በተጨማሪ ኢ.ኤ.አ በ1991 የራሷን አስተዳደር የመ ሰረተችውና ዓለም እውቅና ያልሰጣት ሶማሊ ላንድ እንኳ በፍትሃዊ ምርጫ፣ በሰላም መሪዎቿን በመምረጥ በአፍሪካ ቀንድ ብቸኛዋና በዓለም መንግስታት በአገርነት እውቅና ላገ ኙትም በምሳሌነት እየተጠቀሰች ትገኛለች።

በሌላ በኩል አገራችን ኢትዮጵያ ረዥም የነጻነትነት እድሜ ያላት ብትሆንም አሁን ላይ ቀደም ብላ ከቅኝ አገ ዛዝና ጭቆና ነጻ እንዲወጡ ካገዟቸው የአፍሪካ አገራት ባነሰ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። ለዚህ ኋላ ቀርነቷ ደግሞ ባለፉት 23 አመታት ያገኘቻቸውን አጋጣሚዎች ገዥዎቹ መጠቀም ባለመቻላቸው እንደዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ስልጣን ላይ የሚገኘው ህወሓት/ኢህአዴግ መጀመሪያ ላይ የዓለምን ማህበረሰብ ቀልም ለመሳብ መሰረታዊ ለውጦችን አድርጎ የነበርና እነዚህንም በህገ መንግስቱ ላይ ያስቀመጠ ቢሆንም ሲተገብራቸው ግን አልታየም። በተለይ ስልጣን ከያዘ ከአራትና አምስት አመት በኋላ ወደ ነበረበት ‹‹ግራ ዘመምነት›› በመመለስ በህገ መንግስቱ የፈቀዳቸውን መብቶች እንደገና በግልጽ ሲደፈጥጥ ተስተውሏል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን እንደያዘ በመቶዎቹ የሚቆጠሩ የህትመት ሚዲያዎች ፈቃድ አግኝተው ለህዝብ መረጃ በማድረስ ላይ የነበሩ ቢሆንም ሚዲያ ህዝብን ማንቃቱን ያልወደደው ገዥው ፓርቲ እየቆየ አፈናውን ተያይዞታል። በመሆኑም በርካታ ሚዲያዎች ወደ አደባባዩ ወጥተው እን ደገና ለመዘጋት ተዳርገዋል። ጋዜጠኞች ታስረዋል፤ እየታ ሰሩም ነው። በጫናው ምክንያት ተሰደዋል፤ እየተሰደዱም ይገኛሉ። በተለይ ህወሓት/ኢህአዴግ የደነገጠበት የ1997 ምርጫን ተከትሎ በርካታ የህትመት ሚዲያዎች ሲዘጉ፣ ጋዜጠኞች በአገር ክህደት ወንጀል ተከሰው ዘብጥያ ወርደ ዋል። በርካቶቹ ተሰደዋል። ይህን ሁሉ ጫና ችለው ለህ ዝባቸው መረጃ ለማድረስ የጣሩት እንደ እስክንድር ነጋ፣ ርዕየት ዓለሙና ውብሸት ታየ ያሉት ደግሞ በአሁኑ ወቅት ‹‹አሸባሪ›› ተብለው እስር ቤት ውስጥ ይገኛሉ። በቅርቡ ከዞን ዘጠኝ አባላት ጋር የታሰሩት ሶስት ጋዜጠኞች ስርዓቱ ባለፈው 23 አመት ያደበረውን የአፈና ባህል አጠ ናክሮ እንደቀጠለ የሚያሳይ ሆኗል።

በተመሳሳይ የመደራጀት፣ የመሰብሰብና ሌሎች መብቶች ባለፈው 23 አመት ህገ መንግስቱ ላይ ከሰፈረው በተቃራኒ እየተደፈጠጡ ቀጥለዋል። በአንድ ወቅት ጠንካራ ተቃዋሚ እንዳጣ በግልጽ ሲናገር የነበረው ገዥው ፓርቲ ከ1997 በኋላ ለተቃዋሚዎች መፈናፈኛ ላለመስጠት በርካታ ፀረ ህገ መንግስታዊና አፋኝ አዋጆችን አጽድቆ በህግ መሳሪያ ነት እየገዛ ቀጥሏል። ባለፉት 8 አመታት ህገ መንግስቱ የፈ ቀደው ሰላማዊ ሰልፍ ገዥው ፓርቲ ተከልክሎ ቆይቷል፡ ፡ በአሁኑ ወቅትም በተቃዋሚዎች ግፊት የተጀመሩ የተቃ ውሞ ሰልፎች በገዥው ፓርቲ የደህንነትና የፖሊስ ኃይል የሚጠበቅባቸውን ያህል ሚና እንዳይወጡ ተከልክለዋል።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህጋዊ በሆነ መንገድ የስብሰባ አዳራ ሽና ሌሎቹንም ለትግሉ ሊያገኙዋቸው የሚገቡ አገልግሎ ቶችን እንዳያገኙ ገዥው ፓርቲ ጠንክሮ እየሰራ ይገኛል። ይህም የፖለቲካ ኃይሎች በሰላማዊ ትግሉ ተስፋ እንዲቆ ርጡና ሌሎች ሰላማዊ ያልሆኑ አማራጮችን እንዲከተሉ እስከማድረግ ደርሷል። ከተቃዋሚ ፓርቲዎች በተጨማሪ ሲቪክ ማህበራትና ሌሎችም ለህዝብ ጥቅም የሚቆሙ የህ ዝብና የመንግስትን ተቋማት አንድም ለራሱ መጠቀሚያ ማድረጉ ከዚህም በተጨማሪ ስራቸውን እንዳይተገብሩ መሰ ናክል መፍጠሩ ህዝብ ድምጹን የሚያሰማበት መድረክ እን ዲያጣ ተደርጓል።

ሚዲያ፣ ተቃዋሚዎችና ተቋማት በመዳከማቸው ገዥው ፓርቲና ፖለቲከኞቹ ያለምንም ተጠያቂነት የአገሪቱን ሀብት ተጠቅመውበታል። በመሆኑም ባለፉት 23 አመታት ከአገርና ከህዝብ ጥቅም ይልቅ ግለሰባዊ፣ የፓርቲና ቤተሰ ባዊ ጥቅምን ማጋበስ የስርዓቱ ባህሪ እንደሆነ ታይቷል። በዚህም ምክንያት ህዝብ ከአገሩ ኢኮኖሚ የሚገባውን እን ዳያገኝ ተደርጓል። በሙስና፣ በስርዓቱ ደጋፊነትና በመሳሰ ሉት ካልሆነ ህጋዊ መንገድን የያዘ ዜጋ ስራ መስራት ባለ መቻሉ አገሪቱ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እን ዳታገኝ ተደርጋለች። ምሩቃን፣ ከስርዓቱ ጋር ግንኙነት የሌ ላቸው ምሁራንና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች ህጋዊ በሆነው መንገድ ጥቅም ባለማግኘታቸው ለስደት፣ ለድህ ነት ተዳርገዋል።

በተቃራኒው ግን ይህ ያፈጠጠ እውነታ ተገልብጦ የግንቦት 20 ፍሬዎች እየተባለ ህዝብ ባዶ ፕሮፖጋንዳ ይጋታል፡ ፡ በመሆኑም ገዥው ፓርቲ እንደሚለው ግንቦት 20 የኢ ትዮጵያ ህዝብ ነጻነቱን ያገኘበት ሳይሆን ከአንዱ አምባገነን ስርዓት ወደ ሌላ መልኩን የቀየረ አምባገነን ስርዓት የተሸ ጋገርንበት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። እናም ያለን በትን ትክክለኛ መልክ ሽፋፍኖ ስለሌለ ለውጥ ህዝብን በፕ ሮፖጋንዳ ከማደንቆር ይልቅ ወደ ትክክለኛ የህዝብ ተጠቃ ሚነትና ነጻነት የሚያደርሰውን መንገድ ይዞ ለአዲስ ለውጥ መስራት እንደሚገባ መገንዘብ ይገባል።

እንዲህም ተብሏል!

‹‹የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች ባህሪ ከአዕምሮ ችግራቸው ስሜታዊ ድንፋታቸው በመ ነሳት ስመረምር ምንጩ ጥላቻ፣ ንፉግነት፣ ክፋት በቀል፣ እኩይነት እና ራስ ወዳድ ሆኖ የበላይነትን ከመፈለግ ህመማቸው ጋር የተያያዘ ሆኖ እናገኛቸዋለን››

አርቲስት ደበበ እሸቱ

(ምንጭ አውራምባ ታይምስ 2003 ዓ.ም)

ነገረ-ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጥር 2006 ዓ.ም ተመሰረተች፡፡ ነገረ-ኢትዮጵያ በሰማያዊ ፓርቲ አሳታሚነት የምትታተም ፖለቲካዊ፣ ወቅታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የምትዳስስ በየሳምንቱ አርብ የምትወጣ ጋዜጣ ናት፡፡

ጋዜጣዋ ሚዛናዊና ነጻ ሆና የማገልገል መርህ አላት፤ ማንኛውም ሀሳብ በነጻነት የሚስተናገድባትና የሚንሸራሸርባት እንድትሆን እንፈልጋለን፡፡ ገዥው ፓርቲም ቢሆን አቋሙንና ፖሊሲውን ለመግለጽ ቢፈልግ የሰፊ ሚዲያ ባለቤት ነው ብለን ዕድሉን አንነፍገውም፤ በራችን ለሁሉም ክፍት ነው፡፡

የአሳታሚ አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/10 ቤት ቁ.460
E-mail: info@semayawiparty.org
P.O.Box: 180298

ዋና አዘጋጅ ፡- ጌታቸው ሺፈራው
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02
ቤት ቁ. 07/859/14
E-mail:getcholink@gmail.com
ስልክ ቁጥር: 09-10-45-99-32

ምክትል ዋና አዘጋጅ፡- በላይ ማናዬ
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02 ቤት ቁ.099
E-mail: belaymb@gmail.com
ስልክ ቁጥር: 09-20-19-09-72

ሌይ አውት ዲዛይን ፡-
ደሳለው ጌትነት

አምደኞች ፡-
ፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም
ታዴዎስ ታንቱ
ታምራት ታረቀኝ
አፈወርቅ በደዊ
እያስፔድ ተስፋዬ

ሕትመትና ክትትል
ሳሙኤል አበበ
0913 98 46 40

አታሚ፡- ሰማያዊ ፓርቲ

ልብ አድርጉ

ግንቦት 20'ና

ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት

በላይ ማናዬ

«አንድ ለእናቱ» የተሰኘውን በአጼ ቴዎድሮስ ህይወ ትና የሀገር አንድነት ተጋድሎ ላይ የሚያጠነጥነውን ታሪካዊ ልቦለድ መጽሐፍ ለንባብ ሲያበቃ በአድናቆት የተደመሙ እንደነበሩ ሁሉ በስራው የተከፉም አልጠ ፉም ነበር፡፡ በተለይ አጼ ኃ/ስላሴ የቴዎድሮስ ስብዕና እንዲያ ገንኖ እንዲታይ አለመፈለጋቸው በግልጽም ባይሆን በገደምዳሜ ተመልክቷል፡፡ ቢሆንም ንጉስ ቻይ ነውና፣ የንጉስ ሆድ ከሀገር ይሰፋልና ደራሲው በ«አንድ ለእናቱ» ድርሰቱ የተፈጠረበት ችግር አልነበ ረም፡፡ በዚህ የተበረታታው ደራሲ ቀጣይ ልቦለድ መጽሐፉን ለንባብ አበቃ፣ የደራሲው ቀለም ለመሆን የቻለውን «አልወለድምን»፡፡ ይህ ደራሲ አቤ ጉበኛ ነው፡፡

አቤ «አልወለድምን» ለንባብ ባበቃበት ጥቂት ቀናት ውስጥ 800 ያህል ኮፒዎች ቢሸጡለትም በዚሁ ሊቀጥል ግን አልቻለም፡፡ አዎ፣ መጽሐፉ ታገደ፡፡ ስለ ሆነም የተሰራጨው መጽሐፍ ሁሉ በአስቸኳይ እንዲ ሰበሰብ ተደረገ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ መጽሐፉ «ህዝቡን ለአመጽ ያነሳሳል» የሚል ነበር፡፡ ስለሆነም የተሰበ ሰቡት መጽሐፎች ተቃጠሉ፡፡ ደራሲውም በንጉስ ነገስት አጼ ኃ/ስላሴ የደህንነት ኃይሎች ታድኖ ተያዘ፡፡ ደራሲ አቤ ጉበኛ ትንሽ ጊዜ በእስር እንደቆየ በጊዜው «ወንጀለኞችና አደገኛዎች» በግዞት ወደሚቀመጡበት ኢሊባበር ሞቻ ተጋዘ፡፡ አድናቂዎቹና ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት መከበር አለበት ብለው የሚሟገቱ አካላት የአቤ መጥፋት አሳሰባቸው፣ ምላሽም ሻቱ፤ ሞቶ ይሆን ሲሉም ስጋት ገባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አቤ ምላሽ ሰጠ፣ «ሞቻለሁ» አለ፡፡ በቅኔ መናገሩ ነበር፡፡ አንድም በህይወት ብኖርም አለ አትበሉ፣ ሞቻለሁኝ የለሁም ለማለት፣ ሁለትም ሞቻ የሚባል ቦታ አገኛ ለሁ ለማለት፡፡ ይህ እንግዲህ አቤ ሃሳቡን በመግለጹ፣ በመጻፉ የደረሰበት እንግልት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

አቤ ብቻ ሳይሆን በርካታ ከዘመኑ ፖለቲካዊ ስርዓት ለየት ያለ ሀሳብ የያዙና፣ የያዙትን ሀሳብ በተለያዩ መንገድ የገለጹ ኢትዮጵያውያን በበጎ ዓይን የሚታዩ አልነበሩም፡፡ ደራሲ አቤ ጉበኛ በብዕሩ የተቃወመ ውና «አልወለድም» ድርሰቱ በጊዜው የነበረውን (አሁንም ድረስ ያለውን) የበዛ በህዝብ ላይ የሚደርስ ጭቆና አጋልጧል፤ በአደባባይ ተቃውሟል፡፡ የንጉሱ ዘውዳዊ ስርዓት በአብዮት ተገርስሶ ወታደራዊው ደርግ ስልጣን ላይ ሲወጣ አቤ ጉበኛ ትንሽ ፋታ ያገኘ መስሎ ነበር፡፡ ዳሩ ግን አፈናው በዛ እንጂ የሚናፍ ቃት ነጻነት አልተወለደችም፡፡ ቢሆንም ለአጭር ጊዜ «አልወለድምን» ድጋሜ አሳትሞ ገበያ ላይ ለማዋል በቅቶ ነበር፤ ወዲያው ግን በደርጉ ስርዓትም ለሁ ለተኛ ጊዜ መጽሐፉ ታገደ፡፡ አቤ የዋዛ ሰው አልነበ ረም፤ «ፖለቲካና ፖለቲከኞች» የሚል ሌላ መጽሐፍ ደረሰ፡፡ በዚህ ጊዜ ትልቁ ስንክሳር ሳንሱር የሚባል ነገር የስራው ማነቆ፣ ሀሳብን የመግለጽ መብት ጸር ሆኖ ተደንቅሮበት ነበር፤ ወቅቱ ደግሞ የደርግ መንግ ስት በመላ ሀገሪቱ የነገሰበት፡፡

እውነት ነው በንጉሱም ሆነ በወታደራዊው ደርግ ዘመነ መንግስታት ሀሳብን በነጻነት መግለጽ ብዙ ዋጋ ያስከፍል እንደነበር የአቤ ጉበና ውጣ ውረድ ብቻ ሳይሆን የሌሎች በርካቶቹ ህይወትም የሚነ ግረን ጉዳይ ነው፡፡ በአጼ ኃ/ስላሴ ዘመን የነበረው ታዋቂውና ትንታጉ የሬድዮ ጋዜጠኛ አሳምነው ገብ ረወልድን ማን እንደገደለው ማንም በትክክል የሚያ ውቅ አልተገኘም፡፡ የሚታወቀው ነገር ቢኖር በሬድዮ በሚሰራቸው ፕሮግራሞቹ የማይደሰቱ ባላስልጣና ትና ሙሰኞች እንደነበሩና የጋዜጠኛውን ሞት ከእ ነዚህ አካላት ጋር የሚያያይዙት መኖራቸው ብቻ ነው፡፡ በደርጉ ጊዜ ስለነበረው ባለጣፋጭና ሰንፋጭ ብዕር ባለቤቱ ደራሲና ጋዜጠኛ በዓሉ ግርማ አሟሟት ወይም የት እንዳለ የሚያውቅና እንዲህ ነው ያለን ሰው እስካሁን አልመጣም፡፡ አሁንም የታወቀው ነገር ቢኖር በዓሉ ሀሳቡን በጹሑፍ በመግለጹ ብቻ ብአጥ ፊዎቹ አሊማ ውስጥ ገብቶ እንደነበር ነው፡፡

እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ አያሌ ኢትዮጵያውያን ሀሳባቸ ውን በመግለጻቸው ብቻ ከጉልበታሞች የሚመጣባ ቸውን አስፈሪ አደጋ የሚከላከልላቸው ከየትም አል ተገኘም፡፡ እናም ከህይወት ማጣት ጀምሮ እስር፣ እን ግልት፣ ማስፈራሪያና ዛቻ፣ የአካል ጉዳት ወዘተ ደርሶ ባቸዋል፡፡ ይህም በርካቶች ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት በሀገራቸው እንዲሰፍን ምን ያህል ዋጋ እንደከ ፈሉ መገንዘብ የሚያስችለን ይሆናል፡፡ በስዕል፣ በስነ-ፅሑፍ፣ በንግግር፣ በሙዚቃና በመሳሰሉት መንገዶች ሀሳባቸውን ለህዝብ ለማድረስ የጣሩ ሰዎች መንገዱ አልጋ በአልጋ ሆኖላቸው አያወቅም፡፡

ከግንቦት 20/1983 ዓ.ም በኋላስ?

ግንቦት 20/1983 ዓ.ም ደርግ ለውድቀት፣ ኢህአ ዴግ ደግሞ ለአዲስ መንበር የበቁበት ጊዜ ነበር፡፡ ይህ የኢህአዴግ «ድል» አስገኛቸው ከሚባሉት «ትሩ ፋቶች» መካከል ዋነኛው የሽግግር መንግስቱን ጊዜ ማብቃት ተከትሎ በ87 ዓ.ም የጸደቀው የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት ነው፡፡ ይህ ህገ-መንግስት በግልጽ እን ደሚደነግገው ቀደም ብሎ በደርግ ዘመን ሲተገበር የነ በረው ቅድመ ምርመራን (ሳንሱርን) በመሻር፣ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን እውቅና የሰጠ ለመሆን የበቃ ነው፡፡ በዚህም ህገ-መንግስቱ ለአያሌ ኢትዮ ጵያውያን «ብሩህ ተስፋን የፈነጠቀ እንደነበር ይነገ ራል፤ በቅድመ ምርመራ የተሰላቹ ደራሲያን፣ በመና ገራቸው ችግር ይደርስባቸው የነበሩ ዜጎች ሁሉ በህገ-መንግስቱ መጽደቅ መደሰታቸው አልቀረም፤ ሊደሰ ቱም የተገባ ነበር፡፡ እናም በየቤቱ ታፍነው የቆዩ መጻ ሕፍት፣ ሙዚቃዎች፣ ስዕሎች ወዘተ ወደ አደባባይ፣ ወደ ህዝብ ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡

ይህን የመሰለው የዜጎች ተስፋ ግን ረጂም ጊዜ አብ ሯቸው መዝለቅ አልቻለም፡፡ አንዳንድ መጽሐፍት በሀገር ውስጥ እንዳይነበቡና ገበያ ላይ እንዳይሰራጩ መታገዳቸው፣ ስርዓቱን ያወገዙ ሙዚቃዎች በሬድ ዮና በቴሌቪዥን እንዳይተላለፉ መደረግ መጀመራ ቸው አዲሱን ስርዓትም ጥርጣሬ ውስጥ ከተተው፡፡ ገርበብ ማለት የጀመረው የነጻነት በር እንደገና በአጅጉ መጥበቡን ገፋበት፡፡ ቀጥተኛ ሳንሱር ቀርቶ የእጃ ዙር ሳንሱር ማቆጥቆጥ ቀጠለ፡፡ ህገ-መንግስቱ ከሰላ ይሆናል ቢባልም በአርቃቂዎቹ በራሳቸው መጣሱ አስገራሚ ሊሆን ቻለ፡፡

እርግጥ ነው በንጉሱ ዘመን ንጉስ ነገስቱንና የንጉሳ ውያን ቤተሰቦችን «ክብር» አለመጠበቅ ዋጋ ያስከ ፍል ነበር፡፡ እርግጥ ነው በደርጉ ዘመን ኮሚኒስታዊ ሀሳብን መቃረን ዋጋ ያስከፍል ነበር፡፡ አስር ቤት ያስ ወረውር ነበር፤ ያስገድል ነበር፡፡ ሆኖም ግን በንጉሱም ሆነ በወታደራዊ መንግስቱ ጊዜ ሽንገላ ብሎ ነገር አል ነበረም ማለት ይቻላል፡፡ በዴሞክራሲ ስም መነገድ መለያው አልነበረም፡፡ ግልጽ ጭቆና ነው የነበረው፡ ፡ በዚህም አጼ ኃ/ስላሴንም ሆነ ፕሬዚዳንት መንግ ስቱ ኃ/ማርያምን መቃወም ቀላል አልነበረም፡፡ ዳሩ ግን ከግንቦት 20 በኋላም ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሰንደቅ ዓላማ ዘቅዝቀዋል ብሎ በማህበራዊ ድረ-ገጽ የጻፈ (ለዚያውም በፎቶ ማስረጃ አስደግፎ) ዜጋ በዚሁ ምክንያት ይሰራበት ከነበረው መስሪያ ቤት ከስራው ከመባረር የታደገው ኃይል አልያም ህግ አል ተገኘም፡፡

እውነት ነው አሁን ሳንሱር የለም፤ ሀሳብን በነጻነት መግለጽ የሚያስከፍለው ዋጋ ግን አልቀነሰም፡፡ ኢህ አዴግ ግንቦት 20 አስገኝቷቸዋል ከሚላቸው ድሎች መካከል ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት መረጋገ ጡን እንደ አንድ ማሳያ ሲያነሳ ይደመጣል፡፡ ይህ ግን በወረቀት እንጂ በተግባር አልታየም፡፡ ምክንያቱም ዛሬም መጻፍ ያሳስራል፤ መናገር ከሐገር ያስከበልላል፡ ፡ ጥቂት የማይባሉ ዜጎች ሀሳብን ከመግለጽ ነጻነት ጋር በተያያዘ ቤታቸው ቃሊቲ፣ ዝዋይ፣ ቂሊንጦ... እስር ቤቶች ሆኖ ይገኛል፡፡ ህገ-መንግስቱን የሚጻረሩ አፋኝ አዋጆች እየወጡ ሀሳባቸውን የገለጹ ዜጎች ኢላማ ሆነዋል፡፡ ጋዜጠኞች በጻፉት ጽሑፍ ደህንነት አይሰማ ቸውም፤ ከሰላ የሚሉት አስተማማኝ ነገር የላቸውም፡፡ ዛሬ በሚገልጹት ሀሳብ ምክንያት ነገ አሸባሪ ላለመባላ ቸው በቂ ዋስትና የላቸውም፤ አሸባሪ ተብለው ዘብጥያ የወረዱ ወገኖቻቸውን እያዩ ነውና፡፡

ህዝብ አዲስ ዘመንን ብቻ እንዲያነብ፣ ኢቴቪን ብቻ እንዲመለከት፣ የኢትዮጵያ ሬድዮን ብቻ እንዲያደ ምጥ ሊፈርዱበት የሚቃጣቸው የስርዓቱ ጀሌዎችና አዛዥ ናዛዦች በርካቶች ናቸው፡፡ ስለ «ብሄር፣ ብሄረ ሰብና ህዝብ» እንዲዘፈን ብቻ የሚሹ የሞሉበት ስርዓት ላይ ሆነን ግንቦት 20ን የገድል ዕለት አድርገን መቀበል እንዴት ይቻለናል? «ጃ ያስተሰርያሌን» የመሳሰሉ ስር ዓቱን ይነቅፋሉ የሚባሉ መዝሙሮች በህዝብ ሚዲያ አይጫዎቱም፡፡ ምክንያቱም ይህ የኢህአዴግ አፋኝ ስርዓት ይህን አይፈቅድም፤ ሀሳብን በተቃውሞ መልክ መግለጽ በኢህአዴግ ሀሳብን በነጻነት መግለጽ መብት ዝርዝር ውስጥ አልተካተተም፡፡

በፊት አቤ ጉበኞን፣ በዓሉ ግርማንና አሳምነው ገብረ ወልድን የመሰሉ ኢትዮጵያውያን ሀሳባቸውን በነጻነት በመግለጻቸው ታስረዋል፤ ተገድለዋል፤ ተሰውረዋል፡፡ አሁን ላይ እስከንድር ነጋ፣ ርዕዮት ዓለሙ፣ ውብሸት ታዬ...ቃሊቲ ገብተዋል፡፡ ሙሉጌታ ሉሌ፣ ሲሳይ አጌና፣ አብይ ተክለማርያም፣ መስፍን ነጋሽ፣ አቤ ቶኪቻው... ሀሳባቸውን በመግለጻቸው ምክንያት የተደቀነባቸውን አደጋ በመሸሽ ሀገር ጥለው ሄደዋል፡፡ ጋዜጠኛ ተስፋ ለም ወልደየስ፣ አስማማው ኃይል ጊዮርጊስና ኤዶም ካሳዬ እንዲሁም የዞን ዘጠኝ ጦማሪዎቹ በፍቃዱ ኃይሉ፣ ናትናኤል ፈለቀ፣ ማህሌት ፋንታሁን፣ አጥናፍ ብርሃኔ፣ ዘላለም ክብረትና አቤል ዋበላ በቅርቡ ሀሳብን በነጻነት መግለጽ ባመጣባቸው «ጣጣ» በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ይህ ነው ግንቦት 20 ያረጋገጠው ሃሳብን በነ ጻነት የመግለጽ ህገ-መንግስታዊ መብት?

እናም ከብዙ መስዋዕትነት በኋላም፣ ከብዙ አቤ ጉበ ኞዎች፣ ከብዙ እስከንድር ነጋዎች፣ ከብዙ አሳም ነው ገ/ወልዶች ጊዜ በጓላም ሀሳብን በነጻነት የመግ ለጽ መብት እንደተደፈጠጠ ይገኛል፡፡ ያለፈውን ሳን ማርበት፣ ከዚያኛው ሳንሻል አሁንም ባለንበት እየረገ ጥን አንዳንዴም የኋሊዮሽ እየተጓዝን ቀጥለናል፡፡ በተ ለይማ ከ1997 ዓ.ም ወዲህ ብሶብናል፡፡ ዓለም የትና የት ጥሎን ሲሸመጥጥ እኛ ዛሬም «ግንቦት 20 ያስገኘ ልን ፍሬዎች» እያልን የሚሸሽ ፍሬ ጨብጠን፣ የነመ ራውን ፍሬ ከርቀት አሻግረን እያየን እንዳለን አለን፡፡ እናም መልኩን ቀየረ እንጂ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ጉዳይ ዛሬም ዋጋ ያስከፍላል፤ ስለሆነም ዛሬም የተጻ ፈው ህገ-መንግስት እንዲከበር፣ አፋኝ አዋጆች እንዲ ሰረዙ፣ የተሻለ ስርዓት እንዲመጣ እንተጋለን፡፡ እናም ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ጥያቄ ገና አልተመለ ሰም! እናም ግንቦት 20 ወዲህ፣ ሀሳብን በነጻነት የመግ ለጽ መብት ገና ወዲያ...ወዲያ...ሩቅ ወዲያ ነው!

ግንቦት 20 የበላቸው ቀሺ ገብሩዎች

ወይንሸት ሞላ

ኢህአዴግ ታግዬ አስገኘኋቸው ከሚላቸው መብቶች መካከል አንዱና ሁሌም የሚያወራሉት የሴቶች መብት ነው፡፡ በተለያዩ ፎረሞች ያደራጃቸው አባላቱም ኢህአዴግ የሴቶች መብትን እንዳስከበረ ለማሳየት ተደራጅተው ዶሮ የሚያረቡትን፣ ድንጋይ የሚቀጠቅጡትን ሴቶች «ተጠቃሚነት» በመጥቀስ የፓርቲያቸውን ስኬት ሲያወድሱ መዋላቸው የዕለት ተዕለት ተግባር ነው፡፡

በእውነቱ ከባህልም ሆነ ከእምነት ጋር በተያያዘ ሴቶችን እንደሚጨቁኑ የሚወቀሱት የአረብ መንግስታት እንኳ ለሴቶች መብት መከበር በሚጥሩበት ወቅት ሴቶች ድንጋይ ስለፈለጡና ሌሎች አድካሚ ስራዎችን ስለሰሩ የሴቶችን መብት አስከብሬያለሁ የሚለው ዝባዝንኬ ውሃ የሚቋጥር ሊሆን አይችልም፡ ፡ በ1960ዎቹ ትውልድ ሴቶች የማይናቅ ተሳትፎ እንዳደረጉ እነ ማርታን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡ ፡ ደርግ በሚያፍነው ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሴቶች መብት ተለይቶ የተነፈገበት ጊዜ አልታየም፡፡ ኢህአዴግ ግን ራሱን ከደርግ ጋር በማወዳደር የተሻለ መብት እንደፈቀደ የሚገልጸው የቱን እንደሆነ በግልጽ አይጠቀስም፡፡

ሆኖም የሴቶችን መብት አስከብሬያለሁ ድስኩር በወቅቱ ያለውን ዘርፈ ብዙ ጭቆና ለመሸፈን ካልሆነ በእውነታው የምናየው አይደለም፡፡ በህወሓት/ኢህአዴግ ትግል ውስጥ በርካታ ሴቶች መሳሪያ አንግተው ስርዓቱን አዲስ አበባ ድረስ ሸኝተውታል፡ ፡ እንደ አረጋሽ ያሉት በፖለቲካ ልዩነት ስርዓቱን ጥለው ሲወጡ ሌሎቹ ደግሞ የረባ ቦታ ሳይሰጣቸው በሌለ መስክ ሲሰማሩ ስልጣኑ በወንዶች ቁጥጥር ስር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ህወሓት ጋር ታግለው ስልጣን ላይ ከወጡት ይልቅ ጦር ሜዳ ላይ እያሉት የተሰዋቸው ቀሺ ገብሩ በርካታ ሰዎች ያውቋታል፡ ፡ መቼም በህወሓት/ኢህአዴግ የትጥቅ ትግል ከቀሺ ገብሩ ውጭ ሌላ ቆራጥ ታጋይ ጠፍቶ ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቁን በህይወት ያሉትን ቀሺ ገብሩዎች ቦታ እንዳልተሰጣቸው ግልጽ ነው፡፡ ቀሺ ገብሩም ብትሆን ስለሞተች እንጂ በህይወት ብትኖር ይህ ነው የሚባል ቦታ ልታገኝ እንደማትችል አሁን ኢህአዴግ ካለው ተሞክሮ ለመረዳት ቀላል ነው፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ ለግንቦት 20 ያደረሱትን ሴቶች እንኳ የሚገባቸውን ክብርና ስልጣን ያልሰጠው ገዥው ፓርቲ የሴቶችን መብት አስከብሬያለሁ ቢል ከተለመደው ፕሮፖጋንዳ ያለፈ አይሆንም፡፡

በተቃራኒ ጎራ የሚገኙት የፖለቲካ ቡድኖችና አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሴቶችን ስናይ ደግሞ ጭራሹን መሬት ላይ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን እንደያዘ ጀምሮ መልካም መልካም የሚባሉትን የዴሞክራሲና የነጻ ገበያ መርሆች ለአገራችን ህዝብ እንዳይደርሱ ሲከለክል የአገራችንን ባህል የሚጎዳውን ግን በሩን ከፍቶለታል፡፡ በደርግና በኋይለስላሴ ወቅት ሲወዝና

ወደ ገፅ 10 ዞሯል ...

ግንቦት 20ና የእምነት ነፃነት

ብርሃኑ ተክለያሬድ

በየአመቱ የግንቦት 20 ሰሞን የኢትዮጵያ ቴሌቪ ዥን ስቱዲዮ የጦርነት አውድማ ይመስላል፡፡ ፕሮ ግራሞቹ በሙሉ ጦርነት ጦርነት የሚሸቱ፣ ዜናዎቹ ሁሉ ‹አንዳንድ› ነዋሪዎች ግንቦት 20 ያመጣላቸውን ትሩፋት የሚመሰክሩባቸው ይሆናሉ፡፡ ታንክ እሳት ሲተፋ፣ ከጦር ኃይል ጀቶች እሳት ሲዘንቡ፣ ጓድ መን ግስቱ ኃ/ማርያም በወኔ ሲቁነጠነጥና ሲቃ በተሞላው ሁኔታ ጦሩን ሲቀሰቅስ ቁምጣ ለባሾቹ ወጣቶች ከባድ መሳሪያ ተሸከመው ሲሮጡ ብቻ ምኑ ቅጡ ኢ.ቴ .ቪ የጦር አውድማ መስሎ ይከርማል፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ ውጥንቅጥ ብባ ለራዕዩ መሪ ንግግርና ህወሓት/ ኢህአዴግ የእምነት ነፃነት መብት ማረጋገጡን በሚ ያሳዩ የመዘምራን ሽብሽባ፣ የረመዳን ሶላትና የፓስተ ሮች ስብከት ይጠናቀቃል፡፡ ይህ አመታዊ የግንቦት ወር የተለመደ የኢ.ቴ.ቪ. ፕሮግራም ነው የዛሬው ፅሁፌም የሚያጠነጥነው፡፡ ነፃ አውጪዎቹ እንደሚ ሉት ከግንቦት 20/1983 ዓ.ም ወዲህ የእምነት ነፃነት መብት በአግባቡ ተከብሯል ወይስ አልተከበረም? በሚለው መጠይቃዊ ሀሳብ ላይ ያጠነጠነ ሲሆን ይህንን መጠይቅ ለመመለስ እንዲረዳን የተለያዩ የእ ምነት ተቋማት ድህረ ግንቦት 20/1983 ዓ.ም ያሉበ ትን ሁኔታ ለመዳሰስ እንሞክር፡፡

ኦርቶዶክስ፡-«የሀይማኖታችን ዋስትና ህገ መንግስታ ችን ነው!»

ነፃ አውጪዎቹ ገና ከመነሻቸው ‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ማዳከም› የሚል አቅድ በፕሮግራማቸው ቀርጸው ከመነሳታቸው ጀምሮ በትጥቅ ትግሉ ወቅትም ነፃ ባወጧቸው ወረዳዎች አብዮታዊ የቤተክርስቲያን መዋቅሮች ከመዘርጋታ ቸውም በላይ ታጋዮችን መነኮሳት አስመስሎ በየገዳ ማቱ በማስረግና ህዝብን በማስተባበር ድጋፍ ለማግ ኘትና ደርግን ለመጣል ቤተ ክርስቲያኒቷን በከፍተኛ ደረጃ እንደተጠቀሙባት የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡ ፡ ይሁንና ህወሓት/ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጣ ረበት ጊዜ ጀምሮ ቤተክርስቲያ ኒቷ በሁለት ሲኖዶስ ከመመራት ጀምሮ እስከ አስከፊው የነሳ መከፋፈልና ጉስቸነት ተዘፍቃ ትገናለች፡፡ በርግጥም እነዚህ ችግሮች አልነበሩም፡፡ የግንቦት 20 ፍሬዎች እንጂ፡፡

በዚህ ስሌት መሰረትም በየሀገረ ስብከቱ የሚገኙ አማንያን ካህና ትን በማግለልና ቀኖና በመጣስ ጭምር ቤተክስቲያኗን የስርአቱ መጠቀሚያ ከማድረግም አልፎ በቤተክርስቲያኗ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የስርዓቱ ባለስልጣናት ‹የነፍጠኞች ዋሻ፣ ‹የትምክተኞች መሰብሰቢያ› በማለት በድፍረት አማን ያኑንና ቤተ እምነቱን ሲሳደቡ ተስተውለዋል፡፡

የቤተክርስቲያኒቷ ካህናት ስለዶግማ ቀኖናና ህገ ቤተ ክርስቲያን ከማስተማር ይልቅ መንግስት አመጣሁት የሚለውን ልማትና ሌሎች ‹ለውጦች ሲሰብኩ ሰርክ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ጳጳሳት ይባስ ብለው ለአባይ ግድብ ያላዋጣ ኢትዮጵያዊ አይደለም ኢትዮጵያዊ ነቱ ተሰርዟል ይሉናል፡፡ የቤተክርስቲያኒቷ መዋቅር በቅዱስ ሲኖዶስ ከመመራት ይልቅ በደህንነቶችና ለመ ንግስት ቅርብ በሆኑ መበለቶች እየተዘወር ይገኛል፡፡

ታጋዮቹ ለቤተክርስቲያን አመጣነው የሚሉት ነፃነት ከቶ ምንድነው? ባሳለፍናቸው 23 አመታት ገዳማ ቶቿ በ«ልማት» ምክንያት ፈርሰዋል፡፡ አፅመ ቅዱሳን ፈልሷል፡፡ የበዓል ማክበርያ አደባባዮች ወደ አነስተ ኛና ጥቃቅን ሸቀጥ መሸጫ ተለውጠዋል፡፡ በበዓላት ወቅትም በበዓል ማክበሪያ ቦታዎች ላይ የ«ሀይማኖታ ችን ዋስትና ህገ-መንግስታችን ነው!» የሚል ፈጣሪን የሚያቃልል ፅሁፍ ይለጠፋል፡፡ «እምነታችንን አታ ርከሱ!» ብለው የጠየቁ አማንያንና መነኮሳት ተገድለ ዋል፡፡ ተሰቃይተዋል፡፡ ተደብድበዋል፡፡ ህወሓት/ኢህ አዴግ ለቤተክርስቲያን አለኝታ ሊሆኑ የሚችሉ ማህበ ራትን በሽብርተኝነት በመፈረጅ አባላቶቻቸውን ማሸ ማቀቅና ማስፈራራት ተያይዘታል፡፡ (የቤተ ክርስቲያኗ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የኦህዴድ ስራ አስፈፃሚ አባል በሆነና ኦህዴድን ወከሎ የፓርላማ አባል በሆነ ግለሰብ ስራ አስኪያጅነት መመራቱም ለዚህ አንድ ማሳያ ነው፡፡) ይህ ዘመን ለቤተክርስቲያኒቱ ከዲዮቅል ጥያኖስ ዘመን የሚለየው በምን ይሆን? (ድዮቅልጥያ ኖስ በክርስትና ታሪክ አማኞችን በመጨፍጨፍ ወደር የማይገኝለት ንጉስ ነበር፡፡)

ፕሮቴስታንት፡- «ኢየሱስ ጌታ ነው፣ ኢህአዴግም...»

በቅርቡ መንግስት በሰራው አንድ ዶክመንተሪ ፊልም ላይ አንድ የፕሮቴስታንት ፓስተር፣ «በደርግ ዘመን ኢትዮጵያ ትቅደም ማለት ይቻል ይሆናል እንጂ ኢየሱስ ጌታ ነው ማለት አይቻልም ነበር» በማለት መናገራቸውን አስታውሳለሁ፡፡ ከፓስተሩ ገለፃ በተ ጨማሪም ብዙዎቹ የእምነቱ መሪዎች እንደሚናገ ሩት በቀድሞው ስርዓት በነፃነት ማምለክ በመከልከ ላቸው መፀዳጃ ቤት ጭምር ተደብቀው ያመልኩ እን ደነበር ይናገራሉ፡፡ በርግጥም ኢየሱስ ጌታ ነው ማለት እንደ ወንጀል የሚቆጠርበት ዘመን አልፏል፡፡ ይሁን እንጂ «ኢህአዴግ ጌታ ነው!» የሚለውን ቃል በተጓ ዳኝ እንዲነገር ያልተፃፈ ህግ ተደንግጓል፡፡ እውነተ ኞቹ የእምነቱ ተከታዮች እስኪሸማቀቁ ድረስ በየማ ምለኪያ ቤቱ ስለትራንፎርሜሽኑ መሳካት ይፀለያል፡ ፡ ትንቢት ተናጋሪ ነን የሚሉ ልማታዊ፣ ነቢያት፣ ህወሓት ህዝቡን ለረጅም ዘመናት እንዲገዛ ከአምላክ እንዲታዘዝ የሚገለፅ ልማታዊ ትንቢት ይናገራሉ፡፡

ህዝቡ በረሃብና በኑሮ ውድነት እየተሰቃየና ተስፋ ቢስ እየሆነ በመጣበት ዘመን በከፍተኛ የመንግስት ባለስል ጣናት የተጋበዙ ‹ተአምር አድራጊ› ሰዎች በኪሳቸሁ ያለውን ገንዘብ እናበዛለን፣ ቦርጭ እናጠፋለን በማለት ይሳለቃሉ፤ የቤተክርስቲያን እውነተኛ አማኞች እምነ ቱን የሚፃረር ተግባር ለመቃወም አቅም አጥተው በዝ ምታና በሀዘን ከአምላካቸው ጋር ብቻ በመነጋገር ላይ ተጠምደዋል፡፡ ይህ ተግባር በእምነቱ ላይ በደርግ ጊዜ ከነበረው ጫና በምን ይለይ ይሆን?

ህወሀት ገና አዲስ አበባ በገ ባበት ወቅት የመጀመሪያው ተግባሩ ያደረገው የወቅቱን ፓትርያርክ በጫናና በማስ ፈራራት ከሀገር እንዲወጡ ማድረግና የስርዓቱ ቀኝ እጅ የሆኑ መነኩሴን ወደ ፓትር ያርክነት በማምጣት ቤተክ ርስቲያኗን በቁልፍ የስርአቱ ሰዎች መሙላት ነበር፡፡

እስልምና፡- «ሂጃብ እንደ ወንጀል»

የእስልምና እምነት በህወሓት የስልጣን ዘመን የተፈ ጠረ ይመስል ስለ እስልምና እምነት በተነሳ ቁጥር ነፃነ ትን ያመጡት እነሱ መሆናቸውን የሚነግሩን ታጋዮቹ በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በእስልምና እምነት ላይ ያላቸውን አቋም ግልፅ እያደረጉ መጥተዋል፡፡

በትጥቅ ትግሉ ወቅት የሌላ እምነት ተከታዮችን የሙ ስሊም ስም በመስጠትና ሙስሊም በማስመሰል ከአረብ አገራት ድጋፍ ለማግኘትና ህዝቡን ለማነሳሳት የተጠቀመበት ቢሆንም ህዝበ ሙስሊሙ ለዘመናት ያዳበረው አንድ ሆኖ መኖር ስጋት የሆነበት ህወሓት ህዝበ ሙስሊሙ ለማከፋፈል ከሙስሊም አስተም ህሮ ውጪ የሆነ ሌላ እምነት በማምጣት በህዝበ ሙስሊሙ ላይ የስርዓቱ ቀኝ እጅ በሆኑት የመጅሊስ ተመራጮች አማካኝነት በሃይል ለመጫን የሞከረ ቢሆንም የአማኙ አንድነት ለዚህ እኩይ አስተሳሰቡ ሊመቸው ባለመቻሉ በህዝበ ሙስሊሙ ታሪክ ደርሶ የማያውቅ ግፍ እየደረሰበት ይገኛል፡፡

ዛሬ «መጅሊሶችንን የመምረጥ መብታችን ይከበር!» ብሎ መናገር እንደ ከፍተኛ ሽብር ተቆጥሮ ህዝበ ሙስሊሙ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚሳሳላቸው መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎች በመንግስት ዘግናኝ ግፍና ስቃይ ደርሶባቸዋል፡፡ በቅዱሱ የሮመዳን በዓል እለት ሰላማዊ በሆነው ህዝበ ሙስሊም ላይ ደም በተጠሙ ደብዳቤ ዎች ውርጅብኝ ደርሶበታል፡፡

የእስላም ህግ በሚያዘው መሰረት ሂጃብ የሚለብሱ ሙስሊም ተማሪዎች ያለምንም ወንጀል ሂጃብ በመል በሳቸው ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው ተባረዋል፡ ፡ በቡድን ሶላት የሰገዱ ተማሪዎች መኖሪያ ማዕከላዊ እስር ቤት ሆኗል፡፡ ከቶ እንዲህ አይነት ሰቆቃ በሙስ ሊሙ ታሪክ ተፈፅሞ ያውቅ ይሆን?

እንደመውጫ

ይህ ከላይ የተዘረዘረው በተለያዩ ቤተ እምነቶች ላይ የደረሰው ጭቆና «የእምነት ነፃነት መብት ለማስከ በር ታግለናል» በሚሉት ነፃ አውጪ ነን ባዮች ዘመን የተፈፀመ ነው፡፡ ከእነዚህ ቤተ እምነቶች መካከልም ሙስሊሙ ማህበረ ሰብ ከሚያካሂደው ፍፁም ሰላማዊ ትግል ውጪ በሌሎች ቤተ እም ነቶች ላይ የሚደረ ገውን ጣልቃ ገብነ ትና ተፅዕኖ አማኙ ማህበረሰብ ሲታ ገለው ብዙም አይ ታይም፡፡ ይህ አካ ሄድም ህዝቡ በእ ምነት አባቶቹ ላይ እምነት እንዲያጣና ለእምነቱ ትኩረት እንዳይሰጥ ከማድረ ጉም በላይ ኢአማኒነት እንዲስፋፋና ማህበራዊ ቀውስ እንዲፈጠርም ያደርጋል፡፡ እናም ይህ ጭቆና ተባብሶ ወደ አስከፊ ሁኔታ ከመለወጡ በፊት የሁሉም እምነት ተከታዮችና የእምነቶቹ መሪዎች እውነትን ብቻ መሰረት ያደረገ ትግል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡ ፡ የእምነት አባት ሆኖና ስለማያልፈው መንግስት እየ ሰበኩ ከአላፊው መንግስት ጋር በመተባበር ህዝብን ለአስከፊ ጭቆና መዳረግ በመንፈሳዊም ሆነ በዓለማዊ ህግ እጅግ አስነዋሪ ተግባር መሆኑን ሊረዱ ይገባል፡፡ ሃይማኖቱን ቀደምት አባቶች ያቆዩት በመራር መስዋ ዕትነትና በቆራጥነት መሆኑም መዘንጋት የለበትም፡፡

በመጨረሻም ግንቦት 20 ለሀይማኖቶች ያመጣው ጭቆናን፣ ጣልቃ ገብነትንና ተፅእኖን እንጂ ነፃነትን አለመሆኑን የሁሉም እምነት ተከታይ አውቆ ከዝምታ ድባብ በመውጣት «ነፍሳችሁን የሚገለውን ሰማያዊ አባታችሁን እንጂ ስጋችሁን የሚገድሉ ምድራዊ ዛዥዎ ችን አትፍሩ» የሚለውን አምላካዊ ቃል መሰረት በማ ድረግ ሰላማዊ ትግሉን ይቀላቀሉ ዘንድ እመክራለሁ፡፡

እለ ትነብሩ ተንስኡ (የተቀመጣችሁ ተነሱ)፡፡

ስሞታ

የኢትዮጵያ ህዝብ ይወቅልኝ!

እታገኝ መኮንን ካሣ

እኔ ወ/ሮ እታገኝ መኮንን ካሣ አድራሻ፡- አዲስ አበባ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 760/ሀ ነዋሪ ነኝ፡፡ በአሁኑ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ከላይ ቁጥሩ በተገለፀበት ቤት ከ40 ዓመት በላይ ተከ ራይቼ ስኖር በ1990 ዓ.ም በኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ መያዜን አወኩ፡፡ ቤቴንም ሆነ ልጆቼን እን ዲጠብቅልኝና እንዲረዳኝ በማለት ከ1994-1997 ዓ.ም ድረስ በውክልና ሰጥቸው የነበረ ሲሆን ከ97 በኋላ ግን ውክልናውን ትቶ የራሱን ቤት ሰርቶ ሄዷል፡፡ ቤቱ እስከታሸገበት ጥር 12 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ለአቶ ደረጀ ጎዳና ከመንግስት ተከራይ በማስመሰል በቤት ቁጥር 760/ሐ በአቶ ደረጀ ስም የአንድ አመት (በ1998 ዓ.ም) የቤት ኪራይ በስማቸው ቀበሌ ሂዶ ከፍሏል በማለት እኔ ደካማና በሽተኛዋን የፍርድ ቤት ውሳኔ ነው በማለት ቤቴን ጥር 12 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በመ ድኃኒቴ እና በንብረቴ ላይ በማሸግ በእኔም ሆነ ቤተሰቦቼን ከፍተኛ ችግር ደርሶብናል፡፡

ሆኖም መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ.ም እኛን በፖ ሊስና በመሣሪያ ኃይል ከግቢ ውስጥ አስወጥተው ንብረቴን በሌለሁበት አውጥተው-ብኝ እኔ ስምንት ቤተሰቤን ይዤ ዕቃ ቤት እንድኖርና ግማሹ ንብረ ቴን ውጭ ተጥሎ ለዝናብምና ለፀኃይ እንዲጋለጥ በማድረግ ከፍተኛ ውድመት እንዲደርስብኝ አድ ርገዋል፡፡

በየደረጃው ላሉት የመንግስት አካላት በተደጋጋሚ አቤት ብለም ቤቴን ለፈለጉት ሠው ለመስጠት ሲሉ ያላደረኩትን አድራጎት እያቀረቡ ጥፋተኛ ነሽ

በማለት ለረዥም ወራት እያንከራተቱኝ መሄጃው ጠፍቶብኝ እገኛለሁ፡፡

ሁከት ስለፈጠሩብኝ ይወግድልኝ ጥያቄ ለፍርድ ቤት ባቀርብም የወረዳ 09 ቤቶች ልማት ፅህፈት ቤት የህሰት ማስረጃ እያቀረቡ ሁከት አልፈጠ ረም በማለት ውሳኔ ተሰጠብኝ፡፡ በበኩሌ በ2005 ዓ.ም ይግባኝ ብልም ወረዳውን መጥራት ሳያስፈ ልገኝ የተሠጠው ውሳኔ ትክክል መሆኑን አረጋግ ጭአለሁ፤ መልስ ሰጪውን መጥራት አያስፈልግም ብሎ መዝገቡን ዘግቶብኛል፡፡

እንዲሁም ሠው ሁልጊዜ ከማስችገር በማለት ትንሽዬ የሸራ መጠለያ አድርጌ ከስል ቸርችሬ የማድርባትን መጠለያ የደረጀ ነው በማለት ግቢው ውስጥ ሁለት ክፍል አድርገው ቀምተው ሰኔ 16/2004 ዓ.ም ለአስቴር መለስና ለጌታቸው መለስ የልማት ተነሺ ናቸው በማለት ሰጥተውብ ኛል፡፡ አሁን ደግሞ የምኖርበትን ከመንግስት በየአ መቱ የምዋዋልበትን ቤት ለኃይልና ለውኃ ልማት በፃፉት ደብዳቤ ቤቴ መሆኑን በማመልከቻ ላይ ገልጸውልኛል፡፡ እኔ እታገኝ መኮንን በየካ ክ/ከተማ በወረዳ 09 መንግስት ቤት ቁጥር 760 ነዋሪ መሆኔን በ 26 ዝውውር 2006 እስከ ዛሬ እኖ ርበት የነበረውን መኖሪያ ቤት ለልማት ተነሺዎች የተሰጠ መሆኑን በደብዳቤያቸው አረጋግጠዋል፡ ፡ እኔ የ63 አመት አዛውንት የሙት ልጆች ይገቼ ብርድና ፀሀይ እየተፈራረቀብኝ እገኛለሁ፡፡ ስለሆ ነም የኢትዮጵያ ህዝብ ይፍረደኝ እላለሁ!

ፖለቲካ

ግንቦትና ግንቦታውያን

ጌታቸው ሺፈራው

ግንቦት በሞቃታማው በጋ እና በክረምቱ መካከል የሚገኝ የሙቀትና የወበቅ ወር ነው፡፡ ይህ ወር አየር ንብረቱ በቅጡ የማይታወቅ፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ የሚፈራረቅበት እንደመሆኑ ለሰዎች ጤና ተስማሚ አይደለም፡ ፡ ሙቀትና ቅዝቀዜው ድብልቅልቅ ባለበት በዚህ ወር አብዛኛው አርሶ አደር በበሽታ ይጠቃል፡፡ በዝናብ እጥረትና በረዥሙ በጋ ምክንያት ከብቶቻቸው ያልታሉ፡፡ በአጠቃላይ ግንቦት ለአብዛኛው ኢትዮጵያውያን የመከራና የስቃይ ወር ነው፡፡

ይህንንም ተከትሎ ኢትዮጵያውያን ወሩን መልካም ነገር ይዞ እንዲመጣ አምላካቸውን ይማጸናሉ፡፡ ለአብነት ያህል ከርስቴያኖችና የሌሎች እምነት ተከታዮችም የግንቦት ልደታ ዕለት (አብዛኛዎቹ ከእምነት ይልቅ አምልኮ አዊ ያደርጉታል) ንፍሮ አንፍረው፣ ቡና አፍልተው የግንቦት ወር ጦስ በጭስና በንፍሮ ውሃ ለመሸኘት ይጥራሉ፡ ፡ ሆኖም ግን ለኢትዮጵያውያን ግንቦት የመከራ ዘመን፣ የደም ወር ከመሆን አላለፈም፡፡ ከዚህ ወር ጦሶች መካከል ለአሁኑ ዘመን መከራ ምንጭ የሆኑትን ግንቦታዊ ከስተቶች ብቻ እጠቅሳለሁ፡፡

25 አመታትን ወደኋላ ስንመለስ ኢትዮጵያ ለአሁኑ ፖለቲካዊ፣ ጂኦ ፖለቲካዊና ሌሎች አሉታዊ ገጽታዎች የዳረጋትን ውጥንቅጥ እናገኛለን፡፡ ግንቦት 8/1981 ዓ.ም፡፡ ይህ ወቅት የኢትዮጵያ ወታደሮችና አመራሮቻቸው በጦርነት የተማረሩበት ወቅት ነበር፡፡ ከጀኔራሎቹም በላይ በእነ መንግስቱ ኃይለማርያም ይሁንታን ያገኘ ካድሬ ስለ ወታደራዊ ስትራቴጅ ለመተንተን የሚቃጣበትና ጀኔራሎቹን ያማረረበት ወቅት እንደነበር በርካቶች እማኝነ ታቸውን ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር የመንግስቱ ኃይለ

ማርያም አምባገነንነትና ከድርድር ይልቅ ጦርነትን ያስቀደመ ስልት ሰራዊቱንና አመራሮቹን አሰላችቷል፡፡ በገፈፋና በግድ ጦር ሜዳ ይቀላቀሉ የነበሩ ወታደሮች በቁር ጠኝነት ይዋጋ የነበረውን ሰራዊት መንፈስ ቀይረውታል፡ ፡ ይህ ሁሉ ውጥንቅጥ ያሳሰባቸው የጦሩ መሪዎች መንግስቱ ኃይለማርያም ከስልጣን ካልተወገዱ ኢትዮጵያ የገባችበት ችግር ሊፈታ እንደማይችል አመኑ፡፡ «በጓድ መንግስቱ ኃይለማርያም»› ላይ ይሞከራል ተብሎ የማይታሰበውን መፈንቅለ መንግስትም ወጠኑ፡፡ አዲስ አበባና አስመራም የመፈንቅለ መንግስት መሪዎቹ ማዕከል ሆኑ፡፡

ሆኖም የአዲስ አበባው ማታ ላይ እንዲሁም አስመራው ደግሞ ከእንድ ቀን በኋላ ግንቦት 8/1981 ዓ.ም ከሽፈ፡ ፡ አዲስ አበባ ውስጥ ሙከራውን ያደረጉት ጀኔራሎች ራሳቸውን ገደሉ፣ ተገደሉ፣ ታሰሩ፡፡ አስመራ ላይ ደግሞ ግንቦት 9 የ102ኛ አየር ወለድ ክ/ጦር በምስራቅና በሰሜን የገጠማትን ጦርነት ሲመሩ የኖሩትን ጀኔራሎች ዓይናቸውን ጎልጉሎ፣ በየጎዳናው እየጎተተ፣ አንገታቸውን ቆርጦ ብቻ ወታደር በመሪዎቹ ላይ ብቻ ሳይሆን ጠላት በማረካቸው ላይ ሊያደርገው በማይታሰበው አረመኔያዊ ድርጊት አስመራን የደም አላባ አደረጋት፡፡ በመፈንቅለ መንግስት በአጠቃላይ ከ37 በላይ የጦሩ አመራሮች ታሰሩ፡፡ ከእነዚህ መካከልም 28 ጀኔራሎች፣ 20 በላይ ኮሎኔሎች፣ 20 በላይ ሻለቃዎች፣ 20 በላይ ሻምበሎች ይገኙበታል፡፡ ገንጣይ አስገንጣይ የሚባሉት ሳይቀሩ አንዳንዶቹ «የኢትዮጵያ መንግስት ቀኝ እጁን በግራ እጁ ቆረጠ!» ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ «ኢትዮጵያ የጦር መሃንዲ ሶቺን ገደለች፣ በላች» ብለው ጽፈውታል፡፡ በዚህ የመንግስቱ ኃይለማሪያም እርምጃ ምክንያት 270 ሺህ ያህል ኤርትራ ውስጥ የነበረው ሰራዊት አመራር አልባ ሆነ፡፡

መፈንቅለ መንግስቱ በከሸፈ በሁለተኛው ቀን ግንቦት 10 በርካታ የኢትዮጵያ ሰራዊት አመራሮች ሲገደሉ፣ ሲታሰሩና ከጦሩ ሲርቁ እንዲሁም ሰራዊቱም ሆነ አመራሩ ሞራሉ ሲላሽቅ ሻዕቢያና ህወሓት የኢትዮጵያን ሰራዊት ይዞት የነበረውን ሰፊ መሬት ማስለቀቅ ጀመሩ፡፡ ይህ ወቅት የኢትዮጵያ ሰራዊት እንደ ውጭ ወራሪ ያለ ርህራሄ የተጨፈጨፈበት ጊዜ ነው፡፡ ህወሓትና ሻዕቢያ የተማረከውን ሰራዊት ሳይቀር መሬት ላይ አስተኝተው በመድፍ ጨፍልቀውታል፡፡ ቁስለኛውን በጅምላ ሲፈልጉ ወደ ገደል፣ ሲፈልጉ ወደባህሩ አሊያም በጅምላ የጨፈጨፉበት ወቅትም ነው፡፡ ይህ ወር ኤርትራና ትግራይ በኢትዮጵያ ሰራዊት ደም የጨቀየበት ከፉ ቀን ነው፡፡

ይህ ግንቦት ያመጣው ጦስ የኢትዮጵያውያን እጣ ፈንታ በገንጣዮቹ እጅ እንዲወድቅ አደረገ፡፡ መንግስቱ ኃይለ ማርያም ለኢትዮጵያ አንድነት «አንድ ጥይትና አንድ ሰው» አስኪቀር እንደሚዋጉ ቃል ገብተው እንደነበር ይነገራል፡፡ በእርግጥ እርሳቸው ብቻ ሳይሆን ሌሎችም መንግስቱ ኃይለማርያም ኢትዮጵያን ጦርነት ውስጥ ዘፍቀው መሸሽት እንደሌለባቸው በአደባባይ ነግረዋቸዋል፡፡ ለአብነት ያህል በመጨረሻው ሽንጎ አንድ የህይማኖት መሪ መንግስቱ ኃይለማርያም አጣብቂኝ ውስጥ የከተቱትን ሀገርና ህዝብ ጥለው መሄድ እንደሌለባቸው በግልጽ እንዲህ ብለዋቸው ነበር፡፡ «....50 ሚሊዮን ህዝብ በጦርነት ባህር ማግደው፣ ቆስቁሰው፣ በእርስበዎ ኃላፊነት 18 ዓመት ሙሉ መርተው ሳያደራድሩ፣ ሳያረጋጉ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ለአሳት ዳርገው፣ በአሁኑ ሰዓት ከመሞት በስተቀር፣ የቴዎድሮስን ጽዋ ከመጠጣት በስተቀር፣ ሌላ እድል የለዎትም፡፡ እንደሌሎች መሪዎች ኢሮፕ ይፈረጥጣሉ ብዬ እምነት የለኝም፡፡ እግዚያብሄር ምስክሬ ነው፡፡ ይህን ህዝብ አጋልጠው ይሄዳሉ አልልም፡፡ መንጊ፤ ከሷ ወንበር ላይ እንደቋንጣ ደርቀው እንደሚቀሩ አምንበዎታለሁ፡፡ ይህንን ባያደርጉ ግን ታሪክ ይፋረድዎታል፡፡»

በዚያ የህይማኖት መሪዎች ስለ እውነት ይናገሩ በነበረው ወቅት ከንግግራቸው ሁለት የግንቦት ጦሶችን በግልጽ እንረዳለን፡፡ እንደኛውና ዋነኛው ፕሬዝደንት መንግስቱ የፈጠሩትን ቀውስ «....50 ሚሊዮን ህዝብ በጦርነት ባህር ማግደው፣ ቆስቁሰው፣ በእርስበዎ ኃላፊነት 18 ዓመት ሙሉ መርተው ሳያደራድሩ፣ ሳያረጋጉ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ለአሳት ዳርገው፣» ሲሉ መንግስቱ ኃይለማሪያም የፈጠሩትን ቀውስ በግልጽ ተናግረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ «ይህን ህዝብ አጋልጠው ይሄዳሉ አልልም፡ ፡» ሲሉ ህወሓትና ሻዕቢያ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ያህል ጠላት እንደሆኑ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ነገር ግን የመንግስቱ «አንድ ጥይትና አንድ ሰው እስኪቀር እንዋጋለን!» ፉከራና የህይማኖት መሪው ንግግር ግንቦት 13/1983ን አላለፈም፡፡

ግንቦት 13/1983 ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ እነ መንግስቱ ሲደነፋብት የነበረው ሚዲያ «ጦርነቱ ያስከተለውን ሁኔታ እንዲለወጥ በልዩ ልዩ ወገኖች በልዩ ልዩ መልክ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ሆኖም ችግሩ አልተቃለለም፡፡ ስለዚህ ደም መፋሰስ እንዲቆም፣ ስምምነት እንዲሰፍን በልዩ ልዩ ወገኖች የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃ/ማርያም ከስልጣን መውረዳቸው እንደሚበጅ የታመነበት ስለሆነ ይህንኑ በማመዛዘን ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃ/ማርያም በዛሬው ዕለት ከስልጣን ወርደው ከኢትዮጵያ ውጭ ሄደዋል፡፡ ፕሬዝዳንቱ ከስልጣን በመውረድ ሀገር ለቀው በመሄዳቸው የሪፐብሊኩ ም/ፕሬዘዳንት ሌፍትናንት ጀኔራል ተስፋዬ ወ/ኪዳን ተክተው ይሰራሉ፡፡» ተባለ፡፡

መጀመሪያ ላይ ብላቴና ማሰልጠኛ ማዕከል በስልጠና ላይ የነበሩ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎችን ለመነጠፍት በሚል ካቀኑ በኋላ ማሰልጠኛው አካባቢ ሲደርሱ «የማ ልቀርበት ስብሰባ አለኝ» በሚል ወደ ኬንያ አቀኑ፡፡ ከዛም ወደ ዚምባብዌ፡፡ «ከመንግስቱ ኃይለማርያም አመራር ጋር ወደፊት!» ይል የነበር ካድሬ ደግሞ ጀርው ሊቀበለው የማይችለውን ነገር ሰማ፡፡ ለመንግስቱ ኃይለማርያም ቆም አመራሮቹን በጭካኔ ያረደው፣ በጭካኔ ዓይናቸውን ያወጣውንና አስከሬናቸውን በአስመራ ጎዳና የጎተተው ጨካኝ የ102ኛ ሰራዊት የመጨረሻው ተስፋውን ቆረጠ፡፡ «መንጊ!» ሲል የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ እጣ ፈንታው «ገንጣይ አስገንጣይ» ሲባሉና ኢትዮጵያን ሊገነጥሉ ሲታገሉ በኖሩት ሻዕቢያና ህወሓት ስር ሆነ፡፡ ሻዕቢያና ህወሓት በሚጠሏት ኢትዮጵያ ላይ የሚፈነጨበት መንገድ ወለል ብሎ ተከፈተ፡፡ ኢትዮጵያ በዚህ ጦሰኛ ግንቦት ወር አዲን ውስጥ ገባች፡፡

ይባስ ብሎ መንግስቱ ኃይለማርያምን የተኩት ተስፋዬ ወልደኪዳን መንግስቱ ጥሎ ከወጣበት ከሁለት ቀን በኋላ የኢትዮጵያ ጦር መሳሪያውን ለ«መንበዴ» አስረክበ ወደ ፈለገበት ቦታ እንዲሄድ አዋጅ አስነገሩ፡፡ ለአንድነት ሲዋጋ የኖረው ሰራዊትም መሳሪያውን እየጣለ ወደየትውልድ ቦታውና ወደ ከተማው ሲያቀና ለህዉሓትና ሻዕቢያ እንዲሁም በደርግ ለተማረረው አርሶ አደር ጥይት ሰለባ ሆነ፡፡ እንደ ምንም ብሎ ህይወቱን ያተረፈው ደግሞ በዚህ ደሙን ባፈሰሰላት አገር ጎዳና ላይ ወደቀ፡፡

ሰራዊቱ ትጥቁን እንዲፈታ በጊዜያዊ ፕሬዝደንቱ መጠ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል ...

እኛና አምባገነንነት

ደጀኑ ሳህሌ
E-mail:- ethiodsf@yahoo.com

"ተዘረፈ፤
ተዘርፎም ተገረፈ፡፡
ራሱ ተበደለ
ራሱ ተገደለ፡፡" (አቤ ጉበኛ፣ አልወለድም ገጽ 7)

ኢትዮጵያችን በእጅጉ የሚያሳማት አንድ እንግዳ (weird) የሆነ ጠባይ አላት፡፡ ጤናማ አስተሳሰብ ባዳበረ ማህበረሰብ ዘንድ የሚያሸልመዉ ስለሀገር ማሰብና መቆርቆር፤ የተበላሸዉን መተቸትና መመርመር በእኛ ዘንድ ውድ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ በእኛ ዘንድ ዘራፊ ሳይሆን ተዘራፊ በዘራፊዉ ይገረፋል፤ በእኛዋ ኢትዮጵያ ተበዳይ በበዳይ ይገደልባታል፡ ፡ የኛዋ ኢትዮጵያ እኔነቱን ትቶ ህመሟን ለማከም የሚዋ ትተዉን፣ እሷን ቀድሞ መሞትን የሚመርጠዉን የእዉነ ተኛ ልጇን ዉለታ መቁጠር ትታ ለሚሸጣት ሆድ አደር ልጇ መገበርን ትመርጣለች፡፡ ይህ ዘመን የተሻገረ እዉነ ትና እንግዳ ጠባይ ነው ዋናዉ ኢትዮጵያን የሚያሳማት፡፡

አቤ ጉበኛን እንደማሳያ እንጥቀስ፡- ደራሲ አቤ ጉበኛ በራሱ ብዕር እንደነገረን ኢትዮጵያ እርሱ በሕይወት በነበረበት በዚያን ዘመን ለገባቸበት ከባድ ችግር ያደረሳት የተበላሸ አስተዳደር መሆኑን ቀደም ብሎ የተረዳው፣ ኢትዮጵያ "በጨለመ የጊዜዉ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በጨለመ የወደፊት እድል" ላይ እንደምትገኝ ዘመንን ተሻግሮ ከፉቅ መመል ከት የቻለ የዘመኑ ቀዳሚ ነበር፡፡ ስለሆነም የወቅቱ የተበላሸ ስርአት በዚያዉ መቀጠል ስለሌለበት ለማስተካከል እና የተሻለ አስተዳደር ለመፍጠር ስርአቱን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ስህተቱን የተቸ፣ ህዝብን ለመብቱ ሲያነቃና ለህዝብ ስቃይ ደረቱን ሲደቃ የኖረ የድርሻዉን ለመወጣት የደከመ በዚያም ብዙ እንግልትና ግዞት ሲደርስበት የኖረ ነዉ፡፡

አቤ ለጨቋኙ ስርአት አጎብዳጅ፣ የግል ጥቅሙን አሳዳጅ፣ የወጣበትን ህዝብ አናዳጅ ባለመሆኑ በግፍ ቢጋዝም፤ የመከራ መዓት ቢዘንበበትም የህዝብን ብሶት ተጋፊ፣ ሀገራዊ ለዉጥን ተጣሪ እዉነትን ተናጋሪ፡ ስርአቱን ሽንቋጭ የጥበብ ሰዉ ከመሆን አላገደዉም፡፡ እርሱ የመርህ ሰዉ ነበርና፡፡

ለእዉነት ካልቆመ እሰር ሲሉት ካሰረ
ሲበላሽ ካልተቸ እንዲታረም ካልመከረ
ለምን?ን ከረሳ ለሆዱ ካደረ
ስለፍትህ ሲባል መሳደድ ከቀረ

መማርም ከሰረ ፊደል መናቀረ፤ እንዲል ገጣሚ፡፡

አቤ የተጣባቸዉ ጥበብ የቀሰማት ፊደል ለእዉነት እዲቆም ስላስገደደች የህዝብ ጠበቃ መሆንን ስላስተማረችዉ እድሚዉን ሙሉ የወቅቱን የተጨማለቀ አስተዳደር ሲሞግት፣ ለሁሉም የምትሆን ኢትዮጵያ ከወዴት እን ደሆነች ሲያማትርና ሲመክር ገፍቶታል፡፡

ከዛሬ 40 አመት በፊት የነበረችዉ የዛኔዋ የነአቤ ዘመን ኢትዮጵያ በወቅቱ እንደነአቤ አይነቶቹን በነጻነት ማሰብ የሚፈልጉና የዜጋን እኩልነት የሚሰብኩትን፣ ስርአቱን ስለዝቅጠቱ የሚተቹትን አጥብቃ የምትጠላና ለሰብአዊ ህልዉናቸዉም እዉቅና የማትሰጥ እንደነበረች "... የእ ያንዳንዱ ሰዉ የግል ነጻነት ፈጽሞ የተዘነጋባት የመንግስት ስልጣን ያላቸዉ ብቻ ሙሉ ሰዎች ... ሆነዉ የሚታዩባት አገር ነበረች" ሲል ነግሮናል፡፡ በመጨረሻም ከማንነቱ ዉጪ ሌላ ሰዉ እንዲሆን የተመኙለትን አሻፈረኝ ብሎ እዉነትን እንደያዘ ለእዉነት መሞትን የመረጠ፤ ለገዢ ሳይሆን ለህዝብ ምስጢር በሆነ መንገድ የሕይወት ጉዞዉን የደመደመ ባለቅኔ፤ ደራሲና ገጣሚ ነበር፡፡

ዛሬስ? ከስርአቱ ያልወገኑና በወገናቸዉ መከራ ላይ ልባቸዉን ያላደነደኑ ተርታ ኢትዮጵያዊያን እንደሙሉ ሰዉ ተቆጥረዉ ሰዉ የሚያምረዉንና ለሰዉ የሚያስፈልገዉን እንዲጠይቁ ተፈቅዶላቸዋልን? በልቶ የማደር፣ የዜግነት እኩልነት፣ በነጻነት ማሰብ፣ ማምለክ የመሳሰሉትን ሰብአዊ መብቶችን ስለመጠቀም መብቱ አላቸዉ? የስርአቱ መበላሸት፣ የዜጎች በጠነ ከሰዉ ተርታ ወርደዉ ከቆሻሻ ገንዳ ምግብ ፍለጋ መዋተት፣ የሰብአዊ ነጻነት መጥፋት አሳስቧቸዉ ስርአቱን ለመተቸት ብዕራቸዉን ላነሱ ዜጎች የምትሰጠዉ ምላሽ ምን ሆኖ ይሆን? የዛኔ ከነበረችበትና ከነተበ የዕለት ጨለማዊ የወደ ፊት እድል ተላቃ ብሩህ ነገን የምትጠብቅ ሀገርስ ሆና ይሆን? እኛ የዚህ ዘመን ዘመነኞች ኢትዮጵያ ቀድሞ ከነበረችበት በእጅጉ ያጓሊት ተጉዟ ለዘነጋቺ የማትመች ገህነም፤ በልቶ ማደር ብርቅ የሆነባት አሊያም በልቶ ለማደር ህሊና በማስዮገነት የሚቀርባበት መጻጉዕ ሆናለች እንላለን፡፡ ምክንያቱስ ቢሉ ዘ ኢኮኖሚስት የተባለዉ ነፍሳቸዉን ይማርና አቶ መለስ ለንባብ እንደሚመርጡት የነገሩን መጽሔት የእርሳቸዉን ሞት አስመልክቶ "The man who tried to make dictatorship acceptable" ሲል ያስነበበዉን ዘገባ ዋቢ አድርገን አምባገነንነት ቅቡል ስርአት እንዲሆን ሳይታክቱ የሰሩ አምባገነን ሰዎች ስለመሆት ነዉ ይሆናል መልሳችን፡፡

ወደ ገፅ 7 የዞረ ...

ተቃዋሚዎች ስለ ግንቦት 20 ይናገራሉ

ኢህአዴግ ስልጣን ላይ ከወጣ ድፍን 23 ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ በእነዚህ 23 ዓመታት ውስጥ ኢህአዴግ በሀገሪቱ በርካታ ለውጦችን እንዳመጣ ሲናገር ይደመጣል፡፡ በዚህም ስልጣን ላይ የወጣበትን ዕለት (ግንቦት 20) በየአመቱ ያከብራል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ግንቦት 20 ለኢትዮጵ ያና ኢትዮጵያውያን ያመጣው ተጨባጭ ለውጥ የለም ሲሉ በተቃውሞው ጎራ የተሰለፉት ይሞግታሉ፡፡ ለመሆኑ ግንቦት 20 ምን ለውጥ አመጣ? ከግንቦት 20 ማን ተጠቀመ? ቀጣይስ ምን መደረግ አለበት? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ ‹ነገረ ኢትዮጵያ› የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን አነጋግራለች፡፡

«ግንቦት 20 ህዝቦቻችን የታፈኑበት እንጂ ነጻ የወጡበት አይደለም»

አቶ አበባው መሐሪ፣ የመኢአድ ፕሬዚዳንት

እኛ ግንቦት 20 አመጣቸው የሚባሉትን ውጤቶች ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ይመሩት ከነበረው መዐሕድ ጀምረን ነው ስንቃወም የኖርነው፡፡ ግንቦት 20 ህዝቦቻችን የታፈኑበት እንጂ ነጻ የወጡበት ነው ብዬ አላስ ብም፡፡ አገራችን በዘርና በቋንቋ የተከፋፈለችበት፣ ወደ ውድቀት ያመራችበት ወቅት ነው ብዬ ነው የማስበው፡ ፡ ባለፉት 23 አመታት አገራችን ወደ ውድቀት እየተጓዘች እንደሆነ የታየበት ወቅት ነው፡፡ ግንቦት 20 ወደ ጨለማ እንጂ ወደ ብርሃን የመራን ለውጥ አይደለም፡፡

ከፌደራሊዝሙ ጋር በተያያዘ እኛ የምንቃወመው ኢትዮጵያውያን በቋንቋ እንዲከፋፈሉ ተደረጉ ነው እንጂ በቋንቋቸው በመናገራቸው አይደለም፡፡ በቋንቋቸው የመናገር መብታቸው መከበር አለበት፡፡ ወጋቸው፣ ባህ ላቸው፣ ቋንቋቸው መከበር አለበት፡፡ መከበር ሲባል ግን ከስርዓት ያለፈ መከበር አይደለም፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው ግጭት ከዚህ ስርዓት የቋንቋ ክፍፍል የመነጨ ሲሆን ኢትዮጵያውያን «ይህ የእኛ ነው፣ ውጡልን» እየ ተባሉ ነው፡፡

ግንቦት 20 የሚጠበቀውን ልማትም አላመጣም፡፡ በምጣኔ ሀብት መሰረት እድገት ሲባል ሁለት አይነት እድገት አለ፡፡ በእንግሊዘኛው «ግሮውዝ» እና «ደቨሎፕመንት» የሚባለው ነው፡፡ አንደኛው የሰው ሀይል ልማት (ሂውማን «ዲቨሎፕመንት») ሲሆን ሌላኛው የመሰረተ ልማት ነው፡፡ ከውጭ በሚያገኙት እርዳታም ይሁን በሌላ መንገድ ህዝቡን ያሳተፈ ባይሆንም የተወሰነም ቢሆን እድገት አለ፡፡ ይህም ቢሆን ልማት የለም፡፡ ህዝቡ በኑሮ ውድነት እየተጠበሰ ይገኛል፡፡ ሌላው ችግር የሰብአዊ መብት ችግር ነው፡፡ እኔ የምሰጥህን አየር ካተነ ፈስክ፣ እኔ የምሰጥህን አመራር ካልተቀበልክ በራስህ ልትሄድ አትችልም በሚል አስሮ እየገዛ ነው የሚገኘው፡ ፡ እንደ እኔ ይህ በራሱ ውድቀት ነው፡፡ መሆን ያለበት ዜጎች በራሳቸው እምነት ወይንም በራሳቸው አካሄድ መራመድ አለባቸው፡፡ ያለ በለዚያ ግን እሱ ለከቶ በሰጣቸው ከሆነ እንዲሄዱ የሚፈለገው ትልቅ አፈና ነው፡፡ በአገራችን እየተደረገ ያለው ይህ አይነት አምባገነናዊ ተግባር ነው፡፡ ይህ ትልቅ ውድቀት ነው፡፡ ዛሬ ጋዜጠኛ እንደ ልቡ መረጃ ማግኘትና መጻፍ አይችልም፡፡ ከጻፈም ደግሞ ሽብርተኛ ነው የሚባለው፡፡ እነዚህ ነገሮች በአ ጠቃላይ ዴሞክራሲውን አጨልመውታል፡፡

በሌላ በኩል ለምሳሌ በሱዳን ድንበርን ያየን እንደሆነ የአገራችን አንድነት ተደፍሯል፡፡ ይህ የአንድነታችን መደፈር ግንቦት 20 ያመጣው ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ መሰናክሎች ይመስለኛል፡፡ ከግንቦት 20 ማን ነው የተጠ ቀመው የሚለው ግልጽ ነው፡፡ በጎሳ የተደራጁና ከሻቦው ፓርቲ የወገኑ፣ ከሁሉም ጎሳ የዘር ማጥፋቱን፣ የመ ዝረፉን፣ ሙስናውን ያየን እንደሆነ ከሻቦው ፓርቲ ጎን ከሆነ አገርን በቁንጮው ቢያቆም አይከሰስም፣ አይያ ዝም፡፡ የእነሱን አላማና ሂደት ያልደገፈ ከሆነ ግን ተጎጅ ይሆናል፡፡ ከግንቦት 20 የተጠቀሙት በጎሳ ተደራጅ ተው ከሻቦው ፓርቲ ጎን የተሰለፉት ብቻ ናቸው፡፡ ዛሬ ሚሊየነር የሆኑት የሻቦው ፓርቲ ደጋፊዎች ናቸው፡፡ ላባቸውን አንጠፍጥፈው የሰሩ ኢትየጵያዊያንና ቀሪው ዜጋ ከግንቦት 20 የተጠቀመው ነገር የለውም፡፡ እነዚህ ነገሮች ህዝባችንንና አገራችንን አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ከተዋል፡፡ በዚህ ሰሞን የጸረ ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት በቢ ሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንደተበላ አሳይቷል፡፡ ተበላ እንጂ ተመለሰ ተብሎ አያውቅም፡፡ ይህ የኢህአዴግ አካላት ስለሆኑ እንጂ ሌላ ሰው ላይ ቢሆን የ10ና 20 ብር ጥፋት ያሳስር ነበር፡፡

በእኛ በኩል ግንቦት 20 አመጣቸው የሚባሉት ነገሮች ለአገራችን ጠቃሚ አይደሉም ብለን እየታገልን እንገኛ ለን፡፡ አንድ ፓርቲ ፕሮግራም ቀርጾ ሲቋቋም ያለው መንግስት ትክክለኛ አይደለም ብሎ ስህተቱን እንዲያርም ጫና ማሳደር፣ ካላረመም ስልጣኑን እንዲለቅ ግፊት ማድረግ ነው፡፡ መኢአድም በዚህ ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ የሚገኝ ፓርቲ ነው፡፡

«ሥርዓቱ በከፋ ሁኔታ ወደኋላ ተመልሷል»

«ጥቂት የሥርዓቱ ተለጣፊዎች ተጠቃሚ ሆነዋል»

አቶ ስለሺ ፈይሳ፣ የሰማያዊ ፓርቲ ም/ሊቀመንበር

እንደሚታወቀው ግንቦት 20 ኢህአዴግ ደርግን አሸንፎ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት ቀን ነው፡፡ እነሱ ፋሽስ ታዊ የሆነውን ስርዓት አስወግደን ለኢትዮጵያ ህዝብ ፍትህ፣ ነጻነትና ለወደፊትም የበለጸገች ኢትዮጵያን እናረጋ ግጣለን ያሉበት ቃል ኪዳን እንደሆነና የዚህንም መሰረት የጣሉበት አድርገው ነው የሚያቀርቡት፡፡ በእርግጥ በወቅቱ በርካታ ህዝብ ከዛ አስከፊ ስርዓት ወጥቶ የተሻለ ስርዓት እንደሚያገኝ ተስፋ ነበረው፡፡ ይህ ደግሞ በየ ጊዜው በሚደረጉ ህዝባዊ እንቅስቀሴዎችም የተወሰነ ድጋፍ እንደተሰጠው የሚታወቅ ነበር፡፡ በተጨማሪም በወቅቱ በርካታ የግል ጋዜጦችና መጽሄቶች ተፈቅደላቸው ህዝብ ሀሳቡን በነጻነት የመግለጽ ጅምር ታይቶ ነበር፡፡ በኋላ ፖለቲካዊ ስርዓት ወደ መመስረት ሲገቡ ግን የሚያሸማቅቅና የህዝብን ጥቅም የሚመልስ ሳይሆን የእነሱን ጥቅም የሚያስከብሩ እርምጃዎችን መውሰዳቸው በውል ታይቷል፡፡ በሽግግር መንግስቱ ወቅት በርካታ አስተዋጽኦ ያደረጉትን የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ጎን በመግፋት እነሱ የፈለጉትንና የመረጡን ብቻ አሰባስበው የራሳቸው ስርዓት ሲመሰርቱ በፊት ተስፋ አድርጎ የነበረውን ህዝብ ደግሞ ተስፋ አስቆርጠ ውታል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የማንከዳቸው አንዳንድ በትዝታ የቀሩ የኢህአዴግ አገልግሎቶች ነበሩ፡፡ እነዛ ግን በየ ጊዜው ከአመት ወደ አመት እየተሸረሸሩ መጥተዋል፡፡ እንዲያውም ካለፈው ስርዓት በከፋ ሁኔታ ወደኋላ የተመለስን ይመስለኛል፡፡

ፌደራሊዝም ማለት ራስን በራስ የማስተዳደር መብት የሚረጋገጥበት ነው፡፡ ኢህአዴግ ይህን ስርዓት በቅንነት ነው የመረጠው? የትኛውን የፌደራሊዝም ስርዓት ነው የመረጠው? ብለን ስናስብ ኢትዮጵያን በምታክል አገር ጎሳዎችና ሀይማኖቶች በጋራ ተከባብረው፣ በጋራ ለሀገር መስዋዕትነት ከፍለው፣ ደማቸውን አፍሰው በነባቢት አገር ውስጥ ለምን የጎሳ ፌደራሊዝም አስፈለገ? የሚለው ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ህዝብ ተከባብሮና ተባብሮ እንዲኖር ከማድረግ ይልቅ ህዝብ በጎሳ አስተሳሰብ አገሪቱን ከፋፍሎ፣ በተለይም ይህን ገዥ መደብን የሚመራው ህወሓት በራሱ ባለመተማመኑ ሌላው ህዝብ በየራሱ ታጥሮና ከሌላው ጋር ተፈራርቶ እንዲኖር፣ አንዱ ለሌላ ኛው ጠላት ሆኖ እንዲኖር የፈጠረው ስልት ነው፡፡ በተለይ አሁንም ድረስ የሚሰራው ፕሮፖጋንዳ አንዱ ሌላው አካባቢ ጋር እንዳይኖር፣ የሚኖረውም ተፈናቅሎ እንዲወጣ መንገድ የከፈተ በመሆኑ ግንቦት 20 አመጣው የሚ ባለው ፌደራሊዝም ለኢትዮጵያ መልካም ነገር አመጣ ብዬ አላምንም፡፡

ግንቦት 20 የህዝብን ተጠቃሚነት አረጋግጧል የሚሉትንም ከምን አኳያ? የሚል ጥያቄ ማንሳት ይገባል፡፡ ከልማት፣ ከኑሮ፣ መልካም አስተዳደር፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብትን ከማረጋገጥ አኳያ ናቸው የህዝብ ጥቅም የሚባሉት፡፡ በአሁኑ ወቅት ህዝብ እነዚህን ጥቅሞች እያገኘ አይደለም፡፡ በእርግጥ የተወሰኑ የህብረተ ሰብ ክፍሎች ጥቅም እያገኙ ስለመሆኑ መካድ አይቻልም፡፡ የኦሕዴን ፓርቲ ተጠግተው ስልጣኑን ለማስጠበቅ የሚያገለግሉና በኢኮኖሚ የተሳሰሩ መጅመሪያ ከምንም ተነስተው አሁን በርካታ ሀንጻና ገንዘብ ያላቸው አካላ ትን እናገኛለን፡፡ የእነዚህ የጥቂቶች ተጠቃሚነት ግን የህዝብን ተጠቃሚነት እንዳረጋገጠ ተደርጎ ሊቀርብ አይ ችልም፡፡ በአሁኑ ወቅት ህዝብ ተጠቃሚ እንዳልሆነ የዓለም አቀፍ ተቋማት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ አስ ቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው የሚያወጡት ሪፖርት ያሳያል፡፡ በርሃብ አደጋ ውስጥ ነው ያለነው፡ ፡ ይህ አገር ያወቀው ሀቅ ነው፡፡ በከተማም ሆነ በገጠር ያለው ህዝብ በልቶ እያደረ እንዳልሆነ ሁሉም ያውቀ ዋል፡፡ ኢህአዴግ የሚለው ሶስት ጊዜ መብላት ይቅርና አንድ ጊዜ እንኳን በልቶ ለማደር ተቸግሯል፡፡ የምግብ፣ የውሃ፣ የመብራት፣ የቴሌኮሚኒኬሽን፣ ወጣቱ ተስፋ ያጣበት የስራ ችግርና ሌሎቹን ስናይ ህዝብ አለመጠቀሙ ግልፅ ነው፡፡ ጥቂት የስርዓቱ ተለጣፊዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ግን እነዚህ ህዝብ እንደተጠቀመ ሊያሳዩ አይች ሉም፡፡ ብዙሃኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የመኖር ህልውናውን የተፈታተነ ነው፡፡

በፊትም ኢህአዴግ ራሱ ሲነሳ «ላረጋግጠው የምፈልገው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ነው!» ብሎ ነበር፡፡ ግን ይህን ማረጋገጥ አልቻለም፡፡ ዴሞክራሲ ማለት በህዝብ፣ ለህዝብና የህዝብ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መመስረት ነው፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ የሚሰራው ለእንዲህ ያለ ህዝባዊ ስርዓት መስፈን ነው፡፡ ይህ በሆነበት ስርዓት ደግሞ ህዝብ ወደ ስልጣን ያመጣቸውን ሰዎች መልሶ በህጋዊ መንገድ ማውረድ ይችላል፡፡ ህዝብ መሪዎቹን በሚሰሩት ሁሉ ይጠይቃቸዋል፡፡ ተቋማት ህዝብን እንዲያገለግሉ ይደረጋሉ፡፡ ለዚህ መፍትሄው ለህዝብ የሚቆም ዴሞክ ራሲያዊ መንግስት መመስረት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው ችግር የሚመነጨው ከስርዓቱ መሰረታዊ ባህሪ ነው፡ ፡ አምባገነናዊ በሆነው ኢህአዴግ ተጠያቂነት የሚታሰብ አይደለም፡፡ ህዝብ ለመሪዎች ስልጣኑን ሰጥቶ ስልጣ ኑን የሚነጥቀው ከሆነ የህዝብን ጥቅም ማስከበር ይችላል፡፡ ይህ በህዝብ የተመረጠ ስርዓት በስልጣን የሚቆየው ይህን ተጠያቂነቱን ሲወጣ መሆኑን ያምናል፡፡

አቶ ስለሺ ፈይሳ

«ከግንቦት 20 የተጠቀሙት ፖለቲከኞቹና ጀኔራሎቹ ናቸው»

«ግንቦት 20 ኢትዮጵያዊነትን በእጅጉ አደብዝዟል»

አቶ ሰለሞን ስዩም፣ የአንድነት ፓርቲ የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ

ሁል ጊዜ ግንቦት 20 ሲነሳ «መለስ ዜናዊና ወልደ ተንሳይ» የሚል መፈክር አለኝ፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ፣ ጠቅልሎ በአምባገነን ሓንሰ ርነት ሞተ፡፡ መለስ ዜናዊ ይንቀዋል የምንለው ነገር አይኖርም፡፡ በተመሳሳይ አንድ ወልደተንሳይ የሚባል በግንቦት 20 ‹ድል› አዲስ አበባ የገባ ሰው አለ፡፡ ይህ ሰው በትግሉ ወቅት እጆቹንና አይኖቹን አጥቷል፡፡ መለስ ዜናዊ ሁሉንም ነገር በጠቀለለበት ስርዓት ወል ደተንሳይ ምንም ነገር ስለሌለው በልመና ነው ህይ ወቱን የሚገፋው፡፡ ግንቦት 20 እንዲህ ያለ ጠርዘኛ ውጤቶች ያሉት ቀን ነው፡፡

ግንቦት 20 የኢትዮጵያን ህዝብ ተጠቃሚ ካለማድረ ጉም ባሻገር በትግሉ ወቅት የነበሩት ታጋዮች እንኳ አንደኛው ተጠቃሚ ሌላኛው ተጎጅ የሆነበት ቀን ነው፡፡ ህወሓቶች የትግራይ ህዝብ ላይ ትኩረት እን ዲጣልበት አደረጉ እንጂ ህዝብ ሳይሆን ተጠቃሚ የሆኑት ፖለቲከኞቹና ጀኔራሎቹ ናቸው፡፡ ወደ ቦሌ ወጣ ሲባል ይህ ህንጻ የጀኔራል እንትና ነው፣ ይህኛው ደግሞ የጀኔራል እንትና ነው ይባላል፡፡ ስለሆነም ጊዜ ያዊም ቢሆን ጥቂቶች ተደራጅተዋል፡፡ ይህ አይነት የተዛበ ጠቀሜታ የኢኮኖሚ ከፍፍል ፈንጅ የማጥ መድ ያህል አደገኛ ነው፡፡ ስለሆነም ግንቦት 20 ላይ ቁጭ ብለው ይህን ፈንጅ ያጠ መዱብን ያህል ነው የሚሰ ማኝ፡፡ የኢህአዴግ አምባገነኖ ችን ምንም አይነት የፖለቲካ ጽንሰ ሀሳብ አይገልጻቸውም፡ ፡ ምን አልባት ብልጣ ብልጥ አምባገነኖች ናቸው ልንላቸው እንችላለን፡፡ ዴሞክራሲያዊ ለመምሰል የሚሞክሩ ጠቅላ ዮች ናቸው፡፡

የእኔ ስጋት አሁን ግንቦት 20ን ተከትሎ የመጣው አፋኝነት ህዝብን አፍኖ፣ አፍኖ በመጨ ረሻ ነገሮች በምርጫ ሳይሆን በህዝባዊ እምብይተኝነት የሚፈነዱ ይመስለኛል፡፡ በዚህ አፋኝ ስርዓት ማህጸን ውስጥ በደንብ ሳንጠናከር እንዲህ አይነት ነገሮች ከተ ከሰቱ ስርዓት ማስያዝና ሌሎችም ስለሚኖሩ አስቸ ጋሪ ነገሮች ይፈጠራሉ ብዬ ነው የምሰጋው፡፡ ተቃዋ ሚዎች አሁን ባሉበት ሁኔታ ብዙም ለውጥ የመጣሉ የሚል ሀሳብ የለኝም፡፡ ለምሳሌ ያህል በ1992 ዓ.ም አዲስ አበባ በተደረገው ምርጫ ተቃዋዎች 71 በመቶ ድምጽ ነበራቸው፡፡ ኢህአዴግ 39 በመቶ ድምጽ ቢያገኝም ተቃዋሚዎች ይህን ወንበር በመከፋፈላ ቸው ኢህአዴግ አሸነፈ፡፡ የጋራ የሚያደርግ የፖለቲካ አጀንዳ ሳይኖራቸው ለውጥ ያመጣሉ የሚል እምነት የለኝም፡፡

ኢህአዴግ መብት ተከበረ ሲል እያንዳንዱን ብሄር ማንነት እንደ ነዶ አስሮ ነው፡፡ ዶክተር በድሉ ባለፈው እንደጻፈው አልተዋሃድንም፣ አልተቀላቀልንም፡፡ ኢህ አዴግ በየማንነት ደርድሮ «እኔ የተለየሁ ነኝ፡፡ ከዚህ ባህል ውስጥ በዛ ባህል ውስጥ የተቀነብብኩኝ ነኝ» እንዲል እያደረገ ነው፡፡ ይህም በአገራችን ግጭት እያ ስከተለ ነው፡፡ ግንቦት 20 ኢትዮጵያዊነትንም በእጅጉ አደብዝዟል፡፡ ይህን ስል ግን የድሮዋ ኢትዮጵያም ተሰርታ አልቃለች ለማለት አይደለም፡፡

«የትግራይ ህዝብ ከግንቦት 20 ተጠቃሚ አይደለም»

አብርሃ ደስታ፣ የአረና ትግራይ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ

አንድ ፓርቲ ስልጣን ሲይዝ የሚያከ ናውናቸው ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ለውጥ የለም ሲባል ምንም አይነት እንቅስቃሴ የለም ማለት አይደለም፡፡ ሁሌ መንግስት ቢኖርም ባይኖርም ለውጥ ይኖራል፡፡ ለውጥ ሊኖር የግድ ነው፡፡ አሁን መጠየቅ ያለብን ግን ያ ለውጥ በቂ ነው ወይ? የሚ ለውን ጥያቄ ነው፡፡ አሁን ኢህአዴግ መን ግስት መስርቷል፡፡ ከ20 አመት በላይ ስልጣን ላይ ቆይቷል፡፡ ጥያቄው ግን በዚህ ሁሉ ጊዜ ይህን ብቻ ነው መስራት የነበረበት የሚል ነው? ከዚህም በተጨ ማሪ ኢህአዴግ አሁን ሰራሁት የሚለውን በደርግ ዘመን ከነበረው ጋር እያወዳደረ ነው ሰራሁ የሚለን፡፡ የደርግ ዘመን የጦር ነት ጊዜ ነበር፡፡ አሁን ሰራሁ የሚለን በጦር ነት ተጠምዶ በነበረ ያለፈ ስርዓት ጋር አወ ዳድሮ ነው፡፡ አሁን ባለው አንጻራዊ መረ ጋጋት የተሻለ ነገር መስራት ይቻል ነበር፡፡ ስለዚህ አልሰራም ነው የምንለው፡፡

በሌላ በኩል አሁን የምናየው የመንገድና ተመሳሳይ የመሰረተ ልማት ግንባታ ከኢህአዴግ ብቃት የመነጨ ሳይሆን ድሮ በደርግ ጊዜ እንደነበረው ኢህአዴግን የሚያስቸገር ሌላ አማጺ ቡድን ስለሌለ የሚታይ ነው፡፡ አሁን ያለው አንጻራዊ መረጋጋት አሁን ኢት ዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚዎች ሰላማዊ ትግል መርጠው በሀሳብ ስለሚከራከሩና በጠመንጃ ባለመታ ገላቸው ችግር የሚያደርሱ ባለመሆናቸው ነው ትንሽ የሚሰሩ ነገሮች የሚታዩት፡፡ በደርግ ወቅት ህወሓት ራሱ ህገ ወጥ ድርጅት ነበር፡፡ ይህ ህገ ወጥ ድርጅት በተለያዩ ቦታዎች እየተንቀሳቀሰ ንብረቶችን በማው ደም፣ ባንኮችን በመዝረፍ፣ ያስቸገር ስለነበር ደርግ ብዙውን ጊዜውን ያሳለፈው ፀጥታን በማስከበር ነው፡ ፡ በመሆኑም በደርግ ጊዜ በጦርነቱ ምክንያት ብዙ አል ተሰራም፡፡ ኢህአዴግም ሰራሁ የሚለው ራሱን ከዚህ በጦርነት ተጠምዶ ከነበር ስርዓት ጋር በማወዳደር ነው፡፡ እኛ ግን የምናምነው የሚጠበቅበትን ያህል መስራት እንዳልቻለ ነው፡፡

ትንሽም ቢሆን ተሰራ የሚባለውን ካየን ልማት ሳይሆን መሰረተ ልማት ነው ያለው፡፡ አስፋልትን የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት ለውጦች አሉ፡፡ እነዚህም በውጭ እርዳታ የሚሰሩ ናቸው፡፡ በኢህአዴግ አቅም የሚሰሩ አይደሉም፡፡ ነገር ግን ልማት ፈጽሞ፣ ሙሉ በሙሉ የለም ማለት እንችላለን፡፡ ልማት አለ ለመባል ሶስት መሰረታዊ ነገሮች ሊኖሩ ይገባል፡፡ አንደኛው ኢኮኖሚያዊ እድገት መኖር አለበት፡፡ ሁለተኛው ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል መኖር አለበት፡፡ ሶስተኛው የህዝብ ነጻነት መኖር አለበት፡፡ ሆኖም ግን ነጻነት የለም፡፡ ዴሞክራሲ የለም፡፡ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል የለም፡፡ የተወሰኑ በቤተሰብ የተሰባሰቡ የመንግስት አካላት ከባለስልጣናት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያን ሀብት የሚዘርፉ ግለሰቦች ናቸው ተጠቃሚዎቹ፡፡

የትግራይ ህዝብ እንደተጎዳ ነው፡፡ አሁንም ብዙ ስቃይ አለበት፡፡ አሁንም ድረስ አብዛኛው ህዝብ በእ ርዳታ ነው የሚተዳደረው፡፡ በአዲስ አበባና በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚኖሩ ትግርኛ ተናጋሪዎች አሉ፡፡ እነዚህ ትግርኛ ተናጋሪዎች የባለስልጣናት ዘመ ዶችና ቤተሰቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ከሻዥዎቹ ጋር ባላቸው ቅርበት የያዙት ሀብት ልክ የትግራይ ህዝብ ሀብታም እንደሆነ ተደርጎ እንዲታሰብ አድርጎ ታል፡፡ እንጂማ የትግራይ ህዝብ በስርዓቱ ተጎጅ ነው፡ ፡ በአሁኑ ወቅት በትግራይ በርካታ ተቃውሞና ቅሬታ ነው ያለው፡፡ ህወሓት ለፖለቲካ ሲል የትግራይ ህዝብ ተጠቅሟል ይላል፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚዎችና ግለሰብ አክቲቪስቶችም በተመሳሳይ የትግራይ ህዝብ ተጠቅ ሟል ይላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም፡፡ የት ግራይ ህዝብ በርካታ ችግሮች አሉበት፡፡ እንዲያውም የትግራይ ህዝብ ውስጥ ባለው ቅሬታ ምክንያት መሰረ ታዊ ለውጥ ይመጣል ብለን ነው የምናስበው፡፡

በአሁኑ ወቅት አረና አሁን ኢህአዴግ የሚጠቀም በት ፌደራላዊ ስርዓት በመቀበል ቀስ በቀስ ግን እሴ ቶችን በመጨመር ለኢትዮጵያ አንድነት በሚጠቅም መልኩ በመቀየርና በማስተማር በስተመጨረሻም እን ቀይረዋለን የሚል እቅም ነው ያለው፡፡ ‘ጎን ለጎን ደግሞ በተለይ ከሌሎች ፓርቲዎች መዋሃድ ከቻልን፣ በውህ ደት ጠንካራ ፓርቲ መፍጠር ከቻልን፣ ሁሉም ፓር ቲዎች በሀሳብ ተከራክረን ተወያይተን የምንወስነው ይሆናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ለመደራደር ዝግጁ ነን፡፡

ግንቦት 20 ዴሞክራሲ አላመጣም፡፡ ለምዕራባዊያ ንና ለሌሎች አንዳንድ አገራት በህዝብ የተመረጥን ነን ለማለት ካልሆነ በስተቀር በዴሞክራሲ አያምኑም፡፡ ኢህአዴግ ውስጥ ዴሞክራሲ ስህተት ነው፣ የሚያስፈ ልገን ልማት ነው የሚባል አቋም ተይዟል፡፡ በትግራይ ክልል በግልጽ ዴሞክራሲ የሚባል ነገር እንደሌለ እየ ነገሩን ነው፡፡ ስለዚህ ዴሞክራሲ አልመጣም፡፡ ዴሞ ክራሲ መጣ የምንለው በህዝብ የተመረጠ መንግስት ሲኖረን ነው፡፡ እስካሁን ግን በህዝብ የተመረጠ መን ግስት የለንም፡፡ ኢህአዴግ ስልጣኑን የያዘው በጠመ ንጃ ነው፡፡ ስልጣንን በኃይል ከመያዝ ውጭ በህዝብ የተመረጠ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ በሩን ለዴሞክራሲ የሚከፍት አይደለም፡፡ ነገር ግን አንኳኩተን እንደም ንም ብለን ለመግባት እንሞክራለን፡፡

ህዝብ ምርጫ መረጠ የሚባለው የፈለገውን እንዲመ ርጥ ሲፈቀድለት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ አማራጮች ሲኖሩ ነው፡፡ አማራጮች በሌሉበትና አማራጮችም እንዲዳከሙ በሚሰራበት ስርዓት ሁሉንም ነገር ተቆ ጣጥሮ ተመርጫለሁ ቢል አንቀበለውም፡፡ እስካሁን በህዝብ የተመረጠ መንግስት የለም ያልኩት ኢህአ ዴግ መጀመሪያውኑ ስልጣን የያዘው በጠመንጃው ስለሆነ ነው፡፡ በህዝብ የተመረጠ መንግስት የምንለው ከጅምሩ ሀሳቡን ለህዝብ አቅርቦ፣ ህዝብን አሳምኖ፣ በህዝብ ምርጫና ድምጽ ስልጣን ሲይዝ ነው፡፡ ኢህ አዴግ መጀመሪያ በመሳሪያ ስልጣን ተቆናጠጠ፡፡ ከዛም ምረጡን አለ፡፡ ይህንን በህዝብ የተመረጠ ነው ልንለው አንችልም፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያውኑ ስል ጣኑን በጠመንጃ ነው የያዘው፡፡ ከዛ በኋላ ደግሞ የይ ስመላህ ምርጫ እየተደረገ፣ ተመርጫለሁ ቢል ተቀባ ይነት አይኖረውም፡፡ በመሰረታዊነት በህዝብ የተመ ረጠ መንግስት ሲባል ከጅምሩ ተወዳድሮ፣ ተፎካክሮ፣ አማራጮች ተዘጋጅተው፣ በህዝብና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሲመረጥ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ መቼ ነው የተወዳደረው? ካልን አልተወዳደረም፡፡ አልተ መረጠም፡፡

ከገፅ 5 የዞረ... እኛና ...

ገገር የአምባገነን ስርአት የኖረበት ዘመን የቱንም ያህል ቢለያይ፣ የሰፈነበት አገር የቱንም ያህል ቢራራቅ በተገገር ላይ የሚያደርሰው ግፍ በአብዛኛው ተመሳሳይ፣ የመጨ ረሻ ግቡም ዜጋዉን በፍርሃት አርዶ፣ ሰብአዊ ክብርን አዋርዶ፣ በችግር ቀፍድዶና አስጨንቆ ለዘላለም መግዛት ብቻ ነዉ፤ ከተቻለ፡፡ በየትኛዉም ዘመንና ሀገር የኖረ አም ባገነን ስርአት የስርአቱን እድሜ ዘላለማዊ ለመድረግ ሲል በሚፈጽማቸዉ ከስብአና የራቁ ተግባራትና ወንጀሎች የተነሳ እጁ በንጹሃን ደም የጨቀየ ነዉ፡፡ ስለሆነም ከስ ልጣኑ የሚወገደዉ በኃይል ወይም በህዝባዊ አመጽ ብቻ መሆኑን ከነ አቤ ዘመን ትምህርት ቀስመናል፡፡ የአምባገነን ስርአት የዘመን ዑደትም ይህንኑ እዉነት ያስረግጥልናል፡፡

የአምባገነን ስርአት አገዛዝ ሰለቶን፣ ነጻነትን አጥቶ ከመኖር ለነጻነት መሞት ይሻለናል ብለዉ ዱር ቤቴ ያሉና ለስልጣን የበቁ የዘመናችን ገገርቻች በተራቸዉ እነርሱ ከጠሉት የበለጠ አምባገነን፤ ይባስ ብሎ ከነአካቴዉ ኢት ዮጵያዊነትን ቆፍሮ ለመቅበር የሚታገል፣ የኢትዮጵዊያ ንን ተከባብሮና ተቻችሎ አብሮ የመኖር ነባር ባህል ንዶ በጥላቻ የተቦካ ዘረኝነትን ለመተካት ሌት ተቀን የሚሰራ፤ መጪዉን ዘመን ጨለማ የሚያደርግ ታሪክ ለመጻፍ የሚሞክርና ስልጣንን የሙጥኝ ብሎ ሀገሪቱን እንደ ግል ርስቱ የብቻዉ ለማድረግ የሚታትር አገዛዝ እንብረዋል፡ ፡ ሌላዉን ተርታ ዜጋ ኢትዮጵያ የእርሱም ሀገር እንዳልሆ ነች ሁሉ ከዜግነት ተራ አስወጥተዉ “አሁን ህገ-መንግስት አለን… በሀገርህ አስተዋጽኦ ማድረግ ትችላለህ፡፡ አሁንም ካልተመቸህ ደግሞ ሀገር ለቀህ መሄድ ትችላለህ፡፡፡” ሲሉ በህይወቱ ላይ ማድረግ ያለበትን ሳይቀር ወስነዉ ያስቀ ምጡሊታል፡፡

እያንዳንዱ ዜጋ አለህ የተባለዉ ህገ-መንግስት ይፈቅድል ኛል ከፍ ሲልም ሰብአዊ መብቴ ስለሆነ በነጻነት የማምለክ መብቴ ይከበር ሲል የለም አንተ በነጻነት ማምለክ የምትች ለዉ በዚያም አብዮታዊ ዲሞክራሲ የአምልኮትህ ዋልታና ማገር መሆኑን በልብህ ስታምንና ኢትዮጵያ ለዘጓቿ ምድራዊ ገነት መሆኗን በአፍህ ስትመሰክር ነዉ፤ ለሀገር ህም የሚጠቅም አስተዋጽኦ ላድርግ ካልክ ይህ የሚፈቀ ድልህ እኔ ባስቀመጥኩልህ መስመር መፍሰስ፣ ልማታዊ መንግስትን ማቀነቅን እኔ የምለዉን መድገም ስትችል ነዉ ይባልና ከሰዉነት ተራ አዉርደዉ መናኛ የማባገጥ ቁስ ሊያደርጉት ይሞክራሉ፡፡ ይኸኔ ያለዉ ምርጫ እንደ ሰዉ ከማሰብ ሰዉኛ ጠባይ ወርዶ የተባሉትን መድገም አሊያም ሀገርን ለቆ መሄድ ብቻ እንደሆነ እንዲያስብ ይፈረድበታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁለቱም ሁሌም አም ባገነኖች የሚያቀርቧቸዉ ለጥያቄዉ መልስ የማይሆኑና ለምርጫ የማይበቁ ምርጫዎች ናቸዉ፡፡ ስለሆነም እርሱ የሚፈልገዉን ለምርጫ አቅርቦ የማንፈልገዉን እንድንመ ርጥ የሚያስገድደንን ስርአት በሰላማዊና አስገዳጅ እምቢ ተኝነት ከተቻለ በጡንጫ መፈርጠም ሳይሆን በሀሳብ የበ ላይነት አዲያምን፤ ጥላቻን የሚዘራና የሚለያይ ሳይሆን ሁሉን በፍቅር የሚያቀፍና ወደ መሆን እንዲመጣ ካልተ ቻለ ደግሞ ካነበረዉ የተበላሸ ስርአት ጋር በህዝብ እም ቢተኝነት እንዴና ላይመለስ ታሪክ ማድረግ ብቸኛዉ አማራጭ ይሆናል፡፡

አሁን የግፉኣን እንባና የንጹሃን ደም የአምባገነንነት ጽዋዉን ሞልቶታል፡፡ የሚቀረዉ ሀገርን የማዳን ጥሪን ከግል ጥቅሙ መለየት ተስኖትና ሁለት እግሩን በፖለቲ ካና በንግድ መካከል አንፈራጦ ሁለቱንም ላለማጣት ሁለ ቱንም ሽባ የሚያደርግ አላጋጭ ፖለቲከኛን ከሚዳዉ ማስ ወገድ፣ የወገኑ መገፋትና ስቃይ ያንገበገበዉ እምቢ ባይ ሙሴን መፍጠር፣ ወደተቃዉሞ ጎራዉ በገፍ መትመምና ተቃዉሞዉን ማጠናከር ተባብሮም ለነጻነት የሚከፈለ ዉን ዋጋ በጋራ መክፈልና የራስን ነጻነት በእጅ ማስገባት ነዉ፡፡ ዛሬ ላይ ሆነን “መብታችንን ማግኘትና የሚቀጥለ ዉን ትዉልድ ከነመብቱ መዉለድ፡፡ “ካልቻልን” ቀማኞ ችና ነፍሰ ገዳዮች እንዲሁም የነጻነት ጠላቶች በሰለጠኑ በት ዓለም… የድሆችን ልጆች የሚጠብቃቸዉ የወላጆቻ ቸዉ መከራና ችግር ብቻ ነዉ፡፡፡” ያለው አቤ ነዉ፡፡ እናሳ? እኛን አምባገነኖች ድሃ ያደረጓት የደሃዋ ኢትዮጵያ ልጆች ከፈታችን የሚጠብቁን የታማኝ ካድሬነት ሚናን በመወ ጣት የሚወድቅ ፍርፋሪ መለቀም ነዉ. ወይስ በብታትና በልፋት ብቻ የሚገኝ እንጀራ? በነጻነት አስበን በፍትሃዊ ነት ተወዳድረን ነገን ዛሬ መስራት ሳንችል ከመከራስ በቀር እኛ የምናወርሰው ነገር ይኖረን ይሆን? ለሺህ ዘመናት በጀ ግኖች ልጆችዋ የተባበረ መስዋእትነት የተጓዘች ኢትዮጵያ ከፊት ለፊቷ ያለዉን ጨለማ ተሻግራ ነገን እንድትኖር የማይመኝላት ማን ይሆን? ግን ምኞት ለዉጥ ስለማይሆን ለለዉጡ በጋራ መስራት ግድ ይላል፡፡

የግንቦት 20ን እንክርዳድ ለመመንገል!

ታዴዎስ ታንቱ
የመ.ሣ.ቁጥር 43414

ዛሬ ኢትዮጵያ ሀገሮችን መሆኗን ለመናገር ከማፈራችን የተነሣ በትንሽዋ ጥፍራችን ውስጥ ለመደበቅ እስከ መሞከር ደርሰናል፡፡ ተቸግረናል! ሙበት አልባ ሆነናል፡፡ ከሥነ መንግስት ስልጣን ተገፍትረናል፡፡ ከብሔራዊ ሀብታችን የመጠቀም አቅም አጥተናል፡፡ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ቆመናል፡፡ ወደ ሰማይ ልንመጥቅ አንችልም፡፡ በከርሰ መሬት ውስጥ አንደበቅም፡፡ ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ሀገር ወርሰናል፡፡ ግን ሀገር አጥተናል፡፡ የመከራ ቀንበር በጫንቃችን ተሸከመናል፡፡ ዋይታ ነሣሏል፡፡ መከራ! መከራ! መከራ! እንክርዳድ ጎመራ! በግንቦት አዝመራ!

የጎሳ ግጭት

ባለፉት 23 ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ በታሪኳ አይታ የማታውቀው መጠነ ሰፊ የጎሳ ግጭት በዚህ ሀገር ተካሂዷል፡፡ የጎሣ ግጭት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የግንቦት 20 ገፀ በረከት ነው፡፡ ብሶት የወለዳቸው ጀግኖች የጦርነት ውጤት ነው፡፡ የገዥዎቻችን የድል ብስራት ነው፡፡ ከጎሣዎች እልቂት ህወሓት ተጠቅሟል፡፡ ከየ ብሄረሰቡ በተመለመሉ ሎሌዎቹ አማካይነት በየከፍለ ሀገሩ ጠንካራ ድብቅ ኃይል ሆኗል፡፡ የጎሳ አምበሎችን ታማኝነት በግጭቱ ሂደት ፈትኗል፡፡ ገዥው ህወሓት ተገዥ የጎጥ አምበሎችን በገዥነት ሥነ ልቦና ለማነፅ የጎሳ ግጭቶችን ተጠቅሟል፡፡ አዝዘዙ አንዱን በአንዱ ላይ በማነሳሳት መርጦ በመወገን ከግጭቱ የወርቅ እንቁላል ሰብስቧል፡፡ በዚህ ምክንያት አሁን በኢትዮጵያ ምድር የተንሰራፋው ጨቋኙ የጎሣ ሥነ መንግስት አገዛዝ በይዙቱ ግጭት ነው! እልቂት ነው! ሞት ነው! ለሺዎች አመታት ተከባብረው የኖሩትን ሁለት ጎሣዎች አጋጭቶ ከውጤቱ የሥነ መንግስት ትርፍ ሲያጋብስ ኖሯል፡፡ አሁንም በዚህ ድርጊቱ ቀጥ ሎበታል፡፡ ሒሳቡን ይሥራል፡፡ ትርፉን ይሰበስባል፡ ፡ ለጎሳዎች ሕይወት ደንታ የለውም፡፡ የስነ መንግስት ጥቅም ይቀድማል! ስለዚህ የጎሣ ግጭት ተለመደ ነገር እየሆነ መምጣቱ ይስተዋላል! አገዛዙ ረክቷል! ባለፉት 23 ዓመታት ውስጥ በርካታ ጎሳዎች ተጋጭተዋል፡፡ ብዙ ሕይወትም አልቋል፡፡ በ1987 ዓ.ም ጌዴኦና ጉጂ ከፍተኛ ግጭት አድርገዋል፡፡ በዚሁ ግጭት ቁጥሩ የበዛ የሰው ህይወት አልቋል፡፡ ሁለቱ ጎሳዎች የከብት ዘረፋም አካሂደዋል፡፡ ከብት ተዘራ ርፈዋል፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ ደረጃ የንብረት ውድመት ተከስቷል፡፡ በ1998 ዓ.ም ደግሞ ጥቂት የስ ርዓት አገዛዙ አገልጋዮች ሌሎች ብሄረሰቦችን ከጌዴኦ አውራጃ ለማስወጣት ባደረጉት ቀናትን በፈጀ ሙከራ በርካታ ሕይወት ጠፍቷል፡፡፡ ጥቂት የማይባል ንብረትም ወድሟል፡፡ ለዚህ እልቂት ተጠያቂው ማን ሊሆን ይችላል? ያለ ጥርጥር አገዛዙ ይሆናል! ለምን በቀዳማዊ ኃይለስላሴና በደርግ አስተዳዳር ዘመን ሌሎች ብሔረሰቦች የጌዴኦን አውራጃ ለቅቀው እን ዲሄዱ ለማድረግ እንቅስቃሴ አልነበረም? ባለፉት ሁለት መንግስታት ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ታስበም አያውቅም፡፡ እንዴት ይታሰባል? ሰው በገዛ ሀገሩ ለመኖር ማንንም ማስፈቀድ የለበትምና፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሁለት ሥርዓቶች ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ በየትም ቦታ በኢትዮጵያ ንብረት አፍርቶ፣ ተረጋግቶ የመኖር ነጻነት ነበረው፡፡

የጎሳ ግጭት የስርዓት አገዛዙ መለያ በህሪይ መሆኑ በየወቅቱ በተግባር ታይቷል፡፡ ለመሆኑ ባለፉት 23 ዓመታት ውስጥ ከወገኑ ጋር ያልተጋጨ ጎሣ በዚህች ሀገር ይኖር ይሆን? የለም፡፡ እንዲያውም ኢትዮጵያ ባለፉት 23 ዓመታት ውስጥ በአፍሪካ ቀንድ የጎሣ ግጭቶች ማእከል ሆና አሳልፋለች፡፡ ይህን ማንም ሊያስተባብል አይችልም፡፡ ከፀሐይ የበራ ከጨረቃም የደመቀ ሐቅ እንዴት ይታበላል? በስሜታዊነት እና ወራም፡፡ በእርግጥ ዛሬ በኢትዮጵያ የሥነ መንግስት ሥልጣን ርካብ ረግጦ በህዝብ ጫንቃ ላይ የተከፈ ሰው ራሱን ህወሓት እያለ የሚጠራ ቡድን እንዲወገ ድልን እንፈልጋለን! ሆኖም ግን ሐሰት እናወራም! የአ ገዛዙ ባለሥልጣናት አይደለንም! ለምን ሐሰት እናወ ራለን? የአገዛዙ ካድሬ አይደለንም! ለምን ሀሰት እና ወራለን? የአገዛዙ የፀጥታ አባላት አይደለንም? ለምን ሐሰት እናወራለን? በህሊናችን ሞትን በሆዳችን የምን ኖር የአገዛዙ ሎሌ አይደለንም! ለምን ሐሰት እናወራ ለን? እውነት ሞልቶ ተርፎ ለምን ሐሰት እናውራለን? በፍጹም ሐሰት ከእንደበታችን አይወጣም! ላላፉት 23 ዓመታት ውስጥ በርካታ ዜጎች በዚች አገር ላይ በጎሳ ግጭቶች መተኪያ የሌለውን ህይወታቸውን አጥ ተዋል፡፡ በዚህ ሂደት በ1999 ዓ.ም ቦረናና ጉጂ ተጋ ጭተዋል፡፡ በዚሁ ግጭት ህይወት ወድቋል፤ ንብረት ወድሟል፡፡ የግንቦት 20 እንክርዳድ ጎምርቷል፡፡ በተ መሳሳይ መልኩ በ2000 ዓ.ም ሲዳማና አርሲ ግጭት ፈጥረዋል፤ ሕይወት ጠፍቷል፡፡ ቤቶች ተቃጥለዋል፡ ፡ እንዲሁም በዚሁ ዓመተ ምህረት አላባና አርሲ ግጭት ፈጥረው እንደነበር ታውቋል፡፡ በተዛመደ መልኩ በዚሁ ዓመተ ምህርት የኮንሶና ቦዲ ጎሳዎች ተጋጭተዋ፡፡ በ2001 ዓ.ም ደግሞ አማሮና ቡርጂ ተጋ ጭተው ሕይወት ጠፍቷል፡፡ የቆጭሬና የዶባሲ ጎሳ ዎችም እርስ በርሳቸው ተጋጭተው ሰዎች ሞተዋል፡ ፡ አገዛዙ አንድ ጎሳን እንኳን በመንደር ከፋፍሎ የማ ጋጨት ችሎታ አለው፡፡ በዚህም መሰረት የደራሼ ተወላጆች እርስ በእርሳቸው ተጋጭተው እንዲተላ ላቁ አድርጓል፡፡ እንዲሁም ኮንሶና ጋዶ ተጋጭተው በርካታ ሕይወት ተቀጥፏል፡፡ ገዥዎቻችን የኢትዮ ጵያን የሥነ መንግስት ሥልጣን እንደጨበጡ አማራ ንና ኦሮሞን ኢጋጭተው እርባ ጉጉ ላይ የተከሰተውን እልቂት አንርሳ፡፡ በገዥዎቻችን ቀስቃሽነት ንፁሃን እየተገደሉ በበደኖ ገደል ላይ መጣላቸውንም ልን ዘነጋው አይገባም፡፡ በአሰቦት ገዳም ውስጥ የተፈፀ መውም ጭፍጨፋ ይታወሳል፡፡ ይህ ሁሉ እኩይ ድርጊት ደግሞ የግንቦት 20 ውጤት ነው፡፡ የጎሣ ግጭቱ አሁንም ቀጥሏል፡፡ ሞት በኢትዮጵያ ረክሷል! ዋይታ ነግሷል! ግንቦት ምን አመጣልን? ግንቦት 20 የጎሣ ግጭት አመጣልን!!

> የጎሣ ግጭት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የግንቦት 20 ገፀ በረከት ነው፡፡ ብሶት የወለዳቸው ጀግኖች የጦርነት ውጤት ነው፡፡ የገዥዎቻችን የድል ብስራት ነው፡፡

ህግና ሕጋዊነት

በኢትዮጵያ ውስጥ ህግና ህጋዊነት መኖሩን ለመናገር የሚያስችል ተጠየቅ የለም፡፡ አገዛዙ በጥይት ይገድ ላል፡፡ ቀጥቅጦ ይገድላል፡፡ አስሮ አማቅቆ ይገድላል፡ ፡ የዜጎችን ቤት ያፈርሳል፡፡ የአርሶ አደሮችን መሬት ይቀማል፡፡ ሕግና ህጋዊነት ጠፍተዋል! ለአገዛዙ ኃይል ህግ ነው! ህግም ኃይል ነው! ዜጎች በሰላም ውለው

ወደ ገፅ 12 ዞሯል ...

ሰንደቅ አላማው ከግንቦት 20 በኋላ

አቤል ኤፍሬም

ሰንደቅ ዓላማ በአለማችን ላይ ትልቅ ታሪክ ያለው እና ከጥንት ዘመን ጀምሮ በርካታ የዓለማችን ሐገራቶች እንደየ ህዝቦቻቸው አመለካከት እና አሳቤ የየራሳቸ ውን ሰንደቅ ዓላማ በማዘጋጀት ሲጠቀሙ ኖረዋል፡ ፡ ለምሳሌ ያህል አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማትን ኢትዮጵያውያን እና ቦሊቪያውያን ከቀስተ ዳመና ጋር በማመሳሰል ይጠቀሙበት፡፡ እንደነበር የተለ ያዩ ማስረጃዎች ያስረዳሉ ቦሊቪያውያን እስከአሁን ድረስ ነሐሴ 17 ቀንን የሰንደቅ ዓላማ ቀን እያሉ ያከብ ሩታል፡፡ የእኛ የኢትዮጵያውያንን የቅርቡን የሠንደቅ ዓላማ ታሪክ ስንመለከት አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለምን በመንግስት ደረጃ የተጠቀሙት አፄ ምኒልክ ሲሆኑ ጊዜውም እኤአ 1897 ላይ ነው፡፡ ከምኒልክ ዘመን ጀምሮ አሁን እስከገለው የኢህአዴግ ዘመን ድረስ ንጉሶች እና ገዢዎች በአረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት ላይ የተለያዩ አርማዎችን እየጨመሩ እዚህ ደርሰናል፡፡ ኢህአዴግም ባዘጋጀው ህገመንግስት አንቀፅ 3 ላይ በሰንደቅ አላማው ላይ ከከብ እንዲገባ አዟል፡፡ ይህን ኢህአዴግ ግንቦት 20 ለህዝቦች በአኩል ነት ለመኖር የፈጠረው ተስፋ ምልክት ነው ይለዋል፡፡

ሰንደቅ አላማ የአንድ አገር ምልክትና መለያ ነው፡፡ ቋንቋና ቀለማቸውን፣ የአገራቸውን ካርታና የት እንደ ሚገኙ በውል የማናውቃቸውን ህዝቦች እንኳ ሰንደቅ አላማውን ልናውቀው እንችላለን፡፡ ይህም አንድም በስፖርታዊ ውድድሮች አሊያም ፖለቲካዊ በሆኑ መድረኮች ሰንደቅ አላማው መሪ ተቀያየረ አልተቀያረ ህዝብንና አገርን ወክሎ በተደጋጋሚ የመገኘት እድል ስላለው ነው፡፡ ስለሆነም ሰንደቅ አላማ ከምልክትነ ትም በላይ የሉዓላዊነት መገለጫ ተደርጎ እንዲወሰድ አንድ ምክንያት ሆኗል፡፡

ሰንደቅ አላማ በሐገራችን በተለምዶ ባንዲራ እየተባለ ይጠራል ይኸውም በጣሊያን ወረራ ወቅት ከጣሊያ ነኛው (Bandiera) ተወስዶ እንደሆነ ይታመናል፡፡

አብዛኛዎቹ የአገራችን መሪዎች ለሰንደቅ አላማው ቀናኢ እንደሆነ ታሪካቸው ያስረዳል፡፡ ይህም የመነ ጨው ምንም ያህል ንብጋባና ራስ ወደድ ቢሆኑ እንኳ ከኢትዮጵያ ታሪክ፣ ሉዓላዊነት ጋር የማይጋጨ ስለነ በር ነው፡፡ ከኢህአዴግ በፊት ያለውን ደርግ ብንወ ስድ በሰንደቅ አላማ ጉዳይ የሚታማ አልነበረም፡፡ እንዲያውም ሙዚቀኞች ከአንድ አልበም ውስጥ ስለ አገር አንድነትና ፍቅር የሚያወሳ ዘፈን መዝፈን የግድ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሰንደቅ አላማ ደግሞ ቅድሚያ ይሰጠው እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህ ደርግ ለሰንደቅ አላማው የሚሰጠው ክብር ግን ከእሱ አገር ወዳድነት ብቻ የመጣ አልነበረም፡፡ በተቃራኒው እንደ ህወሓት፣ ኦነግና ሌሎችም መሳሪያ አንግበው አገር ለመገንጠል ሲሰሩ የነበሩ የአገራችን ታጣቂዎች እንወከለዋለን የሚሉትን ህዝብ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማን እንዲ ጠላ ቅስቀሳ ያደርጉ ስነበርና ሰንደቅ አላማውን በማ ዋረዳቸው ነው፡፡ ደርግ ይህን ጸረ ኢትዮጵያውያት በሚገባ መወጣት አለመወጣቱ ሌላ ጉዳይ ቢሆንም የራሱን ጥረት ማድረጉ ግን ሊደበቅ የማይችል ታሪኩ ሆኖ ለትውልድ ይተላለፋል፡፡

በዛን ወቅት ጠንካራ ከነበሩ ድርጅቶች መካከል ሻዕቢ ያና ህወሓት በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ጸረ ኢትዮጵያ አቋም ይዘው የተነሱ ጠርዘኛ ተቃዋሚዎች ታዲያ ደርግን ስልጣን ከመንጠቅም ውጭ ሰንደቅ አላማውንና በዚሁ ሰንደቅ አላማ ውስጥ ያለውን መንፈስ ለመሸርሸር የሚችሉትን ያህል ሰርተ ዋል፡፡ ነገሩ እንደ ሶማሊያና የአረብ አገራት ጋር የተሻ ረከ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ላይ ከዚህም በላይ በደል ቢፈጽም የሚያስገርም አይሆንም፡፡

በወቅቱ ሻዕቢያ ከሁሉም የጠነከረ አቅም ስለነበ ረው ደርግ ይቆጣጠራቸው የነበሩ መስሪያ ቤቶችንና ሌሎች ተቋማትን በመያዝ፣ በመዝረፍ የተለያዩ ቁሳቁ ሶችን ይወስድ ነበር፡፡ በዛን ጊዜ ስለ አገር አንድነት ለማ ስረጽ ሲባል በየ መስሪያ ቤቱ በርካታ ሰንደቅ አላማ ይከፋፈል የነበር በመሆኑ በሻዕቢያ እጅ የገቡ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ሰንደቅ አላማው አብሮ ይዘረፍ ነበር፡ ፡ ከሰንደቅ አላማው ውጭ የተለያዩ የእቃ መያዣደ ጃንያዎች፣ ጨርቆችና ሌሎችንም የመዝረፍ እድሉን አግኝቶ ነበር፡፡ ነገር ግን ጨርቅና ጆንያ ባልጠፋበት ሻዕቢያ የዘረፈውን ምግብም ሆነ ሌላ ነገር በሰንደቅ አላማው በመሸብለል ሰንደቅ አላማውን ለማዋረድ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል፡፡ ይህን የሚያደርገው ቀስ በቀስ አባላቱም ሆነ በአካባቢው የሚገኘው ህዝብ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ «ጨርቅ» አድርጎ እንዲ ያየው ነው፡፡ ከሻዕቢያ ዱቄትም ሆነ ሌሎቹን እየለ መነ የተዋጋው ህወሓትም ይህን የሻዕቢያ ርካሽ ስራ ተምሯል፡፡ ውጊያ ላይ ይህ ነው የሚባል ተሳትፎ እን ዳልነበረውና እንዲያውም በአንድ ወቅት የሚመራ ውን ሰራዊት ጥሎ እንደጠፋ በጎደኞቹ ዘንድ የሚነ ገርለት መለስ ዜናዊ ደግሞ ዱቄትም ሆነ ሌላ ነገርን ከሻዕቢያ ተቀብሎ ለህወሓት በማድረስ ቀዳሚውን ሚና ይወጣ የነበር ሰው ነው፡፡ እናም ይህን የሻዕቢ ያን ሰንደቅ አላማ የማዋረድ «ራዕይ» ለህወሓትም ሆነ ለኢህአዴግ ያስተማረው እሱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስልጣን በያዘ በጥቂት አመታት ውስጥም ይህን እኩ ይነት በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ለመርጨት ሰንደቅ አላ ማውን በአደባባይ «ጨርቅ» ብሎ መናገሩ የማይታ በል ሀቅ ነው፡፡

> ጨርቅና ጆንያ ባልጠፋበት ሻዕቢያ የዘረፈውን ምግብም ሆነ ሌላ ነገር በሰንደቅ አላማው በመሸብለል ሰንደቅ አላማውን ለማዋረድ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል፡፡ ይህን የሚያደርገው ቀስ በቀስ በቀስ አባላቱም ሆነ በአካባቢው የሚገኘው ህዝብ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ‹‹ጨርቅ›› አድርጎ እንዲያየው ነው፡፡

ወደ ገፅ 11 ዞሯል ...

የምርጫ ሽርጉድ በ2007ቷ ኢትዮጵያ

አለማየሁ ገ/ማርያም (ፕ/ር)

እ.ኤ.አ በ2010 በተካሄደው ምርጫ አቶ መለስ 99.6 በመቶ ድምጽ በማግኘት ለማሸነፍ በማሰብ የአራሳቸውን መንገድ በመከተል ፓርቲያቸው እን ዲመረጥ በኃይል አስገድደዋል፤ ጉቦ ሰጥተዋል፣ አስፈራርተዋል እንዲሁም መራጩ ህዝብ በፍር ሀት ቆፈን ውስጥ ተወሽቆ የመምረጥ መብቱን በአ ግባቡ እንዳይጠቀም አድርገዋል፡፡ ከገጠሩ ህዝብ ድምጽ ለመሸመት እና በግዳጅ ድምጽ ለማግኘት በሚል የውጭ የሰብአዊ መብቶችን እና የኢኮኖሚ እርዳታዎችን ከታለመላቸው ዓላማ ውጭ በማጠፍ ለእኩይ የምርጫ አላማቸው ማስፈጸሚያ እንዲ ውሉ አድርገዋል፡፡ የወጣቱን ታማኝነት ለመማዘት በማሰብ ለዘለቄታው የሚያቆዩ እና ለሀገሪቱም ሆነ ለወጣቶቹ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን የሚያስገኙ ስራ ዎችን ሳይሆን ለጊዜው ብቻ ከርስን ለመሙላት የሚ ያገለግሉ ተራ ስራዎችን ለማደል ተፍጨርጭረዋል፡ ፡ የመንግስት ሀብቶችን እና ንብረቶችን ለአራሳቸው ፓርቲ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ዘመቻ እንዲውሉ አድርገ ዋል፡፡ የእርሳቸውን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለመለየት እና ለማኮላሸት ሰፊ የቁጥጥር ፕሮግራሞች፣ የስለላ እና የመረጃ አቀባይ መረቦችን የመዘርጋት ስራዎችን አደራጅተዋል፡፡

አቶ መለስ ዜናዊ እ.ኤ.አ በ2010 በተካሄደው ምርጫ 99.6 በመቶ ድልን ለመቀዳጀት በተዘጋጁ በት ወቅት እንደስልት የተጠቀሙት ለሰው ልጅ ክብር በማይሰጠው አፋቸው በኃይል የማስፈራሪያ ንግግር ማድረግ እና በተደባዳቢ እጃቸው ደግሞ ትልቅ ዱላን መጨበጥ ነበር፡፡ ቁጣን በማነሳሳት እና የጥላቻ ዘመቻን ዓላማ በማድረግ "እረብሻ ለማስነ ሳት" በሚሞክሩት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ላይ የማያዳግም እርምጃ እንደሚወስዱ ያስፈራሩ ነበር፡ ፡ በመጨረሻዋ ደቂቃ እራሳቸውን ከምርጫ ሂደቱ የሚያገልሉ እና ወጣቶች በየመንገዶቹ አደባባዮች በመውጣት ለአመጽ እንዲሰለፉ ቅስቀሳ የሚያደርጉ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን ወደ እስር ዘብጥያ እንደሚወረውሯቸው በድፍረት ይዝቱ ነበር፡፡ 78 የሚሆኑ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን በም ርጫው በዝረራ ካሸነፉ በኋላ የማስመሰያ የወይራ ዝንጣፊ ይዘው ቀረቧቸው፡፡ የተቃዋሚ አመራ ሮች የአራሳቸውን ጭራዎች በአግሮቻቸው መካከል የሚይዙ ከሆነ እና የአቶ መለስን እግር የሚስሙ እስከሆነ ድረስ የእርሳቸውን ምህረት እንደሚያ ገኙ መተማመኛ ተሰጣቸው፡፡ በቀጣይነትም አቶ መለስ እንዲህ አሉ፣ "በዚህ ምርጫ ወቅት ከህዝቡ የምርጫ ድጋፍ ባለማግኘት ስኬታማ ላልሆናችሁ እንዲሁም በፓርላማው መቀመጫ ይኑራችሁም አይኑራችሁም የህዝቡን ፍላጎት አስካከበራችሁ እና የአገሪቱን ህገ መንግስት እንዲሁም ሌሎችን ህጎች እስካከበራችሁ ድረስ በሁሉም አገራዊ ጉዳዮች ላይ እናንተን እያማከርን እና እያሳተፍን የምንሰራ መሆ ናችንን ቃል እንገባለን፡፡ ይህንን ቃል የምንገባው ከእ ናንተ ጋር በአጋርነት መስራት ስላለብን ብቻ አይደ ለም...ሆኖም ግን እናንተ የመሳተፍ እና የመደመጥ መብት ስላላችሁ ጭምር እንጂ፡፡» የአቶ መለስ ቃል ኪዳኖች እነርሱን እንደበቀቀን ለመደጋገም ከሚያወ ጡት ትንፋሽ የበለጠ ፋይዳ የላቸውም፡፡ በዚያው በነበር የሚቀሩ ናቸውና፡፡

የአቶ መለስ ዜናዊ ሙት መንፈስ በ2007

የአቶ መለስ ዜናዊ ሙት መንፈስ፣ የሸክስፒርን ቃላት በመዋስ "በጨለማው የሲኦል ውስጥ ጢስ እንደም ያንጃበበው በኢትዮጵያ 2007 ምርጫ ላይ ያንጃብ ባል፡፡» አቶ መለስ በቀን ብርሀን የተዘረፉ እና የተጭ በረበሩ ምርጫ ዋና ደራሲ ነበሩ፡፡ የምርጫ ማጨበ ርበሪያ እና የዘረፋ ጨዋታ ድርሳኑን እና መጽሀፉን የጻፉት የውርስ ስልጣኑን ከመጨበጣቸው በፊት በጫካ ውስጥ እንደነበሩ ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2005 እር ሳቸው እና ፓርቲያቸው በመጠኑም ቢሆን በአራስ የመተማመን በአዎንታዊ መልኩ ልዩ በመሆን የዴ ሞክራሲ በሩን ገርበብ አድርገው ለመዝጋት ሙከራ አድርገው ነበር፡፡ ሆኖም ግን ከሁኔታዎች ወዲያ ውኑ ትምህርቱን በሚገባ ቀሰሙ፡፡ በምንም ዓይነት መልኩ ለትክክለኛ ተቃዋሚዎች ምንም ዓይነት ቀዳዳ የመስጠት ጨዋታ በፍጹም መደገም እንደሌለ በት ጽኑ አቋም ያዙ፡፡ በዚያው ዓመት ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ሁሉንም ቁንጮ የተቃዋሚ አመራር አባላትን፣ ነጻ ጋዜጠኞችን፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋ ቾችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አመራሮ ችን በጅምላ አሰሩ፡፡

በ2007 አጠቃላይ የምርጫ ዘረፋ ወንጀል ስልቱ በአቶ መለስ የተቀመረው የተለመደው አሮጌው አሰራር ነው፡፡ አቶ መለስ ለኢኮኖሚው "የዕድገት እና ትራንስፎርሚሽን ዕቅድ" ብለው እንዳዘጋጁት ሁሉ በተመሳሳይ መልኩ በፖለቲካውም መስክ እን ደዚሁ "ታማኒነት የጎደለው የኢትዮጵያ የምርጫ ዘረፋ ዕቅድ (ታኢምዘዕ)» በሚል እንዴት አድር ገው ምርጫን መዝረፍ እንደሚችሉ የሚመሩበት መጽሀፍ ጽፈዋል፡፡ የታኢምዘዕ ዕቅድ አንድ ቀላል የሆነ ሀሳብን መተግበር ብቻ ነው፡፡ ይኸውም "ኢህ አዴግ ብቻ ነው ለኢትዮጵያ ተቀርቋሪ!፣ ኢህአዴግ ብቻ ነው ለኢትዮጵያ ቋሚ ተጠሪ! ኢህአዴግ የኢ ትዮጵያ ብቸኛ ተከላካይ፣ አቅራቢ እና ጠባቂነው! ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ብቸኛ የመረጋጋት፣ ሰላም፣ ልማት እና መሻሻል ዋስትና ነው፡፡» የሚል ነው፡፡

የታኢምዘዕ ዕቅድ በ2007 የሚካሄደውን አገር አቀፋዊ ምርጫ መቶ በመቶ ማሸነፍ ነው፡፡ ከዚህ ባነሰ ውጤት ማሸነፍ የአቶ መለስን መታወስ ክብር ማሳጣት እና ዘለፋ ነው! ዕቅዱ ተግባራዊ መሆን የሚችለው የታኢምዘዕ ጠባቂ እረኞች በምርጫ ጨዋታቸው ላይ ያሉት አብዛኞቹ ተጫዋቾች ለማ ታለል እና ሁሉንም ተጫዋች ሰብስበው በመያዝ መቆጣጠር ከቻሉ ነው፡፡

የህወሓት አገዛዝ በማስመሰያ ስሙ "ኢህአዴግ" እያለ እራሱን የሚጠራው ኃላፊነት የጎደለው ቡድን ለኢትዮጵያ ህዝብ እና ለዓለም አቀፍ አበዳሪ እና ለጋሽ ድርጅቶች በአገሪቱ ሰላምን እና ስርዓትን ለማ ስያዝ እንዲሁም በዚህች አገር የእርስ በእርስ የብጥ ብጥ ቀውስ እንዳይመጣ አቅሙ ያለው እና ማድረግ የሚችል ብቸኛ ድርጅት እርሱ ብቻ እንደሆነ ለማሳ መን እና በስልጣን ላይ እንደመቸገር ተጣብቆ ለመ ቆየት ማናቸውንም ዓይነት ዕኩይ ተግባራት ከመ ፈጸም እንደማይቆጠብ ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ አይደለም፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ ይህች አገር እንደ ሩዋንዳ ሁሉ ወደ የእርስ በእርስ ጦርነት ትዘፈቃ ለች በማለት የኢትዮጵያን ህዝብ እና በገንዘብ የሚ ረዱትን የውጭ ድርጅቶች ለማሳመን ጥረት ያደር ጋል፡፡ ከኢህአዴግ ውጭ ይህች አገር በጎሳ መበጣ ጠስ፣ በግጭት እና እንደ ሱዳን ወደ ጦርነት ትገባ ለች በማለት የማስፈራሪያ ውሸጉብራቸውን ያሰራ ጫሉ፡፡ ከኢህአዴግ ውጭ ወይም ኢህአዴግ በስል ጣን ላይ እስካልቆዩ ድረስ "ጭራቆቹ"" አማራዎች" ስልጣንን ይነጠቃሉ፡፡ ከኢህአዴግ ውጭ "ኦሮሞ ዎች" ስልጣንን በመንጠቅ "አማራዎችን" ይቀጣሉ፡ ፡ ከኢህአዴግ ውጭ "ትግራውያን" "በአማራዎች" እና "በኦሮሞዎች" ጣምራ ስቃይ ይደርስባቸዋል፡፡ በብሄር ብሄረሰቦች ብዝሀነት የበለጸጉትው የኢትዮ ጵያ ብሄረሰቦች ከቢታቸው እንዲፈናቀሉ ይገደዳሉ፣ መሬቶቻቸውን ይነጠቃሉ፣ እንዲሁም በቋንቋዎቻ ቸው የመናገር መብቶቻቸውን ያጣሉ እያለ ኢህአ ዴግ ያናፍሳል።

ከኢህአዴግ ከሌለ በመጥፎነቱ የሚታወቀው አስቀ ያሚው ደርግ ከተቀበረበት መቃብር እራሱን ብቅ ማድረግ ይጀምራል፡፡ ከኢህአዴግ ከሌለ "የሙ ስሊሙ ማህበረሰብ" የሻሪያ ህግ በኢትዮጵያ ላያ በኃይል እንዲጫን ያደርጋል፡፡ ከኢህአዴግ ከሌለ "የሙስሊሙ" እና "የክርስቲያኑ» ህዝብ በመካከለ ኛው አፍሪካ ሬፐብሊክ እንደሚስተዋለው እርስ በእርስ ይተራረዳሉ፡፡ ከኢህአዴግ ከሌለ በናይጀሪያ እንዳለው ቦኮሀራም የተባለው ጽንፈኛ አክራሪ የእ ስልምና ቡድን ሁሉ የኢትዮጵያ የእስልምና አክራሪ ዎች በኢትዮጵያ ላይ ታላቅ አደጋ ያመጣሉ፡፡ ከኢ ህአዴግ ከሌለ በሙስና እና በሌብነት እራሳቸውን ከበርቴ ያደረጉ ሙሰኞች እና መንታፊ ሌቦች ሀብ ታቸውን እንዲነጠቁ ተደርጎ ወደ እስር ቤት ዘብጥያ ወይም ወደ ግዞት ይወረወራሉ፡፡ ከኢህአዴግ ከሌለ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተሽመድምዶ ይወድቃል፣ እን ዲሁም ኢትዮጵያ ከ11-15 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ስታስመዘግብ የቆየችው ምናባዊ ዓመታዊ የኢኮ ኖሚ እድገት ይቆማል፡፡ ኢህአዴግ ከሌለ በኢትዮ ጵያ ምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ዕድገት አይኖርም፡ ፡ ከኢህአዴግ ከሌለ ሰማይ ተሰብሮ ይወድቃል፣ እናም ከዋክብቶቹ ከሰማይ ወደ ኢትዮጵያ ምድር ላይ ወድቀው ይንኮታኮታሉ፡፡ ኢህአዴግ ከሌለ ኢት ዮጵያ አትኖርም!!!

በቀላል አነጋገር ሲገለጽ የኢህአዴግ የምርጫ ማሸነፍ ዕቅድ አሮጌውን የፍራቻ እና የጥላቻ ስልት በተግባር ላይ ማዋል ነው፡፡ ስልጣናቸውን ለመጠበቅ አማራ ዎችን ማስፈራራት ከቻሉ እና ኦሮሞዎችን በታላቅ ፍርሀት ውስጥ መወሽቅ ከቻሉ "ምርጫዉን" አሸን ፈው በስልጣን ላይ ይቆያሉ፡፡ ኦሮሞዎች አማራዎ ችን እንዲጠሉ ማድረግ ከቻሉ "ምርጫዉን" አሸን ፈው በስልጣን ላይ ይቆያሉ፡፡ የኦሮሞዎችን አዕምሮ በታሪክ ጸጸት ንትርክ ውስጥ በመዘፈቅ በደርዘኖች የሚቆጠሩ ንጹሀን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን እልቂት እንዲረሱ ማድረግ ከቻሉ "ምርጫዉን" አሸንፈው በስልጣን ላይ ይቆያሉ፡፡ ትናንሽ የጎሳ ብሄረሰቦችን "ኢህአዴግ" ወደፊት የማይኖር ከሆነ ዓለም በእነርሱ ላይ ትጨልማለች በማለት ማሳመን ከቻሉ "ምርጫ ዉን" አሸንፈው በስልጣን ላይ ይቆያሉ፡፡

የክርስቲያኑ እና የሙስሊሙ ማህበረሰብ በፍርሀት፣ በጥላቻ እና እያንዳንዳቸው እርስ በእርስ እንዳይ ተማመኑ ማድረግ ከቻሉ "ምርጫዉን" አሸንፈው በስልጣን ላይ ይቆያሉ፡፡ የእነርሱ ሀብታም ደጋፊ ዎቻቸው ኢህአዴግ የማይኖር ከሆነ በእርግጠኝ ነት ሀብቶቻቸውን እንደሚያጡ እና ወደ እስር ቤት ዘብጥያ እንደሚጣሉ ወይም ደግሞ ወደ ግዞት እን ደሚወርዱ በማስፈራራት ማሳመን ከቻሉ "ምርጫ ዉን" አሸንፈው በስልጣን ላይ ይቆያሉ፡፡ ኢህአዴግ አበዳሪ ድርጅቶቹን እና ለጋሽ ድርጅቶን ኢህአዴግ በስልጣን ላይ የማይኖር ከሆነ በኢትዮጵያ ሰማይ እና ምድር ይገለባበጣል፣ ብሄራዊ ጥቅሞቻቸውም ይቀራሉ በማለት ለማታለል ከቻሉ "ምርጫዉን" አሸንፈው በስልጣን ላይ ይቆያሉ፡፡

በ2007 በሚካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ ኢህአዴግ የሚያሸንፍ ወይም የማያሸንፍ መሆኑን መጠየቅ ጸሐይ ከጠለቀች በኋላ ጨለማ ምድር ላይ ይሰፍ ናል ወይ እንደማለት ያህል ነው፡፡ ለእነርሱ ቀላል ነገር ነው፡፡ የምርጫ ዘረፋ ወንጀል የጨዋታ ደራ ሲነት አቶ መለስ መስርተውታል፡፡ የእርሳቸው ቀሪ ሎሌዎች በአሁኑ ጊዜ ኃላፊነቱን ተረክበዋል፡፡ የወባ ትንኝ ተመራማሪው እና በብርሀን ፍጥነት ወደ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት የተሸሙት እንዲሁም እ.ኤ.አ እስከ 2015 ድረስ በዚሁ የስልጣን እርከን የሚቆዩትን የቴዎድሮስ አድኃኖምን ቀጣይ የጠቅ ላይ ሚኒስትርነት ወንበር በማሞቅ ላይ የሚገኙት የይስሙላው "ጠቅላይ ሚኒስትር" ኃይለማርያም ደሳለኝ እርሳቸው እና ባልደረቦቻቸው የሚያከናው ኗቸው ተግባራት ሁሉ በአቶ መለስ ራዕይ የሚመሩ (በጭፍን) ናቸው በማለት ሌት ከቀን እንደ በቀቀን ደጋግመው ይናገራሉ፡፡ እ.ኤ.አ በ2010 የአቶ መለስ ራዕይ ምርጫውን መቶ በመቶ ማሸነፍ ነበር፡፡ ያንን ራዕይ ሙሉ ለሙሉ በማሸነፍ ለማሳካት የአንድ በመቶ አራት አስረኛ ብቻ ቀርታቸዋለች፡፡

አቶ ኃይለማርያም እና ጓዶቻቸው በአሁኑ ጊዜ ከትልቅ ፈተና ውስጥ ወድቀው ይገኛሉ፡፡ በ2007 የሚካሄደውን ምርጫ ቢያንስ በ150 በመቶ በማሸ ነፍ የአቶ መለስ ባለዕዳነታቸውን ማረጋገጥ አለባ ቸው፡፡ የምርጫ ማሸነፊያ ነጥብ ወሰናቸው ከወር ቃማው 99.6 በመቶ ካነሰ በጣም አሳፋሪ ሁኔታ ነው የሚፈጠረው፡፡ ቢያንስ መቶ በመቶ በማሸነፍ እና አቶ መለስ በኩራት ሲታወሱ እንዲኖሩ ለማድ ረግ አቶ ኃይለማርያም እና ጓደኞቻቸው በ2010 ለገ በሬው ከሰጡት ማዳበሪያ በላይ መለገስ አለባቸው፡ ፡ የገጠር ደኃ ቤተሰቦችን ደምጽ ለመግዛት "ለምር ታማኝት ደህንነት መረብ የሚከፈለውን ክፍያ /Productive safety net payments" ቢያንስ በእጥፍ ማሳደግ አለባቸው፡፡ እንደዚሁም ወጣቶችን ለማ ታለል እና ታማኝነታቸውን በማረጋገጥ ድምጻቸ ውን ለማግኘት እንዲቻል "የማይከሮ ፋይናንስ" ብድር መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም በተጨ ማሪ ለከተማ ኗሪዎች ኮንዶምኒየሞችን ለመስጠት ብዙ የባዶ ቃልኪዳን ተስፋዎችን መስጠት አስፈላጊ ይሆንባቸዋል፡፡

በሚቀጥሉት 11 ወራት ውስጥ ኢህአዴግ እራቁት ገላ ካገኘች የወባ ትንኝ ስራ የበለጠ ጥድፊያ አለባ ቸው። በጥንቃቄ፣ በብልሀት እና ቀስ በቀስ በርካታ የጎሳ ቡድኖችን እርስ በእርስ በማጋጨት እና ጥላቻ እንዲኖር በማድረግ እና በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ደግሞ ድምጽ ለመግዛት በመርጨት የታ ኢምዘዕ ዕቅድ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡ ፡ ቀደም ሲል ስኬታማ የሆኑበትን የከፋፍለህ ግዛ ስልት አጠናክረው ይቀጥሉበታል፡፡ ለሩብ ምዕተ ዓመት የጎሳ ጥላቻ እሳት ላይ ነዳጅ በማርከፍከፍ ስኬታማ ሆነዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሰላማዊ የሆኑ የዩ ኒቨርስቲ ተማሪዎችን በመግደል በጎሳ ጥላቻ ላይ ነዳጅ በመጨመር ላይ ይገኛሉ፡፡ (ከሳምንት ገደማ በፊት ቢቢሲ በኢትዮጵያ ያለው ገዥ አካል ከመና ገሻ ከተማዋ በስተ ምዕራብ በኩል በ80 ማይሎች ርቀት ላይ በምትገኘው አምቦ ከተማ 47 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን መግደሉን መዘገቡን ልብ ይሏል)፡፡ በክ ርስትና እና በእስልምና እምነቶች ተከታዮች መካከል የጥላቻ ነዳጅ ለማርከፍከፍ በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን ይህን ዕኩይ ምግባር ከመፈጸም አይቦዝኑም፡፡ በቆሻሻ እና እርባና የለሽ ማታለሎች የተካኑ ናቸው፡፡

የሀገር ውስጥ ገንዘብ አዳዮቻቸው ማለትም ኢኮኖ ሚውን አንቀው የያዙት የሙስና መጋቢ ወፍራም ዝሆን ደጋፊዎች እገዛ ለማድረግ በመዘጋጀት ወደ እነርሱ ይገርፋሉ፡፡ ከዚህም በላይ ከታኢምዘዕ ጠባ ቂዎች ጋር አንድ ዓይነት ዕጣ ፈንታን ይጋራሉ፡ ፡ በተፈጥሮ አበዳሪ እና ለጋሽ ድርጅቶች እዚህም እዚያም በመርገጥ በመንተባተብ ስለ ነጻ እና ፍትሀዊ ምርጫ ለምንም የማይውሉ የይስሙላ ቃላትን ያዥ ጎደጉዳሉ፡፡ እናም የሚሰጡትን የውጭ እርዳታ እና ብድር ከህግ አግባብ እና ከታቀደለት ዓላማ ውጭ ለፖርቲ ፖለቲካ ጥቅም ሲያውሉት አይተው እንዳ ላዩ በመሆን ጆሮ ዳባ ልበስ ይላሉ፡፡

የምስራች ከጋዜጣ አንባቢያን በመጡ፡-

<<የቀከም ቀንጅ>> የተሰኘች ሳምንታዊ ጋዜጣ በተከየ አቀራረብ በቅርቡ በሀገራችን ወቅታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ተያያዥ ጉዳዮችን ይዛ ከንባብ ትበቃለች። ይጠብቁት!

ሲከለከሉ የነበሩ የባህል ወረርሽኞች ኢትዮጵያውያንን እንዲያደነዝዙ በሩ ተከፍቶላቸዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ የተስፋፋው ሴተኛ አዳሪነትና ሌሎች የባህል ወረርሽኞች ከግንቦት 20/1983 ዓ.ም በኋላ ኢትዮጵያን መዳረሻቸው ያደረጉ ናቸው፡፡ ለስልጣኑ ሲል ጥቃቅን ነገሮችን የሚከለከለው ህወሓት/ኢህአዴግ የባህል ወረርሽኝ ሲያጥለቀልቀን ዝም ያለው ለስልጣኑ ስለማይጎዳ ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱና መብታቸውን አስከብሬላቸዋለሁ ለሚላቸው ሴቶች ጨምሮ ለትውልዱ ደንታ ስለሌለውና አደንዝዞ መግዛት ስለሚፈልግም ነው፡፡

በፖለቲካው መስክ ያለውን ካየን ደግሞ ይበልጡን የባሰ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ በርካታ የተቀናቃኝ (ታጣቂም ሆነ ሰላማዊ) የፖለቲካ ቡድኖችን ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ ከ40 ሺህ በላይ የሚሆኑ አርምኖና ተናጋሪዎች «አነግ» ተብለው ታስረዋል፡፡ ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትና የሌሎች ቡድኖች አባላት የሆኑ በርካታ ኢትዮጵያውያን እስር ቤት ውስጥ ታጉረዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ሴቶች የሚገኙበት ሲሆን ወንዶቹ ደግሞ ሴት ልጆች፣ ሚስቶችና እናቶችን የሚያስተዳድሩ፣ የሚረዱና የሚያግዙ ናቸው፡ ፡ በመሆኑም ህወሓት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አብዛኛዎቹን ሴቶች የሚጎዱ ህገ-ወጥ እርምጃዎችን ከመውሰድ አልተቆጠበም፡፡

በኢኮኖሚው መስክ ሴቶች ተጠቃሚ ናቸው ቢባልም ወደ ውጭ የሚሰደዱት እነሱው መሆናቸው ፕሮፖጋንዳው እርባና ቢስ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ይሆናል፡፡ ከ18 አመት በታች የሆኑትን ጨምሮ በርካታ ሴቶች ወደ አረብ፣ ደቡብ አፍሪካና ጎረቤት የአፍሪካ አገራት ይጎርፋሉ፡፡ እነዚህ አብዛኛዎቹ እህቶቻችን ህይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው የሚሰደዱት ግንቦት 20 አመጣው የሚባለው «ለውጥ» ለእነሱ ጠቃሚ ባለመሆኑ እንጂ አገራቸውን ጠልተው አይደለም፡፡ የሚገርመው ደግሞ ለሴቶች መብት ቆሜያለሁ የሚለው ኢህአዴግ በውጭ አገር ችግር ሲደርስባቸው «ህገ-ወጥ» አድርጎ የሚፈርጃቸውና ተገቢውን እርዳታ የማያደርግላቸው መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ በምሳሌ ልጠቅሰው የምችለው ከሳውዲ አረቢያ ተባረው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ መንግስት «ህገ-ወጥ» ተብለው መፈረጃቸውና ለእነሱም ድምጽ ለማሰማት ሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ የወጡ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ መንግስት ፌደራል ፖሊስ ድብደባ የተበተነ ሲሆን ይህ እንደሀገር መደፈራችንን ያየንበት፣ እንደመንግስት ለህዝብ ተቆርቋሪነት ሞራል የጎደለው ግዥ እንዳለን የታዘብንበት ነው፡፡ ታዲያ ከሳውዲዎች ጎን ቆሞ ኢትዮጵያውያንን ህገ-ወጥ ብሎ የሚፈርጅ መንግስት እንዴት ለሴቶች መብት ቆሜያለሁ ሊለን ይችላል?

ምንም እንኳ ኢህአዴግ በተፈጥሮው ዶክመንተሪም ሆነ ሌላ ነገር አጋንኖ የሚያቀርብ ቢሆንም ቀሺ ገብሩ በዶክመንተሪው ላይ ስትናገር ከነበረው ለመረዳት የሚቻለው ወጣቷ ልክ ጥለውት እንደወጡት ሴቶች ትወጣ ካልሆነ ከኢህአዴግ ጋር አብራ መቆየት እንደማይቻል ነው፡፡ ደርግ ያቺን ወጣት በጭካኔ አሰቃይቶ ገድሏል፡፡ በርካቶችን አሰቃይቷቸዋል፡፡ ኢህአዴግ ደግሞ ያንን ስቃይ በዶክመንተሪ እያሳየን የዘመኑን ቀሺዎች ማሰቃየቱን ተያይዞታል፡፡ ለዚህም ባል፣ አባት፣ ልጅና ሌሎች ወንዶች ዘመድ አዝማዳቸው ታስረውባቸው ከማሰቃየት ሴቶች በዚህ ስርዓት ለሚደርስ በደል ጥሩ ምሳሌ ይሆኑናል፡፡ በጋዜጠኝነት ሙያ ተሰማርታ ህዝቧን ባገለገለች ወይዘሮ ሰርካለም ፋሲል ከባሏ ከታዋቂው ጋዜጠኛ እና የፖለቲካ ተንታኝ እስከንድር ነጋ ጋር እስር ቤት ታጉራ እነው እስር ቤት ውስጥ እንድትወልድ ተደርጋለች፡፡ የሴቶች ብቻ ሳይሆን ለወንዶችም የጥንካሬ ምሳሌ የነበረችው ብርቱካን ሚዴቅሳ ኢህአዴግ በከፉ ዓይን ከሚያያቸው ሌሎች የወቅቱ ፖለቲከኞችም በላይ በእስር እንድትማቅቅ ተደርጋለች፡፡

በተመሳሳይ በአሁኑ ወቅት እስር ቤት ውስጥ የምትገኘው ርዕዮት አለሙ ግንቦት 20/1983 ዓ.ም ላይ ስልጣን የተቆናጠጠው ኢህአዴግ በሴቶች ላይ እየፈጸመው ለሚገኘው በደልና ግፍ ማሳያ ነው፡፡ ርዕዮት አለሙ ከእጮኛዋ በተጨማሪ ከዘመድ አዝማድ እንዳትገናኝ ተከልክላለች፡፡ ጡቷ እየደማ ለብዙ ጊዜ ህክምና መከልከሏ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ትውልድም ከቀሽ ገብሩ የማይተናነሱ በርካታ ቆራጥ ሴቶች ለአገራቸው ዴሞክራሲ ራሳቸውን መስዋዕት እያደረጉ ነው፡ ፡ ደርግ ቀሽ ገብሩን አሰቃይቶ ገድሏታል፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን ከወጣ በኋላ በርካታ ከቀሽ ገብሩዎች የሚገባቸውን ቦታ ሳያገኙ ወንዶቹ ስልጣኑን ተቆጣጥረውታል፡፡ እነዚህ የድሮዎቹ ቀሺ ገብሩዎች እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ሴቶች አበሳቸውን እየበሉ ነው፡፡ በተቃራኒው ጦር ሜዳላይ ያልነበሩት በዝምድና፣ በውሽምነት፣ በሚስትነት.....የማይገባቸውን ጥቅም አግኝተው ከስርዓቱ ቁንጮ ወንዶች ጋር ሌሎች ሴቶችን በማስበደል ላይ ናቸው፡፡ አዜብ መስፍንን በምሳሌነት ባነሳ የምሳሳት አይመስለኝም፡፡ የወቅቱ ቀሺ ገብሩዎች ላይ የሚደርሰው ደግሞ ከሁሉም የባሰና መሪር ነው፡፡ በእነ ርዕዮት ላይ የሚፈጸመው አሁን በዞን ዘጠኝ ጦማሪ ማህሌት ፈንታሁንና ጋዜጠኛዋ ኤዶም ተስፋዬ ላይ ተከትሏል፡፡ ሌላኛው የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎንያየንበት የሴቶች ቀን (March 8) በሴቶች ታላቁ ሩጫ ላይ አጋጣሚውን ተጠቅመው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያሰሙ ሴቶች በስርዓቱ የመጀመርያ ተጠቂዎች ሆነዋል፡፡ ነፃነትን እንሻለን፣ ፍትህ የሰፈነባት ኢትዮጵያን እንሻለን፣ የአባቶቻችን ልጆች ነን፣ የጣይቱ ልጆች ነን፣ የአባ ጅፋር ልጆች ነን፣ አታስደፍሩን.... በማለት የቀዘቀዘውን የሴቶች የትግል ተሳትፎ በአንድ እርምጃ ለመቀጠል ባደረጉት እንቅስቃሴ የመንግስት አፀፋ «የጣይቱ ልጆች ነን፣ የምኒልክ ልጆች ነን» አሉ በሚል ክስ ለዘ ቀናት መታሰራቸው የሚታወስ ነው፡፡ በጣም የሚገርመው ግን እነሱ የማን ልጆች እንደሆኑ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያሳዩበት ትይንት ነው፡፡ ይህን ሁሉ የሚያሳየን ግንቦት 20 ለሴቶች ተጠቃሚነትን ሊያመጣ ቀርቶ ለአገራቸው ማበርከት የሚችሉትን አስተዋጽኦ በማከሰስና

በመቀፍደድ ላይ መሆኑን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሺህ እና ሚሊዮን ቀሺ ገብሩዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንቦት 20 ባመጣው ስርዓት ምክንያት ድምጥማጣቸው ጠፍቷል፡፡ አሁንም ብሌጭ ድርግም የሚለውን የሴቶች እንቅስቃሴ ለመምራት የሚጥሩትን ቀሺ ገብሩዎች ለማጥፋት የተለመደውን ህገ-ወጥ እርምጃውን እየወሰደ ይገኛል፡፡

ከገፅ 5 የዞረ ...ግንቦታውያን ...

የቁን ተከትሎ ሻዕቢያ በወቅቱ ሁለተኛዋ የኢትዮጵያ ከተማ የነበረችውን አስመራን ተቆጣጠረ፡፡ አረመኔዎቹ የሻዕቢያ ታጋዮች ኢትዮጵያውያንን እንደ ወራሪ ጠላት መዓት አወረዱባቸው፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ ከአራት ቀን በኋላ ግንቦት 20 አዲስ አበባን ተቆጣጠረ፡፡ አረመኔው ደርግ መሸነፉን ተከትሎ ኢትዮጵያውያን ይህ ወር መልካም ነገር ይዞ ይመጣል ብለው ቢጠብቁም ያመጣው ግን ተቃራኒውን ሆነ፡፡

ግንቦት 20... ጥቁሩ ቀን

በግንቦት ወር የመጀመሪያ ቀናት ሻዕቢያና ህወሓት አሜሪካን ጨምሮ ከምዕራባውያን መንግስታት ጋር ሎንደን ውይይት አድርገው ነበር፡፡ ከዚህ ውይይት ዋና ጭብጥ መካከል አንዱ ኢትዮጵያ የባህር በር ያስፈልጋታል በሚል ከምዕራባዊያኑ በተለይም ከአሜሪካ የተነሳው ሀሳብ ነበር፡፡ ይሁንና መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ የባህር በር እንደማያስፈልጋት ሽንጡን ገትሮ በመከራከር ምን አል ባትም «ለማስተዳደር» በሚፈልጋት አገር ሉዓላዊነትን አሳልፎ የሰጠ የመጀመሪያው መሪ የሚያደርገውን ከሃዲ ነት ፈጸመ፡፡ ግንቦት 21 ቀን ኤርትራ በሻዕቢያ ስር መተዳ ደር ጀመረች፡፡ ያ የተደከመበት፣ በርካታ የሰው ነፍስ የጠ ፋበት ሉዓላዊነት ግብጽ ጀምራው እነ ሶማሊያ፣ ሱዳንና ሌሎች የአረብ አገራት ትኩስ ስንቅ እየቋጠሩላቸውና የደ ርግም ስህተት ተጨምሮበት በአገር አንድነት ላይ በተ ነሱት «ወንበዴዎች» የበላይነት ተጠናቀቀ፡፡ ሉዓላዊነቷ ተደፈረ፡፡

ህወሓትና ሻዕቢያ ስልጣን ከመያዛቸው በፊትም ጀምረው ተሻርከው እንጨት፣ ብረት፣ ቡና፣ ወርቅ፣ ብር፣ ሳይሉ ያገኙትን የኢትዮጵያን ሀብትና ንብረት መዘበሩ፡፡ ከደርግ ጋርም ሆነ ካለፉት ስርዓት ጋር ግን ኙነት አለው ያሉትን ህዝብ ላይ እስራት፣ ግድያና ሌሎች አሰቃቂ እርምጃዎችን ወሰዱ፡፡ እርግጥ ነው ይህ ተባብሮ ኢትዮጵያን የመመዝበር ተግባር በስምምነት አልዘለ ቀም፡፡ ሁለቱ የኢትዮጵያን ምርጫ ሃብት ለማጋበስ በመ ነበራቸው አለመግባባት እርስ በእርስ መነካከስ ጀመሩ፡ ፡ በዚህ የሁለት ጅቦች ጠብ ምክንያትም ህወሓት የሚ ገዛት ኢትዮጵያ ግንቦት 4/1990 ዓ.ም በሻዕቢያ ተወረ ረች፡፡ በሁለቱ ግለሰቦች፣ ፓርቲዎች ኢኮኖሚያዊና ድሮ ኢትዮጵያን ለመነጣጠል በርሃ በነበሩበት ወቅት በተፈ ጠረ ቁርሾ 70 ሺ ያህል ህዝብ በዚህ ወርሃ ግንቦት በተፈ ጠረ ግጭት ሰበብ ውድ ህይወቱን አጣ፡፡ በዚህ ግጭት ምክንያት በርካታ ኢትዮጵያውያን ጥርሳቸው ሳይቀር እየ ተነቀለ ከአስመራ ተባረሩ፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግም ቢሆን ያ አብዛኛውን ተማባሩን ካስተማረው ሻዕቢያ በቀሰመው ተሞክሮ መሰረት ምላሹን ሰጠ፡፡

ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ እርዳታ ለመ ለመን እከተለዋለሁ ካለው የይስሙላ ዴሞክራሲ ስም አፋኝነቱን ያሰፈነ ድርጅት ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ጥቅም

ይልቅ የራሱንና የሻዕቢያ ጥቅም አስቀድሟል፡፡ ኢትዮጵ ያውያንን በዘውግ ከፋፍሎ መግዛትን እንደዋነኛ ስልት ወስዶታል፡፡ የይስሙላህ ዴሞክራሲና ምርጫ አሰፈንኩ ቢልም ከመግገደያት ያለፈ ግን አልነበረም፡፡ ለዚህም ህወሓት/ኢህአዴግ ስቃይ እያደረሰበት የሚገኘውን ህዝብ ጥላ ለመሆን በህገ መንግስቱ መሰረት የተቋቋሙት ፓርቲዎችና ፖለቲከኞቻቸው የደረሰባቸውን መከራ ማንሳት በቂ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በየክልሉ አነግና ህወሓት/ኢህአዴግ ሲጨፈጭፉት የነበረውን ኢትዮጵያ ዊና የኢትዮጵያ አንድነት ለመታደግ የተነሳው መዐሕድ የመጀመሪያው ተጠቂ ነበር፡፡ የዚህ ፓርቲ መስራችና እውቁ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ደግሞ የዚህ የግንቦት ዘራሽ አምባገነን ስርዓት ዋነኛ ተጠቂ ናቸው፡፡ ፕሮፌሰሩ እስር ቤት ሲማቅቁ ቆይተው ግንቦት 1/1991 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ የሚገርመው መንግስቱ ኃይ ለማርያም እና ውጫዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች በከፈቱላ ቸው ቀዳዳ በግንቦት ነፋስ ወደ ስልጣን ብቅ ያሉትና የአሁኑ ስርዓት «መሃንዲስ» መለስ ዜናዊም በዚሁ የደም ወር እውቁ ፕሮፌሰር ተሰቃይተው በሞቱበት ቀን የተወ ለዱ መሆናቸው ነው፡፡

ፕሮፌሰሩ ከሞቱ በኋላ የመዐሕድ አካል የነበሩም ሆነ ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች በ1997 ተጠናክረው በአዲስ ምዕራፍ ለትግል የመጡበት ዘመን ነበር፡፡ በተለይ የግ ንቦት 1997 ምርጫ ኢትዮጵያውያን ካሉበት አምባገነ ናዊ አገዛዝ ነጻ እንዲሚያወጣ በኢትዮጵያውያኑ ብቻ ሳይሆን ህወሓት/ኢህአዴግ ለኢትዮጵያ፣ ለቀጠናውና ለዓለምም እንደማይመጥንና እንደማይበጅ በተረዳው ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ተስፋ ተጥሎበት ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያን በታሪክቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በምርጫ ነጻ ለመውጣት በሙሉ ልብ ወደ ምርጫ ጣቢያ የነረቃ ትም በዚህ ቀን ነው፡፡ የሚያዝያው ሰልፍና ሌሎች መነ ቃቂያዎች ግንቦት 7 ኢትዮጵያውያንን ነጻ የምታወጣ ቀን አስመስሏታል፡፡ እነዚያ ንፍሮ ቀቅለው፣ ቡና አፍል ተው ግንቦት ከፉውን ይዞ እንዳይመጣ ተስፋ ሳይቆረጡ ሲሌምኑ የኖሩት ኢትዮጵያውያን አሁን አዲስ ተስፋ ሰን ቀዋል፡፡ ተስፋው ከአንድ ቀን በላይ አልዘለለም እንጂ፡፡

ተቃዋሚ አጣን ሲሉ የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ማታ ላይ ብቅ ብለው ይህን የግንቦት 7 ተስፋ አቧራ ነስነሱ በት፡፡ ማታ በኢቲቪ ብቅ ብለው አሁንም ድረስ ኢት ዮጵያውያንን ለቀየደው የጸረ ሽብር፣ የሲቪክ ማህበ ራት፣ የሚዲያ.....ሌሎች ቀያጅ አዋጆች መሰረት የሆነ ውን ጊዜያዊ አዋጅ አወጁ፡፡ በነጋታው ግንቦት 8/1997 ህዝብ ከቤት ውጭ ምንም አይነት ስብሰባም ሆነ እንቅ ስቃሴ እንዳያደርግ ተከለከለ፡፡ በዚሁ ቀን «አብዮታዊ» ፓርቲው ምርጫ ቦርድ ምንም ባላሳወቀበት ግንቦት 8 ከአዲስ አበባ ውጭ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ማሻነፉን በተቆጣጠረው ሚዲያ አሳወቀ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሰ ላማዊ ትግልን የቀፈደዱ በርካታ እርምጃዎች በዚሁና በቀጣዩ ግንቦቶች ተወስደዋል፡፡ ግንቦት 2002 ዓ.ም ምርጫ ደግሞ አፋኝነቱን ያጠናከረው ኢህአዴግ አስፈ ራርቶም፣ አጭበርብሮም 99.6 በመቶ አሸንፎ «አውራ ነኝ» ያለበትን ኢትዮጵያውያንን በግዥነት እንደሚቀጥል ያቀደበት ወቅት ሆነ፡፡

በአጠቃላይ ግንቦት 20 ህወሓት/ኢህአዴግ ሳይገባው፣ ለኢትዮጵያውያን ሳያስብና ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ኢት ዮጵያን የተቆጣጠረበት፣ በኢትዮጵያውያን ላይ ፕ/ር መስፍን እንደሚሉት «ህገ ራራዊት» መተግበር የጀመ ረበት፣ ዓለም አንድ በሆነችበት ወቅት መገንጠልን በወ ርቃማ መብትነት ያጸደቀበት፣ ኢትዮጵያውያን አገራ ቸው ውስጥ እንዳይዘዋወሩ የማንነት ግንብ የገነባበት ጥቁር ቀን ነው፡፡ በተለይ ከኢትዮጵያዊ አላማ ያፈነገጠ መሆኑ፣ ኢትዮጵያው ያንን በስስ ማንነት መከፋፈሉ፣ ለራሱ ቡድናዊ ጥቅም መሯሯጡ ህወሓት/ ኢህአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረ በትን ቀን ለኢትዮጵያውያን ጨለማ፣ አዲስ የጭቆና ዘመን ነው፡፡ ይህን ቀን ምናልባትም የጀርመኑ ሂትለር ለቤል ጀም ሳይሆን ለራሱ የስልጣንና ልሂቃን ጥቅም፣ በበላይነት ተወጥሮ ቤልጀ ምን ከወረረበት የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ግንቦት 1940 ተመሳሳይ ወቅት (ግንቦት 20) ጋር ማመሳሰል ይቻላል፡፡ እንዲያውም ናዚዎቹ የጀርመንን ጥቅም ለማስጠበቅ፣ ቤልጀምን ሰጥ ለጥ አድ ርገው ለመግዛት ግልጽ አላማ ይዘው ነው የገቡት፡፡ ህወሓት ግን እስካሁንም ድረስ፣ ለባለፉት 23 አመታት የሚጠላ ትን አገር የገንጣይ ስምና አላማውን እን ዳነገበ እየገዛት ይኖሯል፡፡ አሁንም ድረስ ኢትዮጵያውያን ንፍሮ አንፍረው፣ ቡና አፍልተው «መከረኛውን» አምላካ ቸውን መለመናቸው ቀጥለዋል፡፡ ግንቦት የሰጠው «አብ ዮታዊ» ፓርቲ ግን በከፍፍለህ ግዛ፣ በስራትና ግርፋት፣ በኑሮ ውድነት፣ በመሰረታዊ አገልግሎት እጥረት፣ በሙስና ኢትዮጵያን የመከራ ምድር አድርጓታል፡፡ ግንቦት ደግሞ በአየር ንብረት ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ውም ውጥንቅጡ የወጣ ክፉ ወር ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ይህም ነው ግንቦት አሁንም የህወሓት/ኢህአዴግ እንጂ የኢት ዮጵያውያን ወር አይደለም ለማለት የሚያስደፍረው፡፡

የግንቦት 20 ልጆች

ዮናታን ተስፋዬ

ባለፉት 23 ዓመታት ህወሓት/ኢህአዴግ ሀገራችን ኢትዮጵያን ቆራጭ ፈላጭ ሆኖ ሲገዛ እዚህ ደርሷል፡ ፡ በነዚህ ዓመታት ውስጥ የተወለዱ ኢትዮጵያዊያን ታዲያ የሀገሪቱን መቶ ሰባኛ በአብላጫው ይሸፍኑ ታል፤ እድሜያቸው በ20ዎቹ መጀመሪያ ላይ ያሉ ወጣቶች፡፡ ለዛሬ ጽሁፌ መነሻ የሆነኝ ይህ የህብረተ ሰብ ክፍል በሀገራችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስተጋብር ያለው ሚና ነው፡፡

ይህ ሰፊውን ማህበረሰብ የሚሸፍን ክፍል የዚህ ትውልድ ዋና ነፀብራቅ ነው፡፡ በ60ዎቹ አብዮት ያስነ ሳውን ትውልድ በጥቅል ‹ያ ትውልድ› እያልን በዘመኑ ለነበሩት በጎም ይሁን ክፉ ተግባራት እንደምናነሳው ሁሉ ይህ ትውልድም በአሁኑ ሰዓት ሀገሪቷ ላለችበት አስጊ ሁኔታ ተጠያቂነቱን የድርሻውን መውሰዱ ግድ ነው፡፡ ያም ቢሆን ታሪክ በቅብብሎሽ ውስጥ ያለ የክ ስተቶች ጥርቅም ነውና ስለዛሬው ትውልድ ስናነሳ እና ስንጥል ያ ያለፈው ትውልድ ያቀበለውን ወይም የነፈገውን አብረን እያነሳን ለክስተቶቹ ተጠያቂነቱን በተገቢው መልኩ ልናስቀምጥ እንችላለን፡፡

በእርግጥ ከዚህ በተፃራሪ በርካታ ጸሃፊዎች ይህን ትውልድ ካለፈው ጋር በማነፃፀር ሲኮንኑትና ሲያ ማርሩት መስማት አሁን አሁን ተራ የለት ተዕለት አፍ ማሟሻ ሆኗል፡፡ በዚህ ክስ ራሳቸውን የጠመቁ ብዕራቸው የማይነጥፍ ሁሉን በቀደመው ስርዓት መነፅር እየቃኙ የሚመዘኑ አታካቾችም ቀላል አይ ደሉም፡፡ እውነት ነው ያ ትውልድ ደረቅና ከኔ በላይ ባይ ቢሆንም ቁርጠኛና በአልባሌ ጊዜውን የማያባ ክን ነበር፡፡ እውነት ነው ያ ትውልድ የዓለማ ሰው የሞላበት ነበር፡፡ ነገር ግን በግትርነቱና ባህልና ወግ ልምዱን ሁሉ ወዲያ ገፍቶ በመጤ ርዕዮተ ዓለም እርስ በእርሱ በመተራረድ ጭዳ ሆኖ አልፏል፡፡ የተረ ፈው እኩሌታው ገድሎ ስልጣኑን ሲይዝ እኩሌታው ደግሞ በባሌና ቦሌ አድርጎ ተሰዷል፡፡ አንድ ሙሉ ትውልድ ባለመደማመጡ ምክንያት ለትውልድ ቅብ ብሎሽ የሚሆን ድልድይ በቅጡ ሳያበጃጅ አዲሱ ትውልድ ጎምርቶ 20ዎቹን እያለፈ ነው፡፡

ይህ አዲሱ ትውልድ፣ ይህ የኛ ትውልድ ደግሞ ገሚሱ የኋላውን ፍሊጋ ሲኳትን ሌላው ደግሞ መሰረቱ ጠፍቶት ልቡ ማዶ እየሸሸፈተ በባዕድ ዛቢያ ይሸከረከራል፡፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የማህበረ መንግስት መበስበስ እና ሴራ የሚደቁ ሰው ሳይበቃ በረቀቀ ሁኔታ ዓለማቀፋዊነትና ዘመና ዊነት በማንነቱ ላይ ይህ ነው የማይባል አደጋ ደቅ ነውበታል፡፡ እንግዲህ በነዚህ መሃል የተከሰተው ይህ ትውልድ የህወሓት ዘመነ መንግስት ከጀሌዎቹ የዘመን ተጋሪዎቹ ጋር በጋራ የጫነበት ጎተራ ሙሉ ችግርና ዘመኑ በሚፈጥረው ተግዳሮት ውስጥ ታጥሮ የሚኖር ያልታደለ ትውልድ ነው፡፡ ለመራራ ትግል እንጂ ለድሎት (መንፈሳዊ) አልተፈጠረም፡፡ ከዚህ አንፃር የግንቦት 20 ልጆች እንደሀገራችን ፖለቲካ መልካችንና አይነታችን ውስብስብ ነው፡፡ እስቲ በእኔ እይታ ትኝሽ ስለ ዘመን ተጋሪዎቼ ላስቃኝችሁ፡-

ጎጠኝነት

ህወሓት/ኢህአዴግ 1983 ዓ.ም ግንቦት 20 አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ጀምሮ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያጣበት ዋና ነገር ጎጠኝነቱና ጠባብነቱ ነው፡፡ ይህ ኋላ ቀር አስተሳሰቡ በጊዜው ተራማጅ ከነበሩ እና መሰል ጠባብ አስተሳሰብ ካላቸው አካላት ጋር እና ከሶታል፡፡ በየመፅሄቱ በስፋት የሚተችበት የሚኮነን በት ጎሰኝነቱ ግን ከደም ካጥንቱ የተጋባ ይመስል እስ ከዛሬ ድረስ ሊተወው አልተቻለውም፡፡ ይህ ከትንሽ ነት የሚመነጭ የጠባብ ቡድናዊነት አስተሳሰብ የሚ ጠላውን እና የሚወዝወዝን ያህል ግን ሊከስምም ሆነ ሊቀንስ አልቻለም፡፡ እንዳውም ይብሱኑ በአንድ ለአናቱ የቴሌቪዥን ጣቢያ (ኢቲቪ) 24/7 ጠባብ ነት ለ23 ዓመት ተዘምሮለታል፡፡ ‹የኢትዮጵያ ቴሌ ቪዥን› ቢባልም ስሙ ግብሩ ግን ከኢትዮጵያዊነት እጅግ ያፈነገጠ ነው፡፡ ታዲያ ይህ ቴሌቪዥን ጣቢያ ስንቶቻቸንን ነው ለአቅሙ አዳም እና ሔዋን ብሎም ለአቅመ ፖለቲካ ያደረሰን? ይህ ብቻ ሳይሆን በት ምህርት ፖሊሲ (አማርኛ የ«አምሐሬ» የተባለ ጎሳ ቋንቋ ነው፡ የተስፋፊዎች ነው፣ የነፍጠኞች ነው፣ የመሳሰሉትን ምክንያቶች በመደርደር ለአንድነት ሁነኛ ሚና የሚጫወተውን ብሔራዊ ቋንቋችንን በማዳከም ሌላውን እስከዛሬ ተረግጠህ በሚል ጠባ ብነትን በማጥመቅ)፣ በአሉባልታ መልክ በሚነዙ መርዘኛ መረጃዎች (ለምሳሌ-እቃ ወደ ቀበሌ ትግሬ ወደ መቀሌ፣ ምኒልክ የሸዋ ንጉስ ናቸው፣ ኦሮሞ ላይ ወረራ ፈፅመው ጡት ቆርጠዋል...)፣ ታሪክን አጣሞ በማቅረብ (የአክሱም ሐውልት ለወላይታ ህዝብ ምኑ ነው፣ ኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ ያላት ሀገር ናት፣ ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ተገዛች ....) እና በመሳሰሉት መልኩ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ወጣቶች በጠ ባብነት ልክፍት ተከትኩተው አድገዋል፡፡

ዛሬ በአንዳንድ የሀገራችን ክፍል እና በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የዚህ መሰሉ የገዘው ፓርቲ ፕሮፖጋ ንዳ ፍሬ ማፍራቱን ህያዉ ምስክር ሆነው እያየናቸው ነው፡፡ በፖለቲካ ድርጅቶችም ሳይቀር በጎሳ ተከፋፍ ለው አንዴ ህብረት ሌላ ጊዜ መድረክ እየተሰኙ የኢ ህአዴግ «ኮፒ-ፔስት» ጠባብ ፖለቲከኛ አራማጆች የግንቦት 20 ልጆችም የዚህ አጫፋሪዎች ሆነን ዘመን ተጋርተናል፡፡ በማህበራዊ ድረ-ገፅ ያለው የጎሳ ጥዝጥ ዝም አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ደግነቱ ከክምፒተር ጀርባ መሆናችን በጀን እንጂ ስንቱ በጎሰኝነት ናላው የዞረ በቀረርቶ ደፍቶ በጣለን ነበር፡፡

ሆድ አደርነት

ሌላው የግንቦት 20 ልጆች መገለጫ ህሊናውን ሸጦ የበላ፣ የተላላኪነትና የታዛዥነት መንፈስ የተጠናወ ተው የትውልዱ ክፍል ነው፡፡ ይህ ክፍል ከጎጠኞቹ ወጣቶች ላቅ ያለ ቁጥር ያለው ሲሆን ከጠባብነት ጋር ያለው ንክኪም የሚተው አይደለም፡፡ ዛሬ ዛሬ የኪድሬ መመዘኛና መመልመያ ከሆኑት መስፈር ቶች አንዱ ሆዳምነት ሆኗል፡፡ እድሜያችንን ሙሉ ያጭበረበረ አንጂ የደከመ ሀብት ንብረት የማያፈራ ባት ሀገር ላይ እንድንኖር የተጨማለቀ ስርዓት በመ ዘርጋት ህወሓት/ኢህአዴግ ለዚህ ከፍተኛ ጥረት አድ ርጓል፡፡ ታዲያ ወጣቱ ከማን ምን ይማር? በዚህም ሆዱ እንጂ ህሊናው ግድ የማይለው ትውልድ እንዲ ፈጠር አይነተኛ በር ከፋች ከህወሓት ሌላ ፍፁም አል ነበረም፡፡ የምናጠናውን የትምህርት አይነት እንኳን የምንመርጠው ያበላሃል፣ ያበላሻል በሚል መስፈ ርት ብቻ መሆኑ ከሆድ በላይ ላሳር ያለ ለመሆኑ ማረ ጋገጫ ነው፤ እድሜ ለትምህርት ስርዓቱ፡፡ የጅማ ደን ሲጨፈጨፍ፣ የአዶላ ወርቅ ሲዘረፍ፣ ሰንጋቅ አላማ ጨርቅ ነው ተብሎ በመሪው ሲዘለፍና ሲዘ ቀዘቅ፣ ጋዜጠኛ ሲታሰር ስንት ጉድ ጆሯችን ሲሰማ የዚህ ክፍል አካል ወጣቶች ግን ሆዳቸው ካልጎደ ለባቸው እንኳን ‘ለምን?’ ሊሉ እንደውም የጨቋ ኞች ተባባሪ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ከነሱ ብሰው ጨቋኝ ሲሆኑ ማየት እንግዳ አይደለም፡፡ ሆድ ነዋ! ለሆድ ሲሉ ህሊና ያለው ሰው ሊያስበው የማይችል ጥፋት ይፈፅማሉ፡፡ ለሆዳቸው ሲሉ የማያምኑበትን ሁሉ እንዲያደርጉ ይገደዳሉ፣ ያስገድዳሉ፣ ይላላካሉ፣ ይልካሉ ብቻ ሆዳቸው ይሙላ፡፡ ድርጅቶችን ለአሳ ዳሪያቸው ይሰልላሉ፣ እውቀታቸውን ማህበረሰቡን በከፋት ጎዳና ለማስኬድ ይጠቀሙበታል፡፡ ያነባሉ፡ ፡ ለሆዳቸው የሚበጀውን እየመረጡ ልቅም አድር ገው ያነባሉ፡፡ የዚህ ክፍል ወጣቶች ከተራ ሰውነት ባንድ ጊዜ የናጠጡ ሀብታሞች ሲሆኑ ማየት በህወ ሓት ዘመን ምንም አያስገርምም፡፡ ለዚህም መንገ ዱን እየመራ ኮትኩቶ ያሳይጋቸው የግንቦት 20ው ህወሓት/ኢህአዴግ ሌብነትንና ሆዳምነትን አለማምዶ አብቅቷቸውልና ነው፡፡

ተስፋ ቢስነት

እነዚህኞቹ ከሆድ አዳሪዎች ቢልቁ እንጂ አያንሱም፡ ፡ ሁሉ ነገር ይጨልምባቸዋል፡፡ ማታ በMTV mbc የመሳሰሉት የውጪ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች የሚ ያዩት የቅንጦት ኑሮ ጠዋት ሲነሱ ከሚያፈጡበት ያደፈ ኮርኒስ ላይ ተታኮ የሸረሪት ድር ከሰራ ግድግዳ ጋር ሲነፃፀር የሚፈጥርባቸው የስነ ልቦና ጫና እጅግ አሳሳቢ ነው፡፡ እንኳን ማታ ቲቪው ላይ ያዩትን ያማረ ሻወር ቤት ሊያገኙ ይቅርና ለፊት መታጠ ቢያ ውሃ እንኳን አንድ ጀክ በልመና ሲሆንባቸው ምነው ፈጣሪ ኢትዮጵያዊ ከምታደርገኝ የፈረንጅ ውሻ በሆንኩ የሚሉትን ቤቱ ይቁጠራቸው፡፡ ይህ ያል ተጣጣመ መረጃ እና ነባራዊ እውነት ከቀን ወደ ቀን በሚፈጥረው ጭንቀት ስንቱ ነገው ከሰመ! ስንቱ የአሳ ነባሪ ሆድ የበረሃ ራት ሆነ! ስንቱ በወጣበት ውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ! ይህ የዚህ ትውልድ አካል የሆነ የተስፋ ቢስ ወጣቶች ጎራ በከሰረ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እና በቀቢፀ ተስፋ በመኖር እና በመሞት መሃከል ነው፡፡ የዛሬን ማለፍ ትልቁ አላማው የሆነ፣ እጁ ደንዝዞ ህሊናው ፈዞ ሳይራመድ በምናብ ሩቅ የሚያድር፣ ተስፋው በራሱም በሀገሩም ላይ የተሟጠጠ ምስኪን ወጣት የህወሓት/ኢህአዴግ የከሰረ ፖለቲካ ውጤት ነው፡፡

የማንነት ችግር

ከላይ የጠቀስኩት የጎጠኞቹ ክፍል ማንነቱ ግራ ካጋባው ብዙም አይበላለጥም፡፡ እንደነዚህ አይነ ቶቹ ወጣቶች ሆን ተብሎ በተሰራ እና በዓለማቀፋዊ ነት አስተሳሰብ ምክንያት የተጠቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ የሚኖር አንድ ከቅይጥ ቤተሰብ የተወ ለደ ወጣት ቀበሌ መታወቂያ ይጠይቃል፡፡ ከዛም ጎሳውን እንዲናገር ይገደዳል፡፡ ለዚህ ልጅ ከኢትዮጵ ያዊነት ውጪ የሚያውቀው እሱነቱን የሚገልፀውም ቡድን የለም፡፡ ስለዚህ መንግስት በጎሳህ ካልሆነ በሰውነትህ ወይም በኢትዮጵያዊነትህ አላውቅም፣ አውቄም መታወቂያ አልሰጥህም ሲባል በእርግጥ ማንነቱ ላይ ጥያቄ ማንሳቱ ሳይታለም የተፈታ ነው፡ ፡ በሌላ በኩል ዘመናዊነትና ዓለማቀፋዊነት ልባቸውን ከሚገባው በላይ ሰርቆ ኢትዮጵያዊነታቸውን ያስረሳ ቸው ነገር ግን ከምንም ያላሳረፋቸው የአየር ላይ ተን ሳፋፊዎች በርካታ ናቸው፡፡ ለዚህም የግንቦት 20ው ህወሓት/ኢህአዴግ ይዞት የመጣው ግራ የተማታበት ይህ ነው የማይባል የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ከፍተኛ ድርሻ ይወስዳል፡፡ ዓለምን የሚረዳበት መነፅር ከነ ጠንካሬ ጋር ተዳብሎ አምባገነንነቱ የሚፈጥረው ግር ጠቢጥ በርካቶችን የማንነት ቀውስ ውስጥ ከቶ ያሻ ቸዋል፡፡

በፍርሃት የተተበተበ ትውልድ

የአምባገነኖች ዋና መሳሪያቸው ማሰር መግደል ከዚህም የተቀረውን ማስፈራራት ነው፡፡ ይኸውም ህወሓት/ኢህአዴግ ኢትዮጵያን መግዛት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ሳይታክት በመግደል፣ በማሰር፣ በማገላታት እና በማግለል በዙ ወጣቶች በፍ ርሃት አኮፋዳ ተሸብበው እንዲኖሩ በግንቦት 20 ስም እየማለ አገዛዙን ያራዝማል፡፡

የትውልዱ ድንዛዜ

24 ሰዓት ኢቲቪ የሚያነበንበውን ከጭንቅላቱ ሞልቶ ሞልቶ ወይ አይፈስ ወይ አይገነፍል ቢቃ ዝም ብሎ መውጣት መግባት፡፡ ጠዋት መነሳት ማታ መተኛት፡ ፡ ሲገኝ ይበላል ሳይገኝ ጥቅልል ብሎ ያድራል፡፡ ቢቃ የ"ዘነደደ" (ይህችን ቃል ከአዳም ረታ ነው የተ ዋስኳት ዘነደደ ዘንዶ ከሚለው ቃል የመጣች ሲሆን እንደ አዳም ረታ አገላለፅ ዘንዶ አንድ ትልቅ እንስሳ አንድ ግዜ ይውጥና ለረዥም ሰዓት ንቅንቅ የለም፡፡ ዝም ብሎ ብቻ ለጥ! ድንዝዝ፡፡ እናም አዳም የዘነደደ ይለዋል፡፡) ይህ ክፍል ቁጥሩ የትየለሌ ነው፡፡ ይዘነድ ዳል አይቶ፣ አይቶ፣ ይሞላና ይተኛል፡፡ ቢቃ ይኸው ነው፡፡ የግንቦት 20ው ህወሓት/ኢህአዴግ ለእውቀት ባለው ንቀት የተረፈን የትውልዱ አንድ ክፍል፣ የደነ ዘዘ፡፡

ፋና ወጊ

ከዚህ ሁሉ በቁጥር እጅግ የሚያንሱት ደግሞ የኋላ ቸውን በአስተዳደግም ሆነ በጥረት ፈልገው ያገኙና መጪውን አሻግረው ያስተዋሉ ናቸው፡፡ ገሚሶቹ ፖለቲካውን በመቀላቀል ደፋ ቀና ሲሉ ገሚሶቹ ደግሞ ህዝብን በጋዜጠኝነት በማስተማር ብዙ መስ ዋዕትነትን እየከፈሉ ይገኛሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በተ ለያየ ሙያም ላይ ሆነው በገባቸው መጠን ለሌላው ብርሃን ለመሆን ከእውነት ጎን ይሰለፋሉ፡፡ እነዚህ ወጣቶች ግን ፈተናቸው ብዙ ነው፡፡ ከላይ በጠቃቀስ ኳቸው ጎጠኞች፣ አድርባይ፣ ሆድ አደሮች ይዘለፋሉ፣ ይገፋሉ፡፡ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጫና ይደርስባ ቸዋል፤ ሲልም ለእንግልትና እስር ይዳረጋሉ፡፡ በዚህ አልመለስ ያሉት ደግሞ እንዲገደሉ ይፈረድባቸዋል፡ ፡ ምክንያቱም የግንቦት 20ው ህወሓት/ኢህአዴግ አያ ውቃቸውም፡፡ አይፈልጋቸውም፤ አይመቹትም ሰላም አይሰጡትም፡፡ እርግጥ ነው እውነት ለሀሰተኞች አት መችም፡፡ ለዛ ነው እነዚህ ወጣቶች በብዙ ከፍና ዝቅ የማለፍ ግዴታቸውን የሚወጡት፡፡ የዚህ ክፍል ወጣቶች በሄዱበት ሁሉ የደነዘዘውን ለማንቃት፣ የፈ ራውን ለማጀገን፣ ሆዱ የገነነበትን ህሊናው ላይ ደወል በማቃጨል ለለውጥ ይተጋሉ፤ በተስፋ ለነገ መልካም ጥርጊያ ያዘጋጃሉ፡፡ በዚህም ታሪክ ያወሳቸዋል፡፡ ህሊ ናቸው አረፍት ይሰጣቸዋል፡፡ ከትውልዱ የዚህ ክፍል አካል መሆን ምንኛ መታደል ነው!!!

እኔ ፅሁፌን በዚሁ ላብቃ! ታዲያ እንባቢዎቼን በዛሬዋ ቀን በችግራችን ላይ ችግር ጨምረው ሀገራችን የዘ መናዊ ስርዓት እና አስተሳሰብ ባለቤት ለመሆን የምሃ ታደርገውን ትግል ያራዘሙ ቡድኖች የሚዘከሩትን የጥፋት ቀን እንድናወግዝ እና ብሩህ ነገን ለማየት በእ ውነት ፀንተን እንድንታገል፣ ጊዜው መቅረቡን አስተ ውሰን እንድንነቃ ለማስታወስ ወደድኩ!

ከገፅ 8 የዞረ... ሰንደቅዓላማው

ደርግ መሃል ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ ህወሓትን የተቀ ላቀለውና ከዛም ሳይስማማ ቀርቶ ከአገር የወጣው ተስፋዬ ገብረ አብ እነ መለስ ዜናዊ ሰንደቅ አላማውን በህዝብ ለማስጠላት ሲሉ መሃሉ ላይ የአህያ ምልክት ሊያደርጉበት እንደነበር ጽፏል፡፡ በወቅቱ ላይ ላዩን ለማሳመን ቀረበ የተባለው ምክንያትም «የኢትዮጵ ህዝብ በድሮ ዘመን ልክ እንደ አህያ ተጨቁኗል» የሚል ነው ይላል ተስፋዬ ገብረ አብ፡፡

አሁን ኢህአዴግ የሚጠቀምበት ሰንደቅ አላማ ላይ መሃሉ ላይ የተጨመረው ምልክት ከዚህ ከአህያው ክርክር በኋላ የመጣ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ቢሆን በኢ ትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘው ኢህአዴግ ለሰንደቅ አላማው ክብር እንደሌለው ስለሚታወቅና ከኮኩ በስተጀርባ አንዳች እኩይነት እንደሚኖር ስለ ሚጠረጥር ነው፡፡ በቅርቡ የባዕድ አምልኮ አምላኪ የሆኑ ታዋቂ ሙዚቀኞችና ሌሎች ታዋቂ ሰዎች የሚ ያመልኩበት ምልክት ጋር ያያዙት አንዳንድ ኢትዮጵ ያውያን የኢህአዴግ ቁንጮ ባለስልጣናት የዚህ ባዕድ አምልኮ ተከታይ መሆናቸውን በመግለጽ መከራከር ጀምረዋል፡፡

ሰንደቅ አላማውን «ጨርቅ» ያሉት አቶ መለስ መን ግስት ባለፉት ጥቂት አመታት የኢህአዴግ ፕሮፖጋ ንዳ የሚነዛበት የሰንደቅ አላማ ቀን ብሎ ማክበር ቢጀ ምርም ክልብ ነው ብሎ የሚያምን ግን አልተገኘም፡ ፡ ይህ በዓል እየተከበረም ቢሆን አቶ መለስ በአንድ ስብሰባ ወቅት ሰንደቅ አላማውን ከላይ ወደታች መገ ልበጣቸው ደግሞ «ይህ ሰውዬ አሁንም ሆዳቸው ውስጥ ያለውን አወጡት» ተብለው እንዲተቹ ምክ ንያት ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ ከግንቦት 20 በኋላ ከኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ይልቅ የኮሚኒስት ምልክት የተጨመረባ ቸው የፓርቲና ክልል ሰንደቅ አላማዎች በህዝብ አእምሮ ውስጥ እንዲሰርጹ ተደርገዋል፡፡ ኢህአዴግ ራሱ ያወገው ብሄራዊ መዝሙር ሳይሆን በየክልሉ መዝሙር ይዘመራል፡፡ ሰንደቅ አላማዎቹም በየመ ስሪያ ቤቱ ይሰቀላሉ፡፡ የድጋፍ ሰልፍም ሆነ ለሎች ላይ ካድሬዎች ይዘው የሚወጡት የየክልሉን ሰንደቅ አላማ ነው፡፡ ይህም ህዝብ በአንድ ሰንደቅ አላማ ስር ሲሰበሰብ ለኢህአዴግ ስልጣን ችግር ስለሚፈጥርና ከሻዕቢያ የተዋሰው ጸረ ኢትዮጵያውይነት አሁንም ባለመብረዱ ነው፡፡

ግርምቢጥ

መሪጌታ ጽጌ መዝገቡ

“ምን ያለ ዘመን ነው ዘመነ ግርምቢጥ፡

ውሻ ወደ ሰርዶ አህያ ወደ ሊጥ፡፡”

ሆነብን እኮ ጎበዝ! ሥርዓት ካስፈለገና አንድ ህብረተሰብ ይሁነኝ ብሎ ካመነና ከተቀበለ ያመነውን የተቀበለውን ነገር ማክበር ቢዘያም መመራት የግድ ነው፡፡ ወደ ሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ስንመጣ ህዝቦች በጋራ ተስማምተው ያጸደቁትን ሕግ የማያከብሩና የሚዳፍሩ ደግሞ የዚሁ የሥርዓት ተቃራኒዎች ናቸው፡፡ የዚህ ዋና ተቃራኒ ደግሞ መንግስታችን ነው፡፡ መንግሥታችን በሕግ የተደነገጉትን ይጥሳል፣ “የእኔ” በሚላቸው ወገኖችም ያስጥሳል፡፡ በጡንቻ ያስባል፤ የእውቀት ሰዎችን እያሳደደ ዕውቀት የሌላቸውን እንዲያስተምሩ በካድሬነት ይመለምላል፤ ስለፍትሕ የሚሟገቱትን በማስፈርጠጥ ፍርደ ገምድሎችን ይሸማል፡፡ ሥልጣን የህዝብ ነው ከተባለና መፈራራት አስፈላጊ ከሆነ ማን ነው መፍራት መፈራት ያለበት? መንግሥት ወይስ ህዝብ? እንደ ወጉ እንደ ሥርዓቱ ባለሥልጣን ነው መፈራት ያለበት፡፡ ባለሥልጣኑም ህዝብ ነው፡፡ በእኛ ሀገር ግን በተቃራኒው ነው የቆምነው፡፡ ህዝብ ይፈራል፤ መንግሥት ይፍፈራል ወይም ያስፈራራል፡፡ ቅኔውም የሚነግረን ይኸኑ ነው፡፡

ያደጉ ሀገራት ህዝቦች ከእኛ በእጅጉ የሚልቁበት ሁለት ዐበይት ነገሮች አሏቸው፡፡ አንደኛው ሥልጣንን በእጃቸው የጨበጡ ሲሆን የእነርሱ መንግሥት ማለት አገልጋይ ማለት እንጂ ተገልጋይ ወይንም ጭራቅ (አስፈራሪ) ማለት አይደለም፡፡ ሌላውና ዋናው የሚያስቀናኝ ነገር ደግሞ ህግን ያከበራሉ፤ በዚያውም ይምመራሉ፤ ያንንም እንደ ዓይን ብሌናቸው ይጠብቁታል፡፡ ስለዚህም ሥልጡን፣ ንቁና ዘመናዊ ህዝብ የሚል ተቀብዖ ስም ተሰጣቸው፡፡ እንደዚህ ያለ ህዝብ ሊመፍጠር መጀመሪያ ኃለፊነት መውሰድ የነበረበትና ያለበት መንግስት ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ግን የኛ መንግሥታት ሲረግጡን፣ ሲያስፈራሩንና ሲጨቁኑን እንጂ ሲያሰለጥኑን አልታየም፤ አይታይምም፡፡ ዕውነት ነው፡፡ ጥቂት ነገስታት ‹ዘመናዊ› ለማድረግ ጥረዋል፤ ‹ኋላቀርነትን› በእጅጉ ተዋግተዋል፡፡ በዚህ ተግባራቸውም ታሪክና ትውልድ እንደማይረሳቸው እሙን ነው፡፡ ይሁንና በተቃራኒው የቆሙ ኀዙዎች ደግሞ ታሪክ ባይረሳቸውም ትውልድ ግን ሲረግማቸው ይኖራል፡፡ በጥቅሉ ግን መንግሥታችንም ሆነ እኛ በተጻራሪው ማንነዱን ትተን በህግ፣ በሥርዓትና በዕውነት መመላለስ አለብን፡፡ ይቆየን!

መወድስ

መገብተ አእምሮ ንጠይቅ ከመ ተወለጠ፣

ነገረ ተፈጥሮ ዘቅድም በዘዚአነ ዘመን፡፡

አምጣነ መሪራኑ ኮኑ ጥዑማነ ፍሬ አውያን፡፡

ወኢኀልቀ ፍጻሜሁ፣

እዝነ ሰብእ እንተ ይሬእዮ ከመ ይስማዕ ዐይን…

እስመ እንዘ ሃሎ በዐለ ቀርን፡፡

ለበዐለ ቀርን ወማዕዎ አዕዳገ ጽጋብ በእዝን፡፡

ይትርፍሰ ዘቀዳሚ ከመ ተነግረ በዛኅን፡፡

ምውታን ይዘፍኑ እንዘ ይትቀበሩ ሕያዋን፡፡

ወአመ ያረምሙ አፈ ሊቃውንት ጽግም ወይምን፡፡

ለተርጉሞ መጽሐፍ በተዝሕሮ ተጸውዑ በሐማን፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ (1984)፣ግዕዝ ቅኔያት የሥነ ጥበብ ቅርስ፣ 3ኛ ክፍል ጥበቡ ከነትርጓሜው፡፡

ትርጉም፡- የእውቀት ሹምምንት! የቀድሞ የተፈጥሮ ነገር፣

በእኛ ዘመን እንደተለወጠ እንረዳ፡፡

የፍሬ ጣፋጮች ወይኖች መራሮች ሆነዋልና፡፡

የሰው ጆሮ የሚያየውን ዓይን ይሰማ ዘንድ፣

ባለቀንድ እያለ የጥጋብ አህዮች ባለቀንዱን በጆሮ ወግተዋልና፡፡

የመጀመሪያው በጸጥታ እንደተነገረ ይቅርና፣

ሕያዋን ሲቀበሩ ሙታን ይዘፍናሉና፡፡

የቀኝና የግራ ሊቃውንትም አፍን ዝም ባሰኙ ጊዜ፣

ዲዳወች በትዕቢት መጻሐፍን ለመተርጎም ተጠሩ፡፡

ምስጢር፡- በሰዎች እውቀት የማይሆኑ የሚባሉ ብዙ ገሮች ይለወጣሉ፡፡

የወይን ዛፍ መራራ ፍሬ ሊያፈራ፣ ሰውም በጆሮው ሊያይና

በዐይኑ ሊሰማ፣ ጊዜ የሰጠው አህያ ቀንድ ያለውን በሬ በጆሮው ሊወጋው…. ይችላልና ይህን እንወቅ፡፡ መጀመሪያም በሕወት የሞቱ ክፉዎችና ሰነፎች በደህና ሰዎች መሞት የሚደሰቱ፣ግራና ቀኙን ማመዛዘን የሚችሉ የዕውቀት ሰዎች ተንቀው ዕውቀት የሌላቸው የሚያስተምሩና የሚፈርዱ ከሆነ ይህ ሁሉ ይሆናልና፡፡ ይህ ቅኔ ብዙ አዳዲስ አመለካከቶች አሉት፡፡ በጆሮ ማየትና በዓይን መስማት የባለጊዜ አህዮች በጆሮ መውጋት፣ በሕያዋን ጉዳት የበድኖች መደሰት፣ በአዋቂዎች ፈንታ ዲዳዎች መሠልጠን፣- - - ይህ ሁሉ ብዙ ትርጉም ይሰጠናል፡፡

ቅኔ ምን ያህል ያልታዩ ነገሮችን ለማየት እንደሚያስችል ይህ ቅኔ አመላካች ነው፡፡ በጆሮ ከማየት፣ በዓይን ከመስማት ተነስተን በጭንቅላት መሄድ፣ በጡንቻ ማሳብ፣ በእግር መብላት፣ በእጅ መራመድ፣ በምላስ መተንፈስ፣ በአፍንጫ መቅመስ፣. . .ማለት እንችላን፡፡ እነዚህ የማይመስሉ የሚመስሉ ነገሮች ሊሆኑ የሚችሉበትን፣ ሁኔታ ማቻልን ማለት ከቅኔው ስነሳ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየተከናወነ ያለው ሀቅ ይህ ነው፡፡

ከገፅ 8 የዞረ .. የግንቦት 20 እንክርዳድ …

ለመግባት የሚችሉበት ሁኔታ ጠቧል! የተበደለ ህዝብ አደባባይ ወጥቶ ብሶቱን ለመግለፅ አይችልም! በብዙ ደጅ ጥናት ሰልፍ ቢወጣም ያቀረበው ጥያቄ ከአገዛዙ መልስ አያገኝም!

አገዛዙ ከምርጫ ጋር በተያያዘ በ1997 ዓ.ም 193 ሰዎችን መግደሉን አምኗል፡፡ በብዙ መቶ የሚቆጠሩትን አካል ጎደሎ ማድረጉንም አልካደም፡፡ ይህ ግን እሱ ራሱ ያመነው መሆኑን አንርሳ፡፡ ስንቱን ሚስጥር ገድሎ እንደሆነ ግን አናውቅም፡፡ አገዛዙ መሰሪ ነው፡ ፡ በሥልጣን ላይ ለመቆየት የትኛውንም ዓይንት ኢ-ሕጋዊ ድርጊት ይፈፅማል፡፡ ለማንም ሕይወት ደንታ የለውም፡፡ አገዛዙ አሁንም ዜችን ይገድላል! ሰሞኑን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የተቀሰቀሰውን የተማሪዎች ሠላማዊ ጥያቄ ለማከሸፍ የወሰደው የኃይል እርምጃ ለፀረ ሕጋዊነቱ በቂ ምስክር ነው፡፡ በተጠየቅ የተደራጀ ሰው ሰውን ሳይሆን ሕግ ሰውን የሚስተዳድርበት ሀገር ቢሆን ኖሮ ብእርና ወረቀት ብቻ የያዙ ተማሪዎች ፈፅሞ አይገደሉም ነበር፡፡ በ2 ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ መሆናችን አይዘንጋ! በዚህ ዘመን ሰው እንደ ድኩላ እየታደነ ሲገደል በጣም ያስፈራል! የነፃነት እመቤት በሆነችው በጥንታዊት ኢትዮጵያ ንፁሃን በግፍና በገፍ ሲገደሉ ማየት ለእውነተኛ ኢትዮጵያውያን ዘግናኝ ትርዒት ነው! ይህ ትርዒት ደግሞ የግንቦት 20 ውጤት ነው፡፡ ካድሬዎች ይዘምሩለታል! አዝማሪዎች ይዘፍኑለታል! ታጣቂዎች ይሰለፉለታል! ሽር ጉድ ይሉለታል! ሕግና ህጋዊነትን ያሳጣውን አገዛዝ ያቆለጳጵሱታል! እንክርዳድ ንምር ቷል! የመከራ ነዶ ታስሯል!

የዋጋ ግሽበት

ግንቦት 20 በኢትዮጵያዊያን ታሪክ ተስምቶም ታይቶም በማይታወቅ ደረጃ ከዋጋ ግሽበት ጋር አስተዋውቆናል፡፡ ዛሬ ሰፊው ህዝብ በጥቂት ገንዘብ ምንም ነገር ለመግዛት ከማይችልበት ደረጃ ደርሷል! አገዛዙ በየዓመቱ በከፍተኛ ደረጃ ኢትዮጵያ ሀገራችን እያደገች መሆኗን ይነግረናል፡፡ ሰው ሰውን ረግጦ ለመግዛት ሲባል ይህን ያህል ይዋሻል እንዴ? ምን አይነት ዕድገት ነው? የዋጋ ግሽበት የምርት ዕጥረት ውጤት መሆኑን ማን ሊክድ ይችላል? ካደግን፣ ምርት ከተትረፈረፈ የሸያጭ ዋጋ ይወርዳል፡፡ ሸማቹ በዝቅተኛ ዋጋ የፈለገውን ነገር ይገዛል፡፡ ይሄ በግልፅ ይታወቃል፡፡ አሁን የምናየው ግን ተቃራኒውን ነው፡፡ የሁሉን ምርቶችና ሸቀጦች ዋጋ በጣም ንሯል! ይሄ ምን ያሳያል? በሁሉም ቁሳዊ ምርቶች ዘርፍ እጥረት መኖሩን ያሳያል፡፡ ለዚህ የስነ ሀብት ጠቢብ መሆን አያስፈልግም፡፡ ማንም ሰው በምልከታ ሊረዳው ይችላል፡፡ ገዥዎቻችን ተጨባጭ ነገር ለማስተባበል ለምን እንደሚሞክሩ አይገባንም፡፡ ማንም ደግሞ አይቀበላቸውም፡፡ ራሳቸውን በራሳቸው ያታልላሉ፡፡ ሕዝቡን ለማታለል ፈፅሞ አይችሉም፡፡ ለዘላለም በስልጣን ላይ የሚቆዩበት ሁኔታም አይኖርም፡፡ ዕድገት ባለ መኖሩ በሥነ ሀብት ታሪክ በዓለም ላይ ታይቶ የማ ይታወቅ የዋጋ ግሽት በኢትዮጵያ ምድር ተከስቷል፡ ፡ አቅርቦት ከፍላጎት እጅግ የወረደ በመሆኑ የዋጋ ግሽበት ተፈጥሯል! ግሽበቱ ደግሞ በሁሉም አቅርቦ ቶች ዘርፍ ነው፡፡ ደግሞም ባሻቀበበት አለመርጋቱ ሚስጥሩ ሊገባን አልቻለም፡፡ አገዛዙ ማደጋችንን የሚ ነግረን ምንአልባት በሁለት አህዝ እንደ ካሮት በየአ መቱ ቁልቁል መውረዳችንን ይሆን እንዴ?

ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ህዝብ የኑሮ ደረጃ ከአለት ወደ አለት ሲወርድ ይስተዋላል፡፡ ዛሬ ሰፊው የኢት ዮጵያ ህዝብ በቀን አንዴ ጠግቦ ለመብላት ከማይች ልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ የዋጋ ግሽበቱን መጠን ቃላት አይገልፁትም! ገዥዎቻችን የግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ስልጣን ላይ ሲወጡ በአንድ መቶ ብር ይሸጥ የነበረው አንድ ኩንታል ነጭ ጤፍ ዛሬ በ2 ሺህ ብር ይሸጣል! ሁሉም የምግብ ሰብሎች ዋጋቸ ውን እንደ ጤፍ ኖሯል! የሸቀጥ ምርቶች ዋጋም ከመር ፈና ከምላጭ አንስቶ ቃላት ሊገለፁት በማይችሉበት ደረጃ አሻቅቧል፡፡

> **ምንም ብሩህ ነገር አይታየንም፡ ፡ ከዓመት ዓመት ቁልቁል እየወረ ድን ነው፡፡ ግንቦት 20 ማቅ ለብሰንና አመድ በአናታችን ላይ ነስንሰን ዋይታ የምናሰማት የሀዘን ቀናችን ነው !**

የኢትዮጵያ ሰፊው ህዝብ በአሁኑ ወቅት በውሃና በመብራት እጥርትም ሲሰቃይ ይስተዋላል፡፡ በተ መሳሳይ መልኩ የጤና አገልግሎቶችንም በተገቢው ደረጃ አያገኝም፡፡ ሆስፒታሎችና ክሊኒኮችም በጎሳ የአገዛዛ መርህ የተደራጁ በመሆናቸው በሰብዓዊነት ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት የተዘጋጁ እንዳ ልሆኑ በግልፅ ይታያል! ሥራ አጥነት ስር ሰድዷል፡ ፡ የምሁር ስራ አጥ ደግሞ ኢትዮጵያ መሸከም ከመ ችችለው በላይ ሆኗል፡፡ ምንም ብሩህ ነገር አይታ የንም፡፡ ከዓመት ዓመት ቁልቁል እየወረድን ነው፡ ፡ ግንቦት 20 ማቅ ለብሰንና አመድ በአናታችን ላይ ነስንሰን ዋይታ የምናሰማት የሀዘን ቀናችን ነው! የኢ ትዮጵያ ስደተኞች ዓለምን አጥለቅልቀዋል፡፡ ልመና መለያ ገፅታችን ሆኗል! በመስና በዓለም ላይ ጎልተን እንታወቃለን! አድሷዊ የሥነ ሀብት ክፍል በግልፅ ይታያል፡፡ ሀገር ተቆርሶ ይሸጣል! እርሶ አደሩ ተፈና ቅሎ መሬት ለባዕዳን ይቸበቸባል! ዝሙት አዳሪነት ባህል እየሆነ ሲመጣ ይታያል፡፡ መልካም አስተዳደር ወፈውም እየቀረ ሄዷል! የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ይህች ነች! የዜጎች የመከራ ሀገር ናት! ይህ ሁሉ ስቃይ ደግሞ ግንቦት 20 ያመጣው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የነፃነት ትግል ጥያቄ በተግባር ወቅታዊና አንብጋቢ ሆኗል፡ ፡ ዘንድሮ ግንቦት ሃያን በተለመደው ዋይታና ለቀሶ እናሳልፍ! ለመጭው ዓመት ግን ነፃነታችንን ለማወጅ መነሣት አለብን! የግንቦት ሃያን እንክርዳድ መንግለን ለመጣል እጅ ለእጅ ተያይዘን መነሣት ያለብን አሁን ነው! ዛሬ ነው!

የምርጫ ታሪካችን

ግርማ ሞገስ

በውጭ በሚኖሩት እና በአገር ውስጥ በሚኖሩት የፖለቲካ መሪዎቻችን መካከል ያለውን የምኞት እና የዳኝነት ስከነት መራራቅ አንባቢ ልብ ይበል። ትናትም ሆነ ዛሬ ተመሳሳይ ነው። ስለ ዩክሬን እና ጆርጂያ ከማውራትህ በፊት አቅምህን መገመት አለብህ። ሊሆን የማይችል ነገር አደርጋለሁ ብሎ መናገር ወይንም ሊሳካ የማይችል ትግል መጥራት የሰላም ትግል መሪዎችን ተአማኒነት ያሳጣል። ሰላማዊ ትግሉንም ይጎዳል።

(5) በ1997 ሐምሌ በአቶ ቡልቻ ደመቅሳ የሚመራው የአሮሞ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄም (ኦፌዴን) ከዶክተር በየነ ጴጥሮስ ጋር የሚመሳሰል አቋም እንዳለው ለህዝብ አሳወቀ።

(6) በ1997 ነሐሴ ወር የቅንጅት ውይይት በእንጥልጥል ላይ እንዳለ ቅንጅትና ህብረት የአንድነት (ብሔራዊ) መንግስት ጥሪ አቀረቡ። ይህ የአንድነት (ብሔራዊ) መንግስት ለአንድ አመት ስልጣን ላይ እንደሚቆይና ሌላ ምርጫ እንደሚጠራ አሳብ አቀረቡ። አቶ መለስ ጥሪውን ወዲያውኑ ውድቅ አደረጉት። በዚህን ጊዜ ኢህአዴግ በአጥቂነት ላይ ስለነበር የአንድነት (ብሔራዊ) መንግስት ጥሪው ውድቅ እንደሚደረግ መገመት አያዳግትም።

(7) 1997 ነሐሴ 18 ቀን የምርጫ ታዛቢዎች ዘገባዎች ይፋ ተደረጉ። (1) የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ዘገባ በኢትዮጵያ የተካሄደው ምርጫ የአለም አቀፍ መስፈርትን እንደማያሟላ አሳወቀ። (2) የካርተር ማዕከል ደግሞ የማጣራቱ ሂደቱ ፍትሃዊ እንዳልነበር ቢገልጽም ምርጫው አለም አቀፍ መስፈርትን አያሟላም እስከማለት አለደረሰም።

(8) ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በአውሮፓ አንድነት የቀረበውን ዘገባ እንደማይቀበሉ ከመግለጽ አልፈው በመሄድ የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢዎች ቡድን መሪ የሆኑትን እና ጎመዝን የተቃዋሚ ሽሬክ ናቸው የሚል እና ግለሰቢቱን የሚያንቋሽሽ መጣጥፍ በኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ ላይ አወጡ።

(9) 1997 ነሐሴ 1 እና ጳጉሜ 3 የምርጫ ውጤት ተገለጸ፥ የምርጫ ቦርድ ነሐሴ 1 ቀን ኢህአዴግ ማሸነፉን ገለጸ ጳጉሜ ሶስት ቀን ደግሞ የምርጫውን ውጤት ይፋ አደረገ። የምርጫ ቦርድ ኢህአዴግ 296፣ ቅንጅት 109፣ ህብረት 52፣ ኦፌዴን 11 የፌዴራል ፓርላማ መቀመጫዎች አግኝተዋል ሲል ዘገበ።

*እርግጥ የድምጽ ማጣራቱን ሂደት ተከትሎ የአቶ መለስ ፍጡር የሆነው ምርጫ ቦርድ በጠራው ድጋሚ ምርጫ ተቃዋሚው በተለይ ቅንጅት ግንቦት 7 ቀን የነበረው የፓርላማ መቀመጫ ከ109 በላይ እንደነበር እናስታውሳለን። ያም ሆኖ እንኳን ይኸ ውጤት የሚያሳየን አምባገነኖች በጠሩት ምርጫ ተቃዋሚው መፎካከር እና ከፍተኛ ቁጥር የፓርላማ መቀመጫ ማሸነፍ እንደሚችል ነው። ስለዚህ ምርጫ 97 ከምላ ገደል የሚከተሉትን አስተምሪን ሄዳለች ማለት ይቻላል፥

ተቃዋሚው ከምርጫ በፊት፣ በምርጫ ቀን እና ከምርጫ በኋላ አምባገነኑ ተፎካካሪ ገዢ ፓርቲ ህጋዊነትን ለማግኘት ሊያደርጋቸውን የሚችላቸውን ሁኔታዎች (Scenarios) መርምሮ በቅድሚያ ከተዘጋጀ እና (1) በህብረት በመቆም የአመራር አንድነት ከሰጠ እና በአጨቋች ማቅረብ ጥያቄ አንድ መሆን ከቻለ፣ (2) በምርጫ ቀን ህዝብ (የመንግስት ሰራተኛው ጭምር) በብዛት ወጥቶ ማጭበርበር በሚያስቸግር መጠን በ70 እና በ80 ከመቶ በሆነ ድምጽ ተቃዋሚው እንዲመርጥ እና ድምጹን ከስርቆት እንዲያድን ህዝቡን ካስተማረው፣ (3) በድከተሊን የታነፀ በሚሊዮኖች የሚቆጠር የሰላማዊ ትግል ሰራዊት ቀደም ብሎ አደራጅቶ መምራት ከቻለ፣ (4) በሰላማዊ ትግል የታነጹ የአገር ታዛቢዎች በብዛት አስልጥኖ በየምርጫ ጣቢያው ካሰማራ፣ (5) የምርጫው ግብ የገባቸው እና በሰላማዊ ትግል የታነጹ እጩዎች ካዘጋጀ፣ (6) ከተቻለ የውጭ አገር



ታዛቢዎች በብዛት እንዲገቡ ካደረገ፣ (7) ተቃዋሚው በምርጫ ቢያሸንፍም የመለዮ ለባሹ ተቋሞች ለህገመንግስት ተገዢ ሆነው ስራቸውን እንደሚቀጥሉ በመጠነም ቢሆን ማስተማር ከቻል።

ምርጫ 97 ተቃዋሚው የነበረው የተሻለ አማራጭ በምርጫ ያገኘውን ፖለቲካዊ እና ድርጅታዊ ድል ከነ እንከኑ መቀበል ነበር። የአዲስ አበባን አስተዳደር ተርከቦ በክብር ፓርላማ በመግባት ለምርጫ 2002 ወዲያውኑ ዝግጅት መጀመር ነበር። ያን ከማድረግ ፈንታ ተቃዋሚው የምርጫ 97ን ሂደት በማጓተት ለጥቀን ወደምናየው የ1998 ጥቅምት እና ህዳር ወሮች ዳግማዊ ቀውስ ይገባል። ሰላማዊ ትግሉ በድጋሚ ይመታል። አመራሩም ከጨዋታ ውጭ ይደረጋል። የምርጫ 97 ድል ይባከናል።

ክፍል (4)፥ ምርጫ 97 - ከ1998 መስከረም ወር እስከ 1998 ጥቅምት እና ህዳር ወሮች ዳግማዊ ሁከት * ይህ ጊዜ ህውሃት/ኢህአዴግ ተቃዋሚውን እና ሰላማዊ ትግሉን ይበልጥ በመምታት ከጨዋታ ሊያስወጣቸው በርትቶ የሰራበት ነበር።

(1) 1998 በመስከረም ወር የአባይ ፀሃዬ ንግግር በዋሽንግተን ዲሲ፥ የህውሃት አባል የሆነው አባይ ፀሃዬ አንድ ቀን ለደጋፊዎቻቸው ኢንቨስተሮችን ጨምሮ ሌላ ቀን ደግሞ ለህውሃት አባሎች ስብሰባ አድርጎ የተለያየ መልዕክት አስተላልፎ ሄደ። (ሀ) ለደጋፊዎቹ፣ ከተቃዋሚዎቹ ጋር ተስማምተን አገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እናስገባለን አለ። (ለ) ለህውሃት አባሎች ደግሞ፥ ቅንጅት የሚባለውን ከነጭራሹ ደምስሰን እኛ የምንፈልገውን ቅንጅት፣

> **የቅንጅት አመራር ውሳኔዎች መጠለፍ ጀመሩ። ይኽ ሁኔታ በቅንጅት አመራር ውስጥ እርስ በርስ መጠራጠር ፈጠረ። በቅንጅት ውስጥ መረጃ ለህውሃት/ኢህአዴግ የሚያቀብል ማነው የሚል ጥርጣሬ ተበራከተ**

ታማኝ ተቃዋሚ አድርገን እናስቀምጣለን አለ። ይህ የአባይ ጸሐይ መልዕክት የተወሰደው ለንግግር ካዘጋጀው ጽሑፍ ገጽ 33 ላይ መሆኑን ክፍሉ ታደሰ ግንቦት 7 ገጽ 164 ላይ ያመለክታል።

(2) የቅንጅት አመራር ውሳኔዎች መጠለፍ ጀመሩ። ይኽ ሁኔታ በቅንጅት አመራር ውስጥ እርስ በርስ መጠራጠር ፈጠረ። በቅንጅት ውስጥ መረጃ ለህውሃት/ኢህአዴግ የሚያቀብል ማነው የሚል ጥርጣሬ ተበራከተ።

(3) 1998 መስከረም እስከ ህዳር ወር ውስጥ የቅንጅት ህጋዊ ህልውና ዘመን ማለቁን መንግስት እና ምርጫ ቦርድ አስታወቁ። ቅንጅት በምርጫ ቦርድ እውቅና ሳያገኝ ቀረ። የቅንጅት ህጋዊነቱ ተሰረዘ። ኢዴአፓ ከቅንጅት ተገነጠለ።

(4) ለ1998 መስከረም 23 ቀን ህብረት ሰላማዊ ሰልፍ ጠራ፡፡ ቅንጅት አበረ። የሰላማዊ ሰልፉ ዓላማ ተሰረቀ የተባለውን የህዝብ ድምጽ በማስገደድ ሌላ የማጣራት እርምጃ ወይንም ሌላ ምርጫ ለማድረግ ጥርጊያ መከፈት እንደሆነ እና ይህን ሂደት ኢህአዴግ ካልተቀበለ ወይንም በእርቅ ላይ የተመሰረተ መፍትሄ ካላመጣ በጅርጂያና በዩክሬን እንደሆነው ሁሉ ትግሉ ቀጥሎ ኢህአዴግ ተገዶ ስልጣኑን እንዲለቅ ይደረጋል የሚል ነው። ይኽ አቋም በውጭ የሚኖሩት የህብረት መሪዎች ነበር።

(5) የ1998 መስከረም 23ን ሰልፍ የጠራው ህብረት 1998 መስከረም 21 ቀን ምክር ቤት (ፓርላማ) መግባት አለመግባት በሚለው ጉዳይ ላይ ተሰብስቦ 10 ለ 3 በሆነ ድምጽ አለመግባት ብሎ ወሰነ። የዚህ ውሳኔ አስቂኝ ክፍል መግባት የለብንም ያሉት ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉት ድርጅቶች መሆናቸው ነው። ለመግባት የወሰኑት ዶክተር በየነና ዶክተር መራራ ነበሩ። በዚህ አይነት ለሁለት አመቶች ያህል አብሮ ሲሰራ የነበረው ህብረት ከሁለት ተከፈለ። በዚህ አይነት በአገር ቤት የሚገኘው ህብረት ምክር ቤት ለመግባት ወሰነ።

(6) የመስከረም 23ቱን ሰልፍ ቅንጅት ወረሰ። እንደ አንድነት (ብሔራዊ) መንግስት ይህ ሰላማዊ ሰልፍም ቀደም ሲል የቅንጅት እጀንዳ አልነበረም። የሆነው ሆኖ ቅንጅት ከአባሪነት ወደ ባለቤትነት ተሸጋግሮ የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ ማስተጋባት ጀመረ። አቶ መለስ የሰልፉ አላማ ህገ-መንግስታዊ ባልሆነ መንገድ መንግስት ለመገልበጥ ነው በማለት ሰልፉ ተከለከለ። በብዙ አቅጣጫ በችግር የተከበበው ቅንጅት ሰልፍ ቅንጅት ቀደም ብለው ታስበባቸው ፕላን የተደረጉ ትግሎች በማድረግ ላይ አልነበረም። ግብታዊ ትግሎች በማድረግ ላይ ነበር። ግብታዊ ትግል አደገኛ ነው።

(7) የመስከረም 23 ቀን ሰልፍ ሲከለከል ቅንጅት ከመስከረም 22 ቀን ጀምሮ በቤት ውስት የመቀመጥ ተቃውሞ ለማድረግ ወሰነ። ይህ ውሳኔ በተላለፈ በ3 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ኢህአዴግ ሊወያይ ፈቃደኛ እንደሆነ ተገለጸ። ውይይቱ እንዲጀመር ለጋሽ አገሮች ግፊት አድርገዋል። በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል ውይይት እንደሚጀመር እና የተጠራው በቤት ውስጥ የመቀመጥ አድማው መሰረዙ ይፋ ተደረገ። 1998 መስከረም 22 እሁድ ቀን ተቃዋሚዎችና ኢህአዴግ ለድርድር ተቀመጡ። ድርድሩ እንደተጀመረ ስለስብሰባው አካሄድ ውይይት ተደረገ። ሁሉም ወገኖች ጋዜጣዊ መግለጫ ከመስጠት ተቆጠቡ። ኢህአዴግ ለመወያያ ያቀረባቸው 5ቱንም ነጥቦች ህብረቱና ቅንጅት ተቀበሉ። በእንጻሩ ተቃዋሚው ካቀረባቸው ውስጥ ኢህአዴግ በተወሰኑት ላይ ብቻ ለመወያየት ፈቃደኛ ሆነ። በኢህአዴግ በኩል ቀረቡ የተባሉት አጀንዳዎች፥ (ሀ) ለአገሪቱ ህገመንግስት፣ ህጎችና ተቋማት ተገዢ ስለመሆን፣ (ለ) ራስን የአመጽ ተልዕኮ አንግበው ከሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ማግለል ወይንም መለየት፣ (ሐ) ህጎችና ተቋማታን ህገ መንግስታዊ ባልሆኑ ስሌቶች ለማፍረስ ከመንቀሳቀስ መታቀብ፣ (መ) የህግን የበላይነትና ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን ስለማክበርና (ረ) የግል ሚዲያ አጠቃቀም

ቅንጅትና ህብረት ለውይይት እንዲያዙ ከጠየቁት ውስጥ የተፈቀደላቸው፥ (ሀ) የመንግስት ሚዲያን አጠቃቀም፣ (ለ) እስረኞችን ስለመፍታት፣ (ሐ) የፖለቲካ እስራትን ስለማቆም፣ የተዘጉ ጽፈት ቤቶችን በማመለከትና (መ) በቅርቡ የወጡ የፓርላማና የማዘጋጃ ቤት ህጎች ነበሩ። ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ የተከለከሉ አጀንዳዎች ሲሉ በዕለቱ ያብራሩት፥ (ሀ) የብሔራዊ አንድነት የሽግግር መንግስት ምስረታ፣ (ለ) የምርጫ ግድፈቶችን ዳግም ማጣራት፣ (ሐ) የምርጫ ቦርድን ብቃቱን ብቻ ሳይሆን መዋቅሩንም ጭምር መነጋገር፣ (መ) በሰኔ 1 ቀን የተገደሉትን ኢትዮጵያውያንን በማመለከት ገለልተኛ የሆነ አጣሪ ቡድን እንዲቋቋም፣ (ረ) የፍትህ ስርዓቱን ነጻና ገለልተኛ እንዲሆን የሚሉና (ሠ) ስምንቱን አጀንዳዎች ለማስፈጸም የሚችል አንድ ገለልተኛ ተቋም እንዲቋቋም የሚሉ ነበሩ። ድርድሩ እስከ መስከረም 27 ድረስ ከዘለቀ በኋላ ተቋረጠ።

(8) በ1998 ዓመተ ምህረት መስከረም 22 የጀመረው ድርድር መስከረም 27 ከተጨናገፈ በኋላ ቅንጅት ተንጠልጥሎ የነበረውን ምክር ቤት (ፓርላማ) መግባት አለመግባት የሚለውን ጉዳይ አንስቶ ውይይት ተደረገ። ፓርላማ መግባትን የሚደግፉም የሚቃወሙም አሳባቸውን አቅርበዋል። ድምጽ ገና አልተሰጠም።

በዚህን ጊዜ አሜሪካ አገር በህክምና ላይ የነበሩት ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል ቅንጅት ፓርላማ አይገባም በማለት በዋሽንግተን ዲሲ አሜሪካ በተደረገ አንድ ስብሰባ ላይ መግለጻቸውንና በኢትዮጵያ ህዝብ ተቀባይነት ያጡት አቶ መለስ ዜናዊ ከስልጣናቸው መልቀቅ አለባቸው ማለታቸውን 1998 መስከረም 10 ቀን የታተመውን ኢትዮጵያዊ ርቪው (Ethiopian Review, September 18, 2005) ገለጸ (ክፍሉ ታደሰ፣ ግንቦት 7፣ ገጽ 211)። በቅንጅት ምክር ቤት የነበረው ውይይት አልተቋጨም ነበርና ኢንጅነሩ በአሜሪካ ያደረጉት ንግግር በቅንጅት ውስጥ ውዥንብር ፈጠረ። ኢንጂነሩም ህክምናቸውን አቋርጠው በውይይቱ ለመሳተፍ በመወሰናቸው የተጀመረው ውይይት ውሳኔ ሳይደርስ እንዲጠብቃቸው ደብዳቤ ላኩ።

ወደ ገፅ 15 ዞሯል ...

ኢቲቪ ስለግንቦት 20 እኔ ስለ ግንቦት /1997...

ሳሙኤል አወቀ

ነጻ አውጭው
ወንዝ ወርዶ፣ ወንዝ ወርዶ፣
እንደ ቀረ ሄደ፣
አጥባለሁ እያለ፣ አነጻነሁ ብሎ፣
እሱው ሆነ ባዶ፡፡
የቀንድ አውጣ ኑሮ

(ደራሲና ገጣሚ ይስማዕከ ወርቀ)

ግንቦት 20/1983 ዓ.ም የህወሓት/ኢህአዴግ ሰራዊት ከደደቢት በርሃ የወለደውን ብሶት ይዞ ምኒልክ ቤተ መንግስት የገባበትና ህወሓት መራሹ የኢህአደግ መን ግስት ራሱን ሾሮ ያደረገበት 23ኛ አመት ግንቦት 20/2006 ዓ.ም ሲሆን ግንቦት 7/1997 ዓ.ም ደግሞ የዴሞክራሲ ተስፋ ጭላንጪል የታየበት፣ ለመጀመ ሪያ ጊዜ ህዝቡ መሪዎቹን የመረጠበት እና ለህወሀት መራሹ ኢህአዴግ የተነጠቀበት 9ኛ ዓመት ግጥምጥ ሞሽ... ኢቲቪ ግንቦት 20ን ሲያከብር እኔ ግን ግንቦት 7 እዘከራለሁ፡፡ በምርጫው ምክንያት የሞቱትን፣ የተ ገደሉትን፣ የተሰደዱትን፣ የታሰሩትንና አካላቸውንና ንብረታቸውን ያጡትን እያሰብኩኝ ህወሓት /ኢህአ ዴግ የነጠቀኝን ተስፋ ስለማስመለስ አስባለሁ፡፡

አንድ ጓደኛዬ ስለ ግንቦት 20 ቀን 1983 እና ግንቦት 7 ቀን 1997 አውርቶ አይጠግብም፡፡ «እኔ ያኔ ለግሊጋ ወጣት ነበርሁ ወያኔ ገብታ አዲስ አበባን ስትቆ ጣጠር እሪ.....! ብየ ሳለቅስ ዋልኩ፡፡ ምን እንደታ የኝ እንጃ! ይኸው ወያኔ ያስለቀሰኛል፡፡ ግንቦት 7 ቀን 1997 ምርጫን በደስታ አሳልፌዋለሁ፡፡ ከምር ጫው በኋላም ድጋሚ ጥልቅ ሀዘን ውስጥ እንደገባሁ ነኝ፡፡ ምንጊዜም ግንቦት 7 እና 20 ቀን ሲሆን ሻማ ለኩሽ በምርጫ ለሆነው ሁሉ የህሊና ጸሎት አደርጋ ለሁ------" ይለኛል፡፡

ግንቦት 20 ህዝባዊ በዓል ወይስ------

በእጄ ይገቼ የምገለገልበት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አሳትሞ ያሰራጨው የ2006 ዓ.ም አጀንዳ ከመስ ከረም 01 ቀን እስከ ነሐሴ 2006 ዓ.ም 13 ህዝባዊ በዓላት ተዘርዝረዋል፡፡ «ግንቦት 20 ዴሞክራሲ የተ ጀመረበት ቀን» ይላል፡፡ ሌሎች ሰነዶች ላይ «ደርግ የወደቀበት» ተብሏል፡፡ ግንቦት 20 ግን ህዝባዊ በዓ ላትን ሊያሟ የሚችልበት መመዘኛ አያስማማኝም፡ ፡ ዴሞክራሲ የተጀመረበት ቀን ለማለትም አያስደ ፍርም፡፡ ደርግም ህገ-መንግስት ነበረው፡፡ ደርግም ሸንጎ ነበረው፡፡ አምባገነናዊና ወታደራዊ ስርዓት ነበር እንጂ፡፡ በአንጻራዊነት ህገ-መንግስቱ ከነጉድ ለቱ የአሁኑ የተሸለ ቢሆንም ተግባራዊ ሲሆን ግን አይታይም፡፡ በእኔ ግምት በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ካጣናቸው ዜጎች ባልተናነሰ ሁኔታ በህወሓት/ኢህአ ዴግ የነሳና የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ ምክንያ ስርዓቱ በማሰር፣ በመግደል፣ በማሰደድ፣ በማፈናቀል የፈ ጃቸው ዜጎች ቁጥር ከጦርነት እልቂት በላይ ነው፡ ፡ በመሆኑም ይህ ቀን እንዴት ህዝባዊ ባህል ሊሆን ይችላል?

ለመሆኑ 23 ዓመት በመንግስትነት፣ 37 ዓመት በፓርቲ ነት የፓርቲው ሊ/ር፣ የህገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ያለ ገደብ በሞት እስኪሰናበቱ የቀድሞው ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ አይደሉም? የትኛው ፓርቲና መሪስ በህዝብ፣ ከህዝብ፣ ለህዝብ በሆነ ምርጫ ተጀምሮ ያውቃልና ነው? ደርግ መስከረም 23ን ብሔራዊ በዓል አድርጎ በድምቀት ያከብር ነበር፡፡ ደርግ ሲወድቅ ግን ይህ በዓል አብሮ ቀርቷል፡፡ ህወሓት የካቲት 11ን ያከብ ራል፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ ግንቦት 20ን ያከብራል፡፡ ልዩነቱ በ40 ዓመታት ውስጥ ደርግ ወድቆ ህወሓት/ ኢህአዴግ መተካቱ ብቻ ነው፡፡

ደርግ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም መፈንቅለ መን ግስት አድርጎ ለውጡን ቀልብሶ ለ17 ዓመት ከመፈ ንቅለ መንግስት/አብዮት/ ወታደራዊ እስከ ፋሽዝም አስጨንቆ እየገዛ ደማቅ ብሔራዊ ክብረ በዓል ያደረገ ነበር፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ የካቲት 11 ቀን የሕወሓትን ቀን፣ ግንቦት 20 ቀን ደግሞ የህወሓት/ኢህአዴግን ቀን በብሔራዊ በዓል በከፍተኛ የጦርነት ፕሮፓጋንዳ ያከብራል፡፡ ራሱንም ውጥን፣ ጅምር፣ ማስፋት እና ሞኖፖል ስልት ከአንድ ፓርቲ የበላይነት ወደ አንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት ቀይሮ ያለምንም ስልጣን ገደብ ሲፈልግ «አውራ ፓርቲ ነኝ» ሲፈልግ «ልማታዊ መን ግስት ነኝ» እያለ አፋኝ ህግ እያፀደቀ፣ እያፈነ፣ እያሰ ቃዩ መማዘፍን ቀጥሎበታል፡፡ አውራ ፓርቲውም፣ አውሬ ፓርቲ ሆኖብናል፡፡ ታዲያ ይህ ፕርቲ መማዝት የጀመረበት ግንቦት 20 ስለምንስ የህዝብ በዓል ይሁን? እንዴትስ የዴሞክራሲ ቀን ይባላል?

ህወሃት/ ኢህአደግ ለምን ዓላማ ታገለ?

የህወሓት/ኢህአዴግ ሰነዶች እንደሚያስነበቡት፣ መሪ ዎችም እንደሚመሰክሩት የትግሉ ዓላማ «ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ስር ስለሆነች ነፃ ትውጣ፣ ታላቋን ትግራይ ትመስረት፣ ሰፊው የትግራይ ህዝብ በአማራ ብሔር ስለተጨቆነ/ ብሔራዊ እና ፖለቲካዊ ጭቆና ደርሶበታል፤» በሚል ከትግራይ ህዝብ ፍላጎ ትና እውነታዎች ውጭ በደርግ አገዛዝ እና ግፍ የተ መረረውን ህብረተሰብ አታሎ ለድብቅ አላማ አውሎ የተነሳ ከፋፍለህ ግዛው የነሳ እና የጠባብነት ትግል ነው፡፡ ርዕዮተ ዓለም ብሎ የተነሳለትም ማርክሳዊ-ሌኒናዊ - ማኦ - ሴንቲጋዊ ነው፡፡ ይህ ማለትም የላ ብአደር ርዕዮተ ዓለም ነዉ፡፡ የፖለቲካ አቋሙም ፀረ-ንዑስ ከበርቴ ፋሺዥም፣ ፀረ ብሔራዊ ጭቆና፣ ፀረ ኢምፔሪያልዝም ሲሆን በአጠቃላይ ፀረ አማራ አቋም ይዞ የተነሳ መሆኑን «የወያኔ ሴራ» የተባለው መፅሐፍ እና የህወሓት ማስረጃዎች ከማረጋገጣቸው በተጨማሪ እነ አረጋዊ በርሄ አብራርተዋል፡፡ ህወሀት የራሱን ካርታ ስሎ እና ጥቁር ባንዲራ ይዞ ኢትዮጵ ያን ከዶ ተነስቷል፡፡ / አሁን ቀይ እና ቢጫ ባለኮከብ ነው/፡፡ በ1968 የታተመው የት.ህ.ነ.ኦድ ሰነድም ይህን ሃቅ ያሳያል፡፡

በመጀመሪያ ማ.ገ.ት (ማህበረ ገስ ገስቲ ትግራይ)፣ ቀጥሎ ት.ህ.ሀ.ት (የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት (ከዚያም ህወሓት/ ህዝባዊ አርነት ትግራይ)፣ እያለ ስሙን እየለወጠ፣ እስከ ህወሓት/ኢህአዴግ ደርሶ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ቤተ መንግስቱን ከተቆጣጠረ እንሆ 23 ዓመት ሞላው፡፡ ነሳን መሰረት በማድረግ ኢትዮጵያን ከዶ በማስካድ የተሰለፈው ህወሓት/ኢህአዴግ ቤተ መንግስቱን ሲቆጣጠር ብሶት የወለደው የህወሓት የኢህአደግ ሰራዊት የኢትዮጵ ያን ህዝብ በብሶት ላይ እየቀሰቀሰ ይገኛል፡፡ አሁንም አውራ ፓርቲ ነኝ ብሎ አውሬ ፓርቲያዊ ስርዓት ሆኖ ብናል፡፡ መንግስታዊ የሙስና እና «የኪራይ ሰብሳቢ ነት› ስርዓት አስፍኗል፡፡

«አብዮታዊ ዴሞክራሲ» በተባለው ሰነዱ ህዝቡን ጠባብ፣ ትምክህተኛ፣ ወዳጅ ጠላትና መሐል ሰፋሪ ሲል መድቦታል፡፡ ከዚህ በላይ የከፋፍለህ ግዛ ልክፍት ምን ይሉታል? ኢትዮጵያን የባህር በር እንዳይኖራት ከደደቢት እስከ ቤተመንግስት ታግሏል፡፡ ዜጎቻችን በስደት እንኳ እየተዋረዱ፣ በየበረሃው መቅረታቸው፣ በባህር የሻርክ ቀለብ መሆናቸው ሳያንስ ህገ-ወጥ ስደ ተኞች እያለ በዓለም ህዝብ ፊት ያዋርዳል፡፡ ህወሓት/ ኢህአዴግ ተዋርዶ ለማዋረድ እረፍት የለውም፡፡

የህወሀት/ ኢህአደግ የ37 ዓመት ክሽፈት

ህወሓት/ኢህአዴግ የአፈና ህግ እያወጣ አፍኖ ይገዛል፡፡ ነጻ የፖለቲካ መብት ተፈቅዷል ብሎ አውጆ ነጻ ፕሬስ ሲያቆጠቁጥ እየቀጨ ያስቀምጣል፡፡ ጋዜ ጠኞችን አስር/ውህኒ/ያወርዳል፣ «ቡቾርቸር» ያሰቃ ያል፣ ያሰድዳል፣ ይገድላል፣ ራሳቸውን በሰቆቃ እስኪ ድሉ ግፍ ይሰራል፡፡ የመድብለ ፓርቲና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ይደፍቃል፡፡ ፖለቲከኞን ያሰራል፣ ይገድላል፡፡ በወጣትነት ዕድሜየ ይህንን አጥግቦኛል፡ ፡ ህወሓት/ኢህአዴግ አረማሞ ሰብል ነው፡፡ ምርት አልባነቱ ሳይሆን ብክለቱም አጥፊ ነው፡፡ እግዚኦ! 23 ዓመት እየበከለ አገሪቱን አረማም እንዳረገ ይገኛል፡፡

በድህረ 1983 ጀምሮ የከሸፈው ህወሓት ኢህአዴግ በብሔራዊ ዕርቅ መቋጨት የነበረበትን የሽግግር ጊዜ በሴራና በእምቢተኝነት የመድብለ ፓርቲ ስርዓ ትን ወደ አንድ ፈላጭ ቆራጭ ፓርቲነት እና አንድ ግለሰብ የበላይነት ለውጦ ራሱን አግንኖ በብተና ፖለቲካው ቀጥሏል፡፡ በ1992 ዓ.ም ምርጫ የይስ ሙላ የቀጠለው የህወሓት አገዛዝ በኢትዮ-ኤርትራ በከንቱ ዜጎቹን አስጨራሷል፡፡ በ1993 ዓ.ም በተፈጠ ረው የህወሓት ክፍፍል በኋላ ደግሞ የራሱን ታጋዮች መብላት ጀምሯል፡፡ በ1994 ዓ.ምና ከዚያ ወዲህም ድርቅና ርሀብን በግዴለሽነት አስተናግዷል፡፡ ዜጎችም በርሀብ እየረገፉ አገዛዝን አስቀጥሏል፡፡ በ1997 ዓ.ም ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ የነበረውን የዴሞክራሲ ተስፋ አጨልሞ ንፁሀንን በጠራራ ፀሀይ ጨፍጭፎ፣ ጋዜጠኞችን ፣ ፖለቲከኞን፣ የሰባዊ መብት ተሟቾ ችን አስሮ የፖለቲካ ድርጅቶችን አፍርሷ፡፡ ወጣቶችን በየጦር ካምፑ አደገኛ ቦዘኔ የሚል ስም ሰጥቶ በግፍ አጉሮ አሰቃይቷ፡፡ በዚህ አፈናው በምርጫው የተሸነ ፈው ህወሓት/ኢህአዴግ በሀይል ነግሶ አገዛዙን ልደት በፕሮፖጋንዳ ያከብራል፡፡ የኢትዮጵያ ወታደሮችን በታሪከ ታይቶ በማይታወቅ ውርደት በሶማሌ ምድር ላይ አስከሬናቸው በአስፓልት ላይ ሲጎተት እያየን በውርደት ማቅ ለብሰናል፡፡ ይህ የህወሓት /ኢህአዴግ የግንቦት 20 የድል ፍሬ መሆኑ ነው፡፡ ህወሓት /ኢህ አዴግ በኢቲቪ ሲጨፍር የኢትዮጵያ ህዝብ ግን በግ ንቦት 7/1997 የተነጠቀውን የዴሞክራሲ ተስፋ ያከ ብራል፡፡ በመሆኑም ግንቦት 20 በግንቦት 7/1997 ምርጫ ተደምስሷል፡፡

ግንቦት 20፣ የኢትዮጵያ ገበሬ እና የኢህአዴግ ስርዓት

ህወሓት/ኢህአዴግ ራሱን «ለአርሶ አደር የቆምኩ ፓርቲ ነኝ፡፡» ነገር ግን የኢትዮጵያ ገበሬዎችን ከቀ ያቸው በማፈናቀል መሬታቸውን ነጥቆ በማቀራ መትና በመቀራመት፣ በሰብአዊ መብት በመርገጥ፣ በጎሳና በቋንቋ ከፋፍሎ በመጨቆን ተወዳዳሪ ያልተ ገኘለት አምባገነን ስርዓት ሆኗል፡፡ በሚዲያ እንደም ናዳምጠው፣ ከፅሁፎች እንደምናነበው፣ እንደምንመ ለከተው የኢትዮጵያን መሬት በርካሽ ገንዘብ ለውጭ ሃገር ኢንቨስተር እየሸጠ፣ አርሶአደሮች በገዛ መሬታ ቸው ላይ ተቀጥረው የሚሰቃዩበት በርሃብና በስደት የሚቀጡበት የሚፈናቀሉበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ የኢትዮጵያ መሬት ያስገኘው ምርት ወደ ውጭ ሃገር እየተላከ ኢትዮጵያዊያን ግን በገዛ መሬታቸው ላይ ለበአዳን ተቀጥረው ይማቅቃሉ፡፡ ከእጅ ወደ አፍ የሆ ነውን ኑሮ ለመምራት የውጭ እርዳታ ፍለጋ እጃቸ ውን ይዘረጋሉ፡፡

ህወሓት/ኢህአዴግ በሚከተለው የመሬት ፖለቲካ በቀላሉ እንኳ በአማራ ክልል የተደረገውን የመሬት

> የፖለቲካ አቋሙም ፀረ-ንዑስ ከበርቴ ፋሺዥም፣ ፀረ ብሔራዊ ጭቆና፣ ፀረ ኢምፔሪያልዝም ሲሆን በአጠቃላይ ፀረ አማራ አቋም ይዞ የተነሳ መሆኑን «የወያኔ ሴራ» የተባለው መፅሐፍ እና የህወሓት ማስረጃዎች ከማረጋገጣቸው በተጨማሪ እነ አረጋዊ በርሄ አብራርተዋል፡፡

ድልደላ ፖሊሲውን ለአብነት ብንወስድ ገበሬዎ ችን ለስደት የዳረገ፣ እርስ በእርስ ያጋጨ፣ ፍትሃዊ ያልሆነ ድልደላን በቀመር የማስራብ ስርዓትን ያረጋ ገጠ የመሬት ፖለቲካ በመጠቀም የመሬት ባለቤትነት መብትን ጠቅልሎ በመያዝ ህዝቡ የኢህአዴግ ጭሰኛ እንዲሆን ያደረገ ስርዓት ነው፡፡ አርሶ አደሩ ባለቸው ኩርማን መሬት እንዳይጠቀም በፖለቲካ አመለካ ከቱ እየተለየ በራሱ የመሬቱ ይዞታ ላይ ሰርቶ እንዳ ይኖር የወንጀልና የፍታብሔር ክስ እየተፈበረከበት ይታሰራል፡፡ ያፈራውን ንብረትም በፍ/ቤት ውሳኔ ይዘረፋል፡፡ ይህ የመሬት ፖለቲካ ስርዓቱም አርሶ አደሩን የኢህአዴግ ጭሰኛ አድርጎታል፡፡ በመሬቱ ምክንያትም በገንዘብና በእስር ይቀጣበታል፡፡ ግብር ከአቅሙ በላይ ይከፍልበታል፡፡ ይህ የኢህአዴግ የግን ቦት 20 ፍሬ ነው፡፡ ገበሬው የመሬት ባለቤት መብት እስከሌለው ድረስ የኢህአዴግ ጭሰኛ ነው፡፡ መሬትም የስርዓቱ የስልጣን ማራዘሚያና «የኪራይ ሰብሳቢ ነት» ስርዓት ግንባታውን ያስፋፋሊታል፡፡ ገበሬዎች ኩርማን መሬታቸውን አርሰው ምርት ለማግኘት የግ ብርና ግብአት ቴክኖሎጂና የአፈር ማዳበሪያ ያስፈልጋ ቸዋል፡፡ ይህን አቅራቢው ህወሓት/ኢህአዴግ ነው፡፡ በፖለቲካ አመለካከታቸው አይደግፉም ያላቸውን ገበ ሬዎች ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ እና የግብርና ቴክኖሎጂ እንዳያገኙ ይከላከላል፡፡ ይህ ነው የኢህአዴግና የኢት ዮጵያ ገበሬዎች ግንኙነት ይህ ነው የግንቦት 20 የድል ፍሬ የከፋፍለህ ግዛ ስርዓት

የዘንድሮውን ግንቦት 20 ልዩ የሚያደርገው

ኢህአዴግ በዓል ሲያከብር «የዘንድሮውን በዓል ልዩ የሚያደርገው» እንዲል ለእኔም የዘንድሮውን ግንቦት 20 ህወሓት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ቆርሶ ለመስጠት በድብቅ መፈራረሙ ልዩ ያደርገዋል፡ ፡ በያዝነው የግንቦት ወር የኦሮሚያ ዩንቨርስቲ ተማሪ ዎችን የአህዴድ/ ኢህአዴግ አባላትን በጥይት መረፍ ረፍ ልዩ ያደርገዋል፡፡ መብራት፣ ውሃ፣ ስልክ መቸገ ራችን የኑሮ ውድነት ከዕለት ወደ ዕለት ወደ አስከፊ ደረጃ መድረሱ ልዩ ያደርገዋል፡፡ የመንግስት ሌቦች መባባስ እና የመንግስት ሌብነት አደራጅት መጠናከር፣ የኪራይ ሰብሳቢነትና የመንግስታዊ የሙስና ስርዓት መባባስ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ዜጎች በሚናገሩት ቋንቋ ተለ ይተው እየተፈናቀሉ በስቃይ ላይ መሆናቸው የዘንድ ሮውን ግንቦት 20 ልዩ ያደርገዋል፡፡ በቅርቡ የጋዜጠ ኞች እና ጦማሪዎች ስቃይ እና እስር መባባስ ልዩ ያደ ርገዋል፡፡ መንግስት በኃይማኖት ላይ የሚያደርገው ጣልቃገብነት መባባስና የኃይማኖት መሪዎች ስቃይና እስር የተከታዮች ትግል መቀጣጠል ልዩ ያደርገዋል፡ ፡ አዲስ አበባ በአንበጣ መወረሯ ልዩ የደርገዋል፡፡ የዴሞክራሲ ተቋማት መዘጋትና የአፈና መስፋፋት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የፍትህ፣ የነፃነትና እኩልነት ጥያቄ ተጋግሎ መቀጠሉ እና አይቀሬው ለውጥ መቃረቡ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ሰላማዊ ጥያቄ ለሚያነሳ የህብረተሰብ ክፍል ህወሓት/ ኢህአዴግ መልሱ ማሰር፣ መግረፍ፣ መግደል፣ ማሰቃ የት በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነት ፍላጎት ጣራ ላይ መድረሱ፣ ህወሓት/ ኢህአዴግ የለመደው ኘሮፖ ጋንዳ እና ህዝብን የመከፋፈል ሴራው በዚህ አመት በርካታ ህዝብን ግጭት ውስጥ ማስገባቱና የህወሓት ኢህአዴግ ሴራ ፍሬ ማፍራቱ የዘንድሮውን ግንቦት 20 ልዩ ያደርገዋል፡፡

ኢህአዴግ በብዝበዛ እና በጭቆና፣ በመከፋፈልና በማጋጨት ተጠምዷል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለእኩልነት በብሔራዊ የአንድነት መንፈስ ነቅቶ በተጠንቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ግንቦት 7/1997ን ምርጫ 9ኛ ዓመት የዴሞክ ራሲ ቀን ዳግም ለማብሰር ተዘጋጅቷል፡፡ ህወሓት/ ኢህአዴግ 1983 ላይ ቆሞ ግንቦት 20ን በኘሮፓጋ ንዳ ያከብራል፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግና ግንቦት 20፣ የኢትዮጵያ ህዝብና ግንቦት 7/1997 የምርጫ ታሪክ ደግሞ ተፋጠዋል፡፡ ህወሓት/ኢህአደግ አሁንም ቆም ብሎ ለማሰብ ከፈለገ ትንሽም ቢሆን ጊዜ ያለው ይመ ስላል፡፡

ሰማያዊ በቅርቡ የተገደሉትን ንጹሃን ዜጎች በሻማ ማብራት አሰበ

ፓርቲው ግንቦት 23 የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም አዘጋጅቷል

አዲስ አበባ፡- ሰማያዊ ፓርቲ (ሰማያዊ) በቅርቡ የአዲስ አበባ እና አጎራባች የኦሮሚያ ክልል ከተሞች ፀተቀናጀ መሪ ፕላንንን በመቃወም በሰላማዊ መንገድ ጥያቄያቸውን ባሰሙ ንጹሃን ዜጎች፣ በተለይም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተወሰደውን ግድያ በማውገዝ በህገ-ወጥ እርምጃው ህይወታቸውን ያጡ ዜጎችን በማስመልከት የሻማ ማብራት፣ ጥቁር የመልበስና የውይይት ፕሮግራም አድርጓል፡፡

ሰማያዊ ውይይቱንና የሻማ ማብራት ፕሮግራሙን ያደረገው ባለፈው ቅዳሜ ሲሆን በፕሮግራሙ ላይ የፓርቲው አመራሮች፣ አባላትና በዝግጅቱ ላይ የተገኙት ዜጎች ጥቁር በመልበስ በወገኖቻቸው ላይ በተፈጸመው ግድያ ሀዘናቸውን ገልጸዋል፡፡

በዝግጅቱ ማጠቃለያ ላይ ንግግር ያደረጉት የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢ/ር ይልቃል ጌትነት በሲቪል ዜጎች ላይ የመንግስት የጸጥታ ኃይሎች የወሰዱትን ህገ-ወጥ የግድያ እርምጃ አውግዘዋል፡፡ የዜጎችን ጥያቄ በግድያ ማስቆም አይቻልም ያሉት ኢ/ር ይልቃል መንግስት በንጹሃን ላይ የሚወስደውን መሰል እርምጃ እንዲያቆምም አሳስበዋል፡፡

በሌላ በኩል ሰማያዊ ፓርቲ «ምሽቱን ከሰማያዊዎች ጋር» በሚል ግንቦት 23 ቀን 2006 ዓ.ም የእራት ግብዣ በማድረግ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ማዘጋጀቱን አስታውቋል፡፡ በፓርቲው የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ አስተባባሪነት የተዘጋጀው ይህ ፕሮግራም በአዲስ ቪው ሆቴል እንደሚደረግ ፓርቲው ጨምሮ አስታውቋል፡፡ በዝግጅቱ ላይ የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም ታዋቂ ግለሰቦችና ተጋባዥ እንግዶች እንደሚገኙ ተገልጹዋል፡፡

❖ ከገፅ 16 የዞረ... ሰለባዎች

አብዛኛው ወጣት ነው፡፡ የፐ/ር መሞት ሲነገር አብዛኛው ያልሰማ ነበርና ቤቱ በለቅሶ ተናወጠ፡፡ ሀዘናችንን ተወጥተን እንባችንን ከአበስን በኋላ ድርጅቱ ምን ያደርግ ይሆን? ሌሎቹ ሰዎችስ መንግሥትስ ምን ያደርጉ ይሆን? እኛስ ምን ማድረግ አለብን? ምንስ ማድረግ እንችላለን? በሚል ሰፊ ውይይት ካደረግን በኋላ አስራትን የሚዘከሩ ጽሁፎች ሥነ-ግጥሞች እንዲዘጋጁ፣ ቀብራቸው በደማቅ ሥነ-ሥርዓት እንዲከናወን፣ አስከሬናቸው ከቦሌ እስከ መኖሪያ ቤታቸው በከፍተኛ ድምቀት ታጅቦ እንዲጓዝ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ተስማምተንና አቅደን ተለያየን፡፡

እዛም የመአህድና የፐ/ር አስራት ተቆርቋሪዎች በሚል የሚንሳቀሱትን ሰዎች አግኝተን ምን ማድረግ አለብን? ምንስ ማድረግ እንችላልን? የሚለውን ስን ነጋር በእኛ በኩል ከአስራት የቀብር ሥነ ሥርዓት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚያስብ ወገን ካለ እን ደማንተባበር ገልጸን ይሄው ስምምነት አግኝቶ እቅድ ተነደፈ፣ ምደባ ተካሄደ፣ ገንዘብ ተዋጣ፣ ሥራ ተጀመረ፡፡

ግንቦት 15/1991 ዓ.ም ከዋሽንግተን ጉዞ የጀመረው የፐ/ር ዓሥራት አስከሬን ግንቦት 17/ቀን 1991 ዓም ከጠዋቱ 4፣30 አዲስ አበባ ይገባል ስለተባለ ሁላች ንም ያዘጋጀነውን ጥቁር ጨርቅ ከንዳችን ላይ አስረ ንና በእጅ የሚውለበለብ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ይዘን በጠዋት ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ የሄድነው ፓርቲው በሚያዘጋጀው የአቀባበል ሥነ-ሥርዓት ተካፋይ ለመሆን ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳንድ የፓር ቲው አመራሮች በቦታው ቢኖሩም ምንም ዝግጅት አይታይም፡፡ በመሆኑም የአስራትን አስከሬን እንዲህ በዝምታ መቀበል ተገቢ አይደለም በማለት እዛው ተመካክረን መፈክር ማሰማት፣ ግጥምና ስነ ጽሁፍ ማንበብ ጀመርን፡፡ ለዚሁ ዓላማ ከመጣው ሰው በተ ጨማሪ በአካባቢው ለተለያየ ጉዳይ የተገኘው ሰው እየተቀላቀለን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰው ለቅሶውንም መፈክሩንም አደመቀው፡፡

አስከሬኑን የያዘው አውሮፕላን ግን በተባለው ሰዐት ሊደረስ አልቻለም፡፡ ሰዐታት ባለፉ ቁጥር ሆን ብለው ያደረጉት ነው፣ በጨለማ ሹልክ አድርው ለመውሰድ ፈልገው ነው ከሚለው ጀምሮ የተለያዩ መላ ምቶች ይሰነዘሩ ጀመር፡፡ ይህ ደግሞ ሰዉን ይበልጥ እልህ ውስጥ አስገባው፡፡

በዚህ ሁኔታ ያለምንም ድካም በእልህ ሥነ-ሥርዓቱ ቀጥሎ አውሮፕላኑ 11፡30 ላይ ማረፉ ተሰማ፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ የመአህድ አመራሮች ከመንግስት ጋር በመስማማት አስከሬኑን በፍጥነትና በጸጥታ ይዘው ሊሄዱ ነው የሚል ወሬ ሲሰማ ፈጥነን በመሄድ የመኪና መንገዱን ዘጋን፡፡ አስከሬኑን የጫነው መኪና ብቅ ሲል በለቅሶ፣ በመፈክር፣ በኡኡታ ምድር ተደበላለቀ፡፡ በየትም በኩል መኪናው ሾልኮ እንዳያልፍ በጥንቃቄ በመጠበቅና መንገድ በመዝጋት በቀስታ የእግር ጉዞ ተጀመረ፡፡ በየመንገዱ የሚቀላለው ሰው ቁጥር ጨመረ፡፡ እጃቢ መኪናዎችም ቁጠራቸው እየጨመረ ሄደ፣ የትራፊክ ፖሊሶች ከፊት እየቀደሙ ከቦሌ ወደ መስቀል አደባባይ መምጫውን መንገድ ከፍት አደረጉ፡፡ ጊዜው እየመሸ ሲመጣ ጧፍና ሻማ እየተ ገዛ ተለኮሰ፡፡ በአካል ያልተቀላቀለው በየፎቁ ላይ ሆኖ መፈክር በመቀበልና በመጮህ ጉዞውን አደመቀው፡ ፡ የታጋይ ድምጽ ይጮኻል፣ አትነሳም ወይ፣ ማን ይፈራል ሞት፣ ወዘተ ተዜመ፡፡ የደህንነት ሰራተኞች በመካከላችን ተሰግስገው አስተባባሪ ናቸው ብለው ከገመቱዋቸው ሰዎች ጎን ተጣብቀው የሚባለውን ሁሉ እያሉ ይጓዛሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጉዘን መስቀል አደባባይ ስንደርስ የሰዉ ብዛት የአንድ ወገን መንገድ ከሚችለው በላይ ሆኖ ነበር፡፡ ስፖርት ኮሚሽን ጋር ስንደርስ ከለገሀር አቅጣጫ አድማ በታኝ ፖሊስ የጫነ መኪና መጣና በቅርብ ርቀት ጥግ ይዞ ቆመ፡፡ ከፊት ይመራ የነበረው ትንሽ የፖሊስ መኪና በጣም ተጠግቶን እንደቆመ አንድ የፖሊስ ባለሥልጣን ወርዶ ወደ እኛ መጣ፡፡ ከቦሌ እስከዛ ድረስ ምንም ያለለን ፖሊስ እዛ ጋር ስንደርስ ችግር ይፈጥርብናል ብለን ባለመገመት ሰው ፖሊስ ሲያይ ስሜቱ ግሎ አላስፈላጊ ነገር እንዳይናገር ስናረጋጋ ፖሊሱ ተበተኑ አለ፣ ሰዉም አንበተንም አለ፣ በዚህ ግዜ ወደ ኋላ ዘወር ብሎ በለው ሲል በመኪናው ዙሪያ በተጠንቀቅ አድፍጠው የነበሩት ፖሊሶች ከመቅጽበት ሰፈሩብ ንና በዱላ መጠዝጠዝ ጀመሩ፡፡ ለማምለጥ ሲሞከር ደግሞ ከዋና መንገድ ወደ ውስጥ የሚያስገቡ መን ገዶች ሁሉ በፖሊስ ተይዘዋል፣ የነበረው ምርጫ አንድም ፊት ለፊት ጥሶ ወደ ለገሀር እንደም ወደ ኋላ ተመልሶ ወደ መስቀል አደባባይ መሮጥ ነበር፡፡ የአስከ ሬኑን መኪና የሙጢኝ ብለው የሚያለቅሱት ሳይቀሩ ዱላ ቀምሰዋል፡፡ ብዙዎች ተይዘው በመኪና ተጭነው ኮልፌ የተወሰዱ ኢሰብአዊ የሆነ ድብደባና ቅጣት ተፈጸመባቸው፡፡ ቀኝ አዝማችን በሚቃወሙት ላይ ቅጣቱ ለየትም ከበድም ያለ ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ከመኖሪያ ቤታቸው የደረሰው የፐ/ር አስራት አስከሬን አዳናን ጸሎተ ፍትሀት ከተደረገ ለት በኋላ በማግስቱ ግንቦት 18 ቀን 1991 ዓ.ም በከፍ ተኛ የህዝብ ቁጥር ታጅቦ ወደ መአህድ ቢሮ አመራ፣ በዛም የተወሰነ ቆይታ ካደረገ በኋላ ስላሴ ካቴድራል እንዳይቀበር በመከልከሉ በባለወልድ ቤተ ክርስቲያን በክብር አረፈ፡፡ ግብአተ መሬቱ ሲፈጸም የሕዝቡ ለቅሶ፣ የተቃውሞ ጩኸት፣ እልህና ቁጭት በቃላት ሊገለጽ የሚችል አልነበረም፡፡ ይህ ያበሳ ጫቸው የጸጥታ ኃይሎች ከቀብር በመመለስ ላይ በነበሩ ወጣቶች ላይ ተኩሰው አንዱን ወዲያው ሲገድሉት አንዱ ቆስሎ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ፡፡ (በኋላ መሞቱ ነው የተሰማው) መአህድ ድረጊቱን ባለማውገዙና ለሞቱትም ሀዘኑን ባለመግለጹ አባ ላትና ደጋፊዎቹን አሳዘነ፡፡

ፐ/ር አስራት ወ/የስ በቀዶ ህክምና ሙያቸው

- የኢትዮጵያ የክብር ኮክብ የፈረሰኛ ደረጃ፣
- የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን የፈረሰኛ ደረጃ፣
- የአብዮታዊ ዘመቻ አርማ፣
- ዓለም አቀፍ የወርቅ ሜሪኩሪ በግል አስ ተዋጽኦ፣
- የቀይ ባህር ኒሻን አንደኛ ደረጃ ተሸል መዋል፡፡

ፐ/ር ዓሥራት ለመጀመሪያ ግዜ ጥርስ ውስጥ የገቡት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ወከለው በተ ገኙበት የሰኔው ኮንፈረንስ ላይ የኤርትራን መገ ንጠል በመቃወም ባደረጉት ንግግር ሲሆን የመ አህድ ሊቀመንበር ሆነው በአጭር ግዜ ትግሉን ከዳር ዳር ማቀጣጠል መቻላቸው ደግሞ ጥርስ ነካሳውን ወደ ተግባራዊ ጥቃት አሸጋገረው፡፡ እናም ደብረ ብርሃን ላይ ባደረጉት ንግግር ጦርነት አውጀዋል ተብሎ የመጀመሪያው ክስ ተመሰረተ ባቸው፡፡ «ከጎጃም ከመጡ ገበሬዎች ጋር በጽ/ ቤታቸው ስለ ጦርነት መክረዋል» የሚል ሁለተኛ ክስ ተጨመረ፣ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እየተጠሩ በዋስ መለቀቁ ሲበዛባቸው አሁንስ ዋስትና በባንክ ማስ ቀመጥ ሊኖርብኝ ነው አሉ፡፡ በመጨረሻም ተፈ ርዶባቸው ወህኒ ወረዱ፣ ህመማቸው እየበረታ ቢሄድም ህክምና ባለማግኘታቸው «ሕክምናውም ቢሆን እኔ ዘንድ ሲደርስ አለው ነገር ይዘገያል» ብለው ነበር፡፡ ህመማቸው ከፍተኛ ደረጃ ከደሰ በኋላ ስንት ህይወት ባሰረዘሙበት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ተኙ፣ ቀጥሎም ወደ አሜሪካ ተላኩ፣ ሐኪሙ አጥተው በሽታቸው እንኳን ሳይታወቅ ይህችን ዓለም ተሰናበቱ፡፡

ከገፅ 13 የዞረ ...የምርጫ ታሪካችን ...

(9) ቁጥሩ ብዙ የሆነ በውጭ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ኢንጂነር ኃይሉ የወሰዱትን እርምጃ ደገፈ፡፡ በውጭ ያለው ኃይል ተቃዋሚውን በፖለቲካም ሆነ በገንዘብ ይደግፋል፡፡ ተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፎች በማድረግ ለኢህአዴግ መንግስት ያለውን ተቃውሞ ግልጿል፡፡

(10) ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል አዲስ አበባ እንደ ደረሱ ውይይቱ ቀጠለ፡፡ ውሳኔው በቀላል ድምጽ ሳይሆን በ2/3 ድምጽ ማለፍ አለበት ሲል ቅንጅት ተስማማ፡፡ አንድ ቀን ፓርላማ አለመግባት ለሚለው አቋም ሌላ ቀን ደግሞ መግባት ለሚለው አቋም ተሰጥቶ በመጀመሪያው ቀን አነገባም የሚለው ወገን ለምን ፓርላማ መግባት ትክክል እንደማይሆን ሲያብራራና ሲከራከር ዋለ፡፡ አንገባም የሚለው ወገን በተመደበለት ዕለት ክርክሩን ጨርሶ በምሽት በቅንጅት ምክር ቤት ስብሰባ ፓርላማ አንገባም የሚለውን አቋም ያራምዱ የነበሩትን ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማሪያም፣ ዶ/ር በፈቃዱ ደገፈ፣ አቶ ግዛቸው ሽፈራውና ሌሎች ሁለት ሰዎች የነበሩበትን መኪና የኢህአዴግ የስለላ ቡድን አስቁመው በመኪናው ውስጥ በነበሩት የቅንጅት ሰዎች ጭንቅላታቸው ላይ መሳሪያ ደቅነው ምራቃቸውን እንደተቶፋቸው እንዳስፈራሩዋቸው ተገለጸ፡፡ ይህ ሁኔታ በመሰማቱ በሚቀጥለው ቀን እንገባ የሚለውን አቋም ይደግፉ የነበሩት የቅንጅት ሰዎች ፓርላማ አንገባም የሚለውን አቋም እንደተቀላቀሉና ይህ ሁኔታ ፓርላማ አንገባም የሚለውን ውሳኔ እንዳጠናከረው በስብሰባው ላይ የነበሩትን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በምንጭነት በመጥቀስ በመጽሐፉ አስፍሯል (ክፍሉ ታደሰ፣ ግንቦት 7፣ ገጽ 213-214)፡፡

(11) መግባት አለመግባት በሚለው ጉዳይ ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ አስታራቂ አሳብ ቀረበ፡፡ ይህ አስታራቂ አሳብ ፓርላማ ለመግባት የሚከተለው ባለስምንት ነጥቦች ቅድመ ሁኔታ እንዲሟላ ጠየቀ፡፡ ቅድመ ሁኔታዎቹ ከተሟሉ ቅንጅት ፓርላማ እንደሚገባ ወሰነ፡፡ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች በቅንጅት ውስጥ የአሳብ መቀራረብ ሊፈጥሩ እንደሚችልና ከህዝብ ሊመጣ የሚችለውን ቁጣም ሊያስታግሱ ይችላሉ ተብሎ ተገመተ፡፡ ቅድመ ሁኔታዎቹ፣ (1) የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ነፃና ገለልተኛ መሆኑን በሚያረጋግጥ መንገድ እንደገና ማዋቀር፣ (2) ፍትሃዊ የመንግስት ሚዲያ አጠቃቀምና የግል ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ እንዲቋቋም፣ (3) የፍርድ ቤት ነፃነትን ማረጋገጥ፣ (4) 1997 ሰኔ 1 ቀን የተካሄደውን ግድያ የሚያጣራ ገለልተኛ አካል በስቶኳይ እንዲቋቋም፣ (5) የፖሊስ፣ የመከላከያና የደህንነት ተቋማት ከፖለቲካ ገለልተኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ (6) የፓርላማና የአዲስ አበባ አስተዳደርን በተመለከተ የወጡ አዳዲስ ህጎች እንዲቀየሩ፣ (7) በፖለቲካ አመለካከታቸው የታሰሩ የፓርቲ አባላትና ደጋፊዎቻቸው እንዲፈቱ፣ የተዘጉ ቢሮዎች እንዲከፈቱ፣ በተቃዋሚዎች ላይ የሚደረገው ወከባ እንዲቆም እና (8) ከላይ የተጠቀሱትን የሚያስፈጽም ፍትሃዊ አካል እንዲቋቋም

ኢህአዴግ ቅድመ ሁኔታዎቹን ሳይቀበል ቀረ፡፡ ከምርጫው ማጣራት ጀምሮ ኢህአዴግ ማጥቃት ላይ ስለነበር ቅንጣትም እንኳን ማፈግፈግ ወይንም ለተቃዋሚው ምላሽ መስጠት አልፈለገም (ክፍሉ ታደሰ፣ ግንቦት 7 ገጽ 214)፡፡ ከቀረቡት 8 ነጥቦች ውስጥ በተለይ 1ኛውን እና 2ኛውን ጉዳዮች ህብረት (ጉዲና እና በየነ) ሲሟሉ የሚገቡ የምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች በሚል ከአቶ መለስ ጋር በመደራደር ላይ ሳሉ ቅንጅት ካለምንም ቅድመ ሁኔታ በምርጫው እንሳተፋለን ማለቱን እና አቶ መለስ የቅንጅትን አቋም በመጠቀም ህብረት የጀመረውን ድርድር ቸል እንዳሉት እናስታውሳለን፡፡

(12) 1998 በህዳር ወር የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኦብኮ) ከሁለት እንዲከፈል ተደረገ፡፡ በህዳር ወር አጋማሽ በኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ ስም 4 ሚሊዮን ህዝብ ለምክር ቤቱ ከመረጣቸው 39 ተወካዮች ውስጥ 37ቱ ከዶክተር መራራ ጉዲና ጎን ቢቆሙም ምርጫ ቦርድ ከአቶ መለስ በመወገን በኦብኮ ውስጥ መፈንቅለ አመራር ለፈጸመው ቡድን እውቅና ሰጠ፡፡ በኦብኮ ላይ ይኸን አይነት እርምጃ የተወሰደበት ምክንያት ዶክተር መራራ ጉዲና ከህብረቱ እንዲወጣ፣ ከቅንጅት እንዳያብር፣ ወይንም ደግሞ ከህወሃት ጋር ጸረ-ትፍጠኛ ግንባር እንዲፈጥር በተደጋጋሚ የተሰጠውን ምክር ባለመስማቱ ነበር፡፡

ዝክረ - ግንቦት 20 ሰለባዎች

ሐኪም አጥቶ የሞተው ሐኪም!

ታምራት ታረቀኝ

«ጦርነት ግድ ሲሆን የሚገባበት ሁኔታ እንጂ እንደ ትልቅ ጀብዱ የሚወደስ ባህል መሆኑ መቆም አለበት፡፡ በተለይም ጦርነቱ የውስጥ ሲሆን ሰላማዊ አማራጮች ሁሉ ከተሟጠጡ በኋላ ብቻ የሚመረጥ መንገድ ሆኖ መታየት አለበት፡፡ የፖለቲካ ልዩነቶችንም በተመለከተ እንዱ ወገን ምንግዜም ቢሆን ፍጹማዊ እውነትን ሊታደል እንደማይችል ተገንዝቦ የሌላውን ወገን ሀሳብ እህ ብሎ ማዳመጥ መቻል ይኖርበታል፡፡ የተቀዋሚ ወገን አየሁ ብሎ ቃታ ለመሳብ መጣደፍ ዞሮ ዞሮ ሀገርን በብርቱ የሚጎዳ መሆኑን ከቀይ ሽብር ያተረፍነው ትልቁ ትምህርት ነው፡፡ ከከፋ ከከፋ ተቀዋሚን ላጭር ግዜ አስሮ ማቆየቱ ይመረጣል፡፡ ማእ ዜ ዱንግ እንዳለው የተቀነሰሰን እንንተ መልሶ መትከል አይቻልምና፡፡» ይህን ያሉት ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ ናቸው፡፡ ያለመቻቻል ፖለቲካ ሰማዕ ታት፣ መቼም እንዳይደገም በሚል ስያሜ የሰማዕ ታት ማህበር ባሳተመው መጽፍ ላይ በሰፈረው ጽሁ ፋቸው፡፡

ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ እነሆ በሚቀጥለው ሳምንት 23 ዓመቱን ያስቆጥራል፡፡ በየአመቱም ሆነ በየምክን ያቱ የእርስ በእርሱ ጦርነት አሸናፊነቱን ጀብዱ ይተር ካል፣ ይፎክራልም፡፡ ተቀዋሚውን ማጥፋትን እንጂ እህ ብሎ ማዳመጥን ዛሬ ድረስ ሊካነው አልቻለም፡ ፡ የፖለቲካ ልዩነት ከአንድ ሀገር ልጅነት በላይ ሆኖ በጠላትነት የሚያስተያይ የመሆኑ ነገር እየታደሰ እንጂ እየከሰመ ሊሄድ አልቻለም፡፡ ፋኖ ሆኖ መዋጋ ትና ቤተ መንግሥት ተቀምጦ ሀገር መምራት ፍጹም የተለያዩ ነገሮች በመሆናቸው ህወሓት/ኢህአዴግ ለ17 ዓመታት የተናገራቸውንና ቃል የገባቸውን ተግባራዊ ማድረግ ተስኖት ሲቃወመውና ሲያውግዘው የነበረ ውን ድርጊት ለመፈጸም ግዜ አልወሰደበትም፡፡

በደኖ፣ ወተርና አርባ ጉጉ የተፈጸሙ ኢሰብአዊ እልቂቶችን አንድ ብለን፣ የአዋሳውንና የጋምቤላ ውን ዳስሰን በምርጫ 97 ተሸጋግረን ሰሞኑን በየዩ ኒቨርስቲዎች የተፈጸመውን ብንቃኝ መነሻ ምክን ያቱ መፍትሄ አገኝቷል የተባለው የብሄር ብሄረሰብ መብት እና የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ጉዳይ ጥያቄ እያስነሳና ተገቢ ምላሽ መስጠት እየተሳነ የተ ፈጸመ ናቸው፡፡ «የሞተው አንድ ሰው ነው፡፡ ያም ቢሆን አድማ መበተኛ መሳሪያ ከቀድሞው መንግ ሥት ባለመውረሳቸን ነው፡፡ እሱም ቢሆን የኢሲፓ አባል ነው፡፡» የተባለበት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ የነበረው ተስፋሁን ወርቁን፣ (የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተመድ ዋና ጸኃፊ የነበሩ ትና ለኤርትራ መገንጠል በብርቱ የሰሩት ግብጻዊው ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊን አዲስ አበባ መምጣት በመቃ ወም ባደረጉት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የተገደለ ነው) በማን አለብኝነት በጠራራ ጸሐይ በአደባባይ የተገደ ሉትን አቶ አሰፋ ማሩን፣ በእስር ቤት ተሰቃይተው ሐኪም አጥተው የሞቱትን እውቁን የቀዶ ህክምና ሐኪም ፕ/ር ዓሥራት ወልደየስን፣ እንዲህ እንዲህ እያልን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ በየመግ ለጫው የጠቀሳቸውን የተገደሉና ታፍነው የተሰወሩ ዜጎችን እንዘርዝር ብንል የጋዜጣ ገጽ አይበቃንም፡፡ ከላይ በገለጽኩት መጽጋፍ ውስጥ የሰፈረው የማህ በሩ መልእክት እንዲህ ይላል፡፡ «መቼም እንዳይደገም የሚለው ውሳኔ እንደዋዛ መወሰድ የለበትም፣ እያንዳ ንዱ እንደ ቃል ኪዳን አድርጎ በመውሰድ ሁሉ የሚመ ራበት መርህ ማድረግ አለበት፡፡ ያጣናቸውን ንጹኃን ወንድም እህት ልጅ፣...የምንዘክረው ሌሎች ንጹኃን ተሰውተው ወገኖቻቸውም እንደኛ በህዘንና በሰቆቃ

ሲያስታውሷቸው እንዳይኖሩ በመታደግ ነው፡፡»

ዶ/ር የራስ ወርቅ አድማሴ በዚሁ መጽጋፍ ውስጥ በሰ ፈረው ጽሁፋቸው «ከኛ ትውልድ ስህተት በመማር የልጆቻችንን ትውልድ ከፖለቲካ ግድያ፣ ከዘር ማጥፋት ፍጅትና ከስጋትም ጭምር ነጻ በሆነችና ፍትህ በነገሰባት ኢትዮጵያ እንዲኖሩ እንመኛለን፡፡ ይህን ምኞታችንን እውን ካደረግን ደግሞ እሱ ጊዜ የማይሽረውና የማያደበዝዘው ዕውነተኛው የሰማዕ ታት መታሰቢያ ይሆንልናል፡፡» ብለው ነበር፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ የማህበሩ መልእክትም ሆነ የዶ/ር አድማሴ ምኞት እውን ባለመሆኑ እነሆ ዛሬም የዚህ ዘመን ሰማዕታትን እንዘክራለን፡፡ ነገር ግን በአንድ ግዜ የጋዜጣ ጽሁፍ ሁሉንም መዘከር ባለመቻሉ የዛሬ 15 ዓመት ግንቦት 18/1991 ዓ.ም ግብአተ መሬ ታቸው የተፈጸመውን ፕ/ር ዓሥራት ወልደየስን እና ስታውሳለን፡፡

ሐኪም አጥቶ የሞተው ሐኪም

እለቱ ግንቦት 7/1991 ዓ.ም፣ ቦታው አሜሪካን ሀገር ዋሽንግተን አካባቢ ቨርጂኒያ ውስጥ ነው፡፡ ከተሰ በሰበው ሰው መካከል አድሜና ጤና ያዳከማቸው መንፈሰ ጠንካራ ሰው በከዘራና በሰው እየተረዱ ወደ መድረኩ ቀረቡና መነጋገሪያውን በመጨበጥ «ዛሬ ሀቀኛ ኢትዮጵያዊነት፣ የሕዝብ ወገናዊነት ወንጀል በሆነበት ጊዜ አሥራት አንተ ከኢትዮጵያዊነት በስተ ቀር ሌላ ወንጀል የለብህም፡፡ ዛሬ የእኛ ምስክርነት ለአንተ አያስፈልግም፣ ዓሥራት ከሰማዕታት ጎን ቆመህ ግን የሞትከላትን ኢትዮጵያ እኛ ምድራዉያኑ እንዴት እንደተቀራመትናት የምትጠይቀን፣ ገመናዋን እንዴት እንዳረከስነው የምታጋልጠን፣ በጦርነት አለንጋ ገላዋን እንዴት እንደገነጣጠልናት የምትመሰክርብን አንተ ነህ፡፡ የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳዬ ነው የምንል ዜጎች ሁሉ ዛሬ ከዚህች መራራ ጥያቄ እንደማናመልጥ የምትመሰ ክርብን አንተ ነህ፡፡ ዓሥራት ዛሬ እንደሚባለው በሐ ረርጌ ድሬዳዋ ልጅነትህ ወይም በመዝዜነትህ ወይም በሸዋነትህ ወይም ስለ አማራነትህ ሳይሆን በቁርጠኛ ኢትዮጵያዊነትህ ነው፡፡ ዛሬ መላው የኢትዮጵያ ልጅ እጅ የሚነሳህ፡፡ ዛሬ በ21ኛው ሳይንሳዊ ዘመን ዘመነ ጥምቀት መግቢያ በር ላይ በማኪያቬሊ ያረጀ ሾተል እንደ ጲላጦስ የሕዝብን ጀግና ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ እጅ መታጠብ በሕዝብም ፊት ከተጠያቂነት ከታሪ ክም ፊት ከኃላፊነት ማናችንም አንድንም» በማለት ተናገሩ፡፡

እኚህ ሰው ብዙም ሳይቆዩ አስራትን ተከትለው ይህችን ምድር የተሰናበቱት ባለቄኔው ሎሬት ጸጋየ ገብረ መድህን ነበሩ፡፡ በዚህ የአስራት አስከሬን አሸ ኛኘት ሥነ-ሥርዓት ላይ የወቅቱን የተመድ ዋና ጸኃፊ ኮፊ አናን ጨምሮ በርካታ ሰዎች ተገኝተው ንግግር አድርገዋል ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ወቅት መአህድ በነውጥ ውስጥ ነበር፡፡ ከሰኔ 1988 ዓ.ም ጀምሮ የተባረረነው ወጣቶች ውስጥም ሆነን ከተባረረንም በኋላ መአህድን ለማደስ ባደረግነው ትግል ተሸንፈን አማራጭ ኃይሎች አዳራሽ ፈቅዶልን ስለመጻኢ ተግባራችን በመምከር ላይ ነበርን፡፡ ከእኛ መባረር በኋላ በቀኝ አዝማች ነቅዐጥበብ በቀለ ካቢኔ ላይ ተቃውሞ ያነሱ ወገኖች ደግሞ የመአህድና የፕ/ር ዓሥራት ተቆርቋሪዎች በሚል አዲስ ትግል ጀምረ ዋል፡፡ ቀድመን እንጠረጥረው የነበረውና ኋላ ተስፋዬ ገብረአብ ያረጋገጠው ቀኝ አዝማች በደሀንነት ሹሙ ክንፈ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ሻማዋ እንዳትጠፋ የሚል ምክንያት እየሰጡ መአህድን አለምም የለምም የማይባልበት ደረጃ አድርሰውት የሚቃወሙዋቸውን ሁሉ ገለል እያስደረጉ የተቀመጡበት ግዜ ነበር፡፡

እንደተለመደው አሁድ ማለዳ በቅሎ ቤት በነበረው የአማራጭ ቢሮ አዳራሽ በርካታ ሰዎች ተሰብስበናል፣

ወደ ገፅ 15 የዞረ...